የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


ድህረ ምረቃ መርሀ ግብር

# የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ (በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በድሬ ጅቦ እና በአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የቀረበ ጥናት)


በጽጌ ግርማ



መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

# የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ (በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ በድሬ ጅቦ እና በአባገዳ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የቀረበ ጥናት)

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎች ጥናት፣ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

ለአማርኛ ማስተማር መርሐግብር ለማስተርስ ዲግሪ ከፊል

ማሟያነት የቀረበ ጥናት

በጽጌ ግርማ

አማካሪ፣ዳዊት ፍሬሕይወት (ዶ.ር)

መስከረም 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስ፣የቋንቋዎችጥናት፣ጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

## ድህረምረቃ መርሐግብር

### የፈተና ቦርድ ማረጋገጫ

ይህ ጥናት ‹‹የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አተገባበር››በሚል አማርኛን ማስተማር (TeAm) የሁለተኛዲግሪማሟያየቀረበጥናት ሲሆን መስፈርት ስለማሟላቱ በጥናቱ አማካሪና ገምጋሚዎች ተረጋግጧል፡፡

**በጽጌ ግርማ**

**የፈታኝ ቦርድ አባላት**

አማካሪ________________________ፊርማ ____________________ ቀን____________

የውጭ ፈታኝ__________________ ፊርማ_________________ቀን_______________

የውስጥፈታኝ__________________ ፊርማ_________________ቀን_____________

# ምስጋና

በቅድሚያ በቸርነቱና በኃይሉ አስጀምሮ ለዚህ ደረጃ እንድደርስ ላበቃኝ የንጉሶች ንጉስ ሀያሉ እግዚአብሔር ከእናቱ ከቅድስት ድንግል ማሪያም ጋር ስሙ ለዘላለም የከበረና የተመሰገነይሁን፡ አሜን፡፡

በመቀጠል የጥናቱን ርዕስ በማስተካከል ከመነሻው ትክክለኛ አቅጣጫ እንዲይዝ በማድረግ፣ የጥናቱን ረቂቅ ከመነሻ እስከ መድረሻ ማለትም ጥናቱ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይሉ ጽሑፉን በጥንቃቄ በማንበብ እያንዳንዱን ቃል፣ ሐረግና ዓረፍተነገር በማየት የፊደላት ግድፈቶችንም ሆነ ሰዋስዋዊ ግድፈቶችን በማቃናትና በማረም፣ አስተያየቶችን እና የማሻሻያ ሀሳቦችን በመስጠት፣ አባታዊ ምክሮችን በመለገስ እንዲሁም ጥናቱ ውጤታማ ይሆን ዘንድ እውቀታቸውን እና ልምዳቸውን በማካፈል ከፍተኛ ሙያዊ ድጋፍ በማድረግ ለረዱኝ የመልካም ባህርይ ተምሳሌት ለሆኑት ለአማካሪዬ ለዶ/ር ዳዊት ፍሬህይወት ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

በሌላ በኩል ለመማሪያነት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችን በማቅረብ ያለምንም ችግር ትምህርቴን በተገቢው መንገድ እንድከታተልና ለዚህ ደረጃ እንድደርስ ላበቃኝ ለአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ እንዲሁም በዚህ ዩኒቨርስቲ ውስጥ ላስተማሩኝ መምህራን በሙሉ ላቅ ያለ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች ሲሰበሰቡ ተማሪዎቹን በማስተባበር እገዛ ላደረጉልኝ የድሬ ጅቦ እና የአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን እንዲሁም የጽሑፍ መጠይቁንለመሙላት ፈቃደኛ በመሆን ለተባበሩኝ ተማሪዎች በሙሉ ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ በቃለ መጠይቁ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ለሆኑት የሁለቱም ትምህርት ቤት የአማርኛ መምህራን ምስጋናዬ ላቅ ያለ ነው፡፡

በተጨማሪም ተገቢ የሀሳብ ድጋፋቸው ላልተለየኝ ጓደኞቼ እና በተለይ በኮምፒዩተር መጻፍና የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ለተባበረኝ ለውድ ወንድሜ ዱጉማ ቦኪ ከነቤተሰቦቹ ከፍ ያለ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ፡፡ በመጨረሻም ፍቅራቸው፣ ትህትናቸው እና ትዕግስታቸው ላልተለየኝ ለልጆቼ ለፍራኦል፣ ለበርሱፍቃድ እና ለየአብስራ ኃ/ገብርኤል እንዲሁም ለባለቤቴ ለኃ/ገብርኤል ክንፈ ወደር የሌለውን ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

## የይዘት ማውጫ

ምስጋና ........................................ i

ሰንጠረዥ ማውጫ ........................................ vi

አጠቃሎ ........................................ vii

ምዕራፍ አንድ ........................................ 1

መግቢያ ........................................ 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ........................................ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................ 2

1.3. የጥናቱ ዓላማ ........................................ 3

1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ ........................................ 3

1.5. የጥናቱ ወሰን ........................................ 4

1.6. የጥናቱ ውስንነት ........................................ 4

ምዕራፍ ሁለት ........................................ 5

ክለሳ ድርሳናት ........................................ 5

2.1. የሰዋስው ምንነት ........................................ 5

2.2. በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት ........................................ 8

2.3. የሥነት ምህርታዊ ሰዋስው ምንነት ........................................ 14

2.4. የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች ........................................ 18

2.5. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማቅረቢያ ባህርያት ........................................ 19

2.5.1. ትክክለኛነት ........................................ 19

2.5.2. ግልጽነት ........................................ 19

2.5.3. አፍላቂነት ........................................ 20

2.5.4. ተመጣጣኝነት ........ 20
2.5.5. ተገቢነት ........ 20
2.5.6. አሳታፊ እና አስደሳችነት ........ 20
2.5.7.ገደብ (ውስንነት) ........ 21
2.5.8. ጽንሰ ሀሳብን ማስጨበጥ ........ 21
2.6. የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ ........ 21
2.7. የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ዘዴ ........ 23
2.7.1. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ........ 24
2.7.2. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ........ 25
2.7.3. ሰዋስውን እንደክሂል ማቅረቢያ ዘዴ ........ 26
2.7.4. ከዝርዝርወደ አጠቃላይ፣ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሄድ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ........ 27
2.8. በትምህርትነት የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ........ 28
2.8.1. ድምጾች ........ 28
2.8.2. ምእላዶች ........ 29
2.8.3. ቃላት ........ 29
2.8.4. ሀረጋት ........ 30
2.8.5. ዓረፍተ ነገሮች ........ 30
2.9. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ትኩረት ........ 30
2.10. የሰዋስው ትምህርት ዝግጅት ........ 31
2.10.1. ዓላማ ........ 32
2.10.2 .መልመጃዎች ........ 32
2.10.3. መርጃ ( ደጋፊ) መሳሪያዎች ........ 33
2.11. የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ ........ 33

2.12. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማለማመጃ ስልቶች ........ 35

2.13. የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ደረጃዎች ........ 37

2.13.1 የሰዋስው ትምህርት የአቅርቦት ደረጃ ........ 37

2.13.2 . የልምምድ ደረጃ ........ 38

2.13.3. የአፍልቆት ደረጃ ........ 39

2.13.4. የምጋቤምላሽ (የግብረመልስ) ደረጃ ........ 40

2.14. የቋንቋ መምህራን ሊኖራቸው የሚገቡ ሰዋስዋዊ እውቀቶች ........ 41

2.14.1. ሰዋስውና ተግባቦት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ማወቅ ........ 41

2.14.2. የሰዋስውና የተግባቦት እውቀት መኖር ........ 42

2.14.3. የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ማወቅ ........ 42

2.14.4. ሰዋስውን በውጤት ተኮር ዘዴ የማቅረብ እውቀት መኖር ........ 42

2.14.5. ንጽጽራዊ የሰዋስው እውቀት መኖር ........ 43

2.15. ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት የሀገር ውስጥ ጥናቶች ክለሳ ........ 43

የአጠናን ዘዴ ........ 47

3.1 . የናሙና አመራረጥ (አወሳሰድ) ስልት ........ 47

3.1.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 47

3.1.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 47

3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 48

3.2.1. ምልከታ ........ 48

3.2.2. ቃለ መጠይቅ ........ 49

3.2.3. የጽሑፍ መጠይቅ ........ 50

3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ ........ 51

ምዕራፍ አራት ........ 52

የመረጃውጤት ትንተና ........ 52

4.1.1. የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ ........ 52
4.1.2. የተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታ ........ 53
4.2. የመረጃ ውጤት ትንተና ........ 54
4.2.1. የመምህራን የትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ ........ 55
4.2.2. ተማሪዎች ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት እና ፍላጎትን በተመለከተ ........ 59
ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ: ........ 60
4.2.3. መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር በተመለከተ ........ 61
4.2.4. የመምህራን የመርጃ መሳሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ ........ 63
4.2.5.ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የሰዋስው ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብን በተመለከተ ........ 65
4.2.6. የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን በመጠቀም የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ ........ 67
4.2.7. የማስተማሪያ ስልቶችን በተመለከተ ........ 70
4.2.8. ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ማድረግን በተመለከተ ........ 71
4.3. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ ........ 73
ምዕራፍ አምስት ........ 77
ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 77
5.1. ማጠቃለያ ........ 77
5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች ........ 80
ዋቢመጻሕፍት ........ 82
አባሪዎች ........ 87

## ሰንጠረዥ ማውጫ


ሠንጠረዥ 1፡- የመምህራንን ዳራ የሚያሳይ ሠንጠረዥ፡ ... 52

ሠንጠረዥ 2፡-የተማሪዎችን ዳራ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ... 53

ሠንጠረዥ 3፡የመምህራንን የትምህርት ዝግጅት በተመለከተ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ ... 55

ሠንጠረዥ 4፡መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የዕለቱን የትምህርት ርዕስከ ማስተዋወቅና አላማውን በግልጽ ከማብራራት አንጻር ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ... 56

ሠንጠረዥ 5፡መምህርቷ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ ቃላትን ሀረጋትንና ዓረፍተ ነገሮችን በምሳሌነት የማስተማር ሁኔታን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ ... 58

ሠንጠረዥ 6፡የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተማሪዎች ተነሳሽነትና ፍላጎት እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር ከምልከታ የተገኘው መረጃ ... 59

ሠንጠረዥ 7፡ ተማሪዎች ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትን በተመለከተ ... 60

ሠንጠረዥ 8፡ተማሪዎችን የማበረታታትና ከተማሪዎች ጋር መልካም መስተጋብር የመፍጠር ሁኔታን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ፡ ... 61

ሠንጠረዥ 9፡ መምህራን መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማስተማራቸውን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡ ... 63

ሠንጠረዥ 10፡-መምህርቷ በክፍል ውስጥ መርጃ መሳሪያዎችን ... 64

ሠንጠረዥ 11፡-መምህርቷ ወደ ክፍል ይዘው የሚመጡት የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማራኪና ሳቢ በሆነ መልኩ ማቅረባቸውን በተመለከተ ከተማሪዎች ... 65

ሠንጠረዥ 12፡- የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የሰዋስው ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ ... 66

ሠንጠረዥ13፡- መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ሲያስተምሩ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸውን በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ፡ ... 67

ሠንጠረዥ 14፡-የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን ተጠቅሞ ማስተማርን በተመለከተ ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ ... 68

ሠንጠረዥ 15፡-ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች በየደረጃ ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ፡ ... 69

ሠንጠረዥ 16፡ የማስተማሪያ ስልቶችን በመጠቀም ማስተማርን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ፡ ... 70

ሠንጠረዥ 17፡-ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርትን ሲማሩ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ እድል መስጠትን በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ ... 71

ሠንጠረዥ 18፡- ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ሁኔታን ... 72

# አጠቃሎ

*የጥናቱአብይ ዓላማ የመምህራንን የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር በመፈተሽ የተስተዋሉ ችግሮችን ለይቶ በመጠቆም የመፍትሄ አቅጣጫዎች ተጠቁመዋል፡፡ ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተግባራዊ አድርጓል፡፡ የጥናቱ ተሳታፊ ተማሪዎች ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች እና የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ሲሆኑ እነዚህ ዋነኛ የመረጃ ምንጮች ናቸው፡፡ ጥናቱ ጥያቄ አድርጎ በተነሳባቸው ነጥቦች ዙሪያ የቋንቋ ምሁራን ያቀረቧቸውን ንድፈሃሳባዊ ብያኔዎች መሰረት በማድረግ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር በሚለው ርዕስ ስር መነሳት ያለባቸውን ነጥቦች በዝርዝር ለማየት ሞክሯል፡፡ የጥናቱ አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የክፍል ውስጥ ምልከታ ሲሆን ከተማሪዎች የጽሑፍመጠይቅ እና ከመምህራን በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችም በመጠናዊና በአይነታዊ የመረጃ መተንተኛ ስልቶች አንድ በአንድ ለመተንተን ተሞክሯል፡፡ ከመረጃ ምንጮቹ የተገኙት መረጃዎችም እርስ በእርስ ባላቸው ተዛምዶ አንድ ላይ በማደራጀት በምዕራፍ አራት ስር ለመተንተን ተችሏል፡፡ ከጥናቱ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው ታላሚዎቹ መምህራን በክፍል ውስጥ በትግበራ ወቅት የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን አለመጠቀማቸው፣ ተማሪዎች በቡድን እንዲወያዩ እና ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲያንጸባርቁ እድል አለመስጠት፣ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን አለመጠቀም፣ እንዲሁም ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ላይ ድክመት እንዳላቸው መመልከት ተችሏል፡፡በሌላ በኩል ታላሚዎቹ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ጥሩ መስተጋብር እንዳላቸው ታይቷል፡፡ በአጠቃላይ የታዩትን ጠንካራ ጎኖች በማበረታታት፣ ደካማ ጎኖቹ ደግሞ ሊቀረፉ የሚችሉበትን እና የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሻለና ውጤታማ ያደርጋሉ ተብለው ከታመነባቸው ሀሳቦች ውስጥ የመምህራንን የትምህርት ዝግጅት በተመለከተ መምህራኑ ትምህርቱን ከማቅረባቸው በፊት በቂ ዝግጅት ቢያደርጉ፣ የሰዋስው ትምህርቱን ሲያቀርቡ የማለማመጃ ስልቶችን እንደ ምልልስ፣ሚና ጨዋታ፣የመሳሰሉትን እና የአቀራረብ ደረጃዎችን በክፍል ውስጥ በመጠቀም ቢያስተምሩ፣ሰዋስውን በተናጠል ከማስተማር ይልቅ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው ቢያቀርቡ፣ ወዘተ. የሚሉትን የመፍትሄ ሀሳቦች በመጠቆም ጥናቱ ተጠናቋል፡፡*

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ቋንቋ ከሰው ልጅ ጋር የጠበቀ ቁርኝት አለው፡፡የሰው ልጅ የእለት ተእለት ተግባሩን የሚያከናውንበት እንዲሁም የእርስ በርስ ግንኙነት በዋናነት የሚመሰርትበት አንዱ የመግባቢያ መሳሪያ ቋንቋ ስለሆነ ነው፡፡ ይህም በቋንቋ ባህሉን፣ወጉን፣ ልምዱን፣ እሴቱን ፣ስልጣኔውን፣ እድገቱን፣ወዘተ. ይገልፅበታል፤ከትውልድ ወደ ትውልድ ያስተላልፍበታል፤ከዚያም አልፎ ተርፎ ቋንቋውን በስርዓትና በአግባቡ ይጠቀማል (ጌታሁን 2011፣ix)፡፡በተጨማሪም ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር ሰዋስው እና ቋንቋ ጥብቅ የሆነ ቁርኝት እንዳላቸው ጌታሁን (2013፣vi) እንደሚከተለው ገልጸዋል፡፡

> *ቋንቋ እስካለ ድረስ ሰዋስው አለ፡፡ ምክንያቱም የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ አባላት በንግግርም ሆነ በጽሑፍ ለመግባባት የቋንቋውን ሰዋስው በማወቃቸው መሆኑን ላይገነዘቡት ይችላሉ፡፡በዚህም ምክንያት ቋንቋውን እንደሚያውቁት እንጂ፣ ሰዋስውን እንደሚያውቁት አያስቡትም፡፡ ይህ የሚሆንበት ምክንያት የአፍ መፍቻ ቋንቋ ሲለመድ ይሁነኝ ተብሎ በሙሉ ንቃት ሳይሆን በከፊል ንቃት (subconscious) በመሆኑ ነው፡፡ በሁለተኛ ቋንቋ ግን መግባባት የሚቻለው ሰዋስዋዊ ስርዓቱን መደበኛ በሆነም ይሁን መደበኛ ባልሆነ መንገድ ይሁነኝ ብሎ በመማር በመሆኑ ይህ ማወቅ አለማወቅ የሚባለው ጉዳይ አይኖርም፡፡*

ከምሁሩ ገለጻ መረዳት የሚቻለው ቋንቋ የሰው ልጅ የሚግባባበት ትልቁ መሳሪያ መሆኑን እና ቋንቋና ሰዋስው ደግሞ የጠበቀ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን ነው፡፡ ይህም ቋንቋ ያለሰዋስው እውቀት መዳበር የማይችል መሆኑንና በሁለተኛ ቋንቋ መግባባት የሚቻለው ሰዋስዋዊ ስርዓቱን በመማር መሆኑን ነው፡፡

እ.ኤ.አ. በ 1960 ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ ሳይንሳዊ የሆኑ ትንታኔዎች በስነልሳን ምሁራን እየቀረቡ ለቋንቋ መማር ማስተማር ስራ ቢውሉም የሰዋስው ትንታኔ ብቻውን ለቋንቋ ትምህርት መጎልበት ያለው ሚና አናሳ ነው በሚል ይህ አቀራረብ ትችት ይሰነዘርበት ነበር፡፡ በዚህም የተነሳ የቋንቋ ትምህርት በሰዋስው ትክክለኛነት ላይ ያተኮረ ከመሆን ይልቅ ተግባቦት ላይ ማተኮር አለበት የሚል ሀሳብ እየገነነ በመሄዱ ከመዋቅራዊ ስነልሳን ይበልጥ ማህበራዊ ስነልሳን ተቀባይነት እያገኘ መጥቷል(Nunan፣1991፣Bygate,etal. 1994)፡፡

እ.ኤ.አ. በ 1970 እና 80ዎቹ አመታት ደግሞ ተግባቦት ላይ ትኩረት አድርጎ የነበረው የቋንቋ ትምህርትአቀራረብ ተቃውሞ ገጥሞት ነበር፡፡ የተቃውሞውም መነሻ ‹‹ያለሰዋስው እውቀት ተማሪዎች ተገቢ የሆነ የቋንቋ ብቃት ላይ መድረስ አይችሉም›› የሚል ነበር፡፡

ተግባቦት በቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪዎች የሚደርሱበት ግብ ነው፡፡ እዚህ ግብ ላይ ለመድረስ ደግሞ የሰዋስው እውቀት ከፍተኛ እገዛ እንደሚያደርግ እና እንደውም ሰዋስው የአንድ ቋንቋ የጀርባ አጥንት በመሆኑ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ትኩረት ሊያጣ አይገባም በሚል ሰዋስው እና ተግባቦት እኩል ትኩረት ሊያገኝ ይገባል ብለው የሚሰጡት የቋንቋ ምሁራን ሀሳብ ተቀባይነትን እያገኘ መጣ (Bygate , etal, 1994 ፤ Kachru ፣ 2010)፡፡ ይህ ሃሳብ የመዋቅራዊ ስነልሳንና የማህበራዊ ስነልሳንን ፍልስፍና አጣምሮ በመያዝ የቋንቋ ትምህርት አቀራረብ ተግባቦት ላይ ወይም ሰዋስው ላይ ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ሁለቱንም ባማከለ መልኩ መቅረብ እንዳለበት የሚያምን በመሆኑ አብዛኞቹን የስነልሳን ምሁራን ያስማማ ዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት እሳቤ ነው (Nunan ፣1991)፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከተሰጡት የምሁራኑ ገለፃ መረዳት የሚቻለው የሰዋስው ትምህርት ከቋንቋ ክሂሎችም ሆነ ከሌሎች የቋንቋ የእውቀት ዘርፎች ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑ ነው፡፡ ይህም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት በክፍል ውስጥ የሰዋሰው ትምህርት ይዘቶች የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው መርሆችን መሰረት በማድረግ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት እና አጠቃቀም አጣምረው እንዲማሩ የሚያስችል አቀራረብ መሆን እንዳለበት የሚያስረዳ ነው፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

የዚህ ጥናት አዘጋጅ ይህንን ጥናት ለማካሄድ የተነሳችበት ዋና ምክንያት በኦሮምያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ ባሉ ሁለት በተመረጡ የድሬ ጅቦ እና የአባገዳ ትምህርት ቤቶች አንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል ለመፈተሽና ለታዩት ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ ለመጠቆም ነው፡፡ ይህም በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ የሚስተዋሉ የሰዋስው ስህተት ችግሮች ማለትም የቁጥር፣ የጾታ፣ የመደብ አለመስማማት እና የመሳሰሉት ችግሮች ተስተውለዋል፡፡

ለዚህም አጥኚዋ በድህረምረቃ መርሃግብር ኤም.ኤ.ማስተር ስትከታተል በተማረችው የሰዋስው ትምህርት ስለ ስነትምህርታዊ ሰዋስው ካገኘችው እውቀት (ግንዛቤ) በመነሳት  በስራ ላይ ባለችበት ወይምበ ቆየችበት አመታት በተማሪዎች ላይ የሚታይባቸውን ችግሮች መነሻ በማድረግ ይህ ችግር የተከሰተው የመምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የእውቀት ማነስ ይሆን? ፤ የሰዋስው ትምህርት የአቀራረብ ዘዴዎች ባለመጠቀም ይሆን? ወይስ የማለማመጃ ስልቶችን በክፍል ውስጥ ባለመጠቀም ይሆን? የሚሉትን ጥያቄዎች እንደ መነሻ በማድረግ ይህንን ጥናት አካሂዳለች (አድርጋለች)፡፡

## 1.3. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኦሮምያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ በድሬ ጅቦ አንደኛ ደረጃ እና በአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ8ኛ ክፍል የአማርኛ የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን መፈተሽ ነው፡፡በዚህ አጠቃላይ ዓላማ ላይ በመመርኮዝ ጥናቱ የሚከተሉት ዝርዝር (ንዑሳን) ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

- የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል መመርመር፣
- የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ እና የሰዋስው ትምህርት  አተገባበር ስልቶችን በተመለከተ ያለውን ጠንካራና ደካማ ጎን መፈተሽ፣
- በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን በመመልከት የታዩትን ችግሮች መፈተሽ፣ ለሚሉት ለእነዚህ የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ምላሽ በመስጠት፣ በአጠቃላይ የጥናቱን አብይ ዓላማ ለማሳካት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ሲጠናቀቅ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ይኸውም፡-

- መምህራን በዘላቂነት የሰዋስው ትምህርትን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው እንዲያስተምሩና ተማሪዎችም በቋንቋው ጥሩ ተግባቦትን እንዲያዳብሩ ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግ መሆኑን ይጠቁማል፡፡
- የመማር ማስተማሩ ሂደት የሰዋስው ይዘቶችን ዘመናዊ የማስተማር ዘዴ አጠቃቀምን ያዳብራል፡፡

- ለመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆችም የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ እና ግራ የማያጋቡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን (መልመጃዎችን)አካተው ማቅረብ እንዳለባቸው ይጠቁማል፡፡
- በተጨማሪም በዚህ ርዕስ ዙሪያ ለሚያጠኑ አጥኚዎች እንደመነሻ ሆኖ ያገለግላል፡፡

## 1.5. የጥናቱ ወሰን

የጥናቱ ወሰን በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ በ8ኛ ክፍል የአማርኛ የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ በተመለከተ በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው፡፡ ምክንያቱም ከጊዜ ማነስ እና ከወጪ አንጻር የሌሎች የክፍል ደረጃዎችንና የሌሎች ትምህርት ቤቶችን ለመፈተሽ አልተቻለም፡፡

## 1.6. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት አስተማማኝነቱ ከፍ እንዲል ለማድረግ አጥኚዋ የተለያዩ ጥረቶችን አድርጋለች፡፡ ከእነዚህም መካከል የጥናቱን ዓላማ መንደፍ፣ አስፈላጊውን መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ የመረጃ ምንጮችን (ተሳታፊዎችን) መምረጥ፣ተገቢ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችን መምረጥ፣ ተገቢነት ያላቸውን ጥያቄዎች ማዘጋጀትና የቅድመ ሙከራ ጥናት ማካሄድ፣ተገቢ የመረጃ መተንተኛ ስልቶችን መምረጥ፣መሰረታዊ ጥያቄዎችን መነሻ በማድረግ ተገቢ የውጤት ትንተናና ማብራሪያ መስጠት፣ ማጠቃለያና የመፍተሄ ሀሳቦችን ማቅረብ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡ ሆኖም ግን ይህ ጥናት በአንድ ወረዳ ስር የሚገኙ ሁለት በተመረጡ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን ወስዶ በአንድ የክፍል ደረጃ ላይ ብቻ በማተኮር የተካሄደ በመሆኑ ሌሎች የክፍል ደረጃዎችን እና መምህራንን የማያጠቃልል በመሆኑ በተፈለገው ደረጃ መረጃ ለማግኘት አስቸጋሪ ሆኖ በመገኘቱ ውስንነት አለው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1. የሰዋስው ምንነት

የሰዋስው ምንነትን አስመልክቶ አንድ ወጥ ብያኔ ለመስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ የቋንቋ ምሁራን በተለያዩ አውዶች የተለያየ ብያኔ ስለሚሰጡ ነው፡፡ ስለሰዋስው ከተሰጡት ብያኔዎች ጥቂቶቹ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

Cook (2001) ስለሰዋስው ምንነት ከመግለጻቸው በፊት ሰዋስው በተለያየ መልክ እየተፈረጀ ብያኔ እንደሚሰጠው ያብራራሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ሰዋስው ጥንታዊ ሰዋሰው ወይም የትምህርት ቤት ሰዋስው በመባል የሚፈረጅና የንግግር ክፍሎችን ለመለየት የሚያስችሉ ህጎችን የያዘ ሆኖ የሚበየን ነው፡፡ ይህ የሰዋስው አይነት ስለንግግር ክፍሎች ማለትም ስም፣ ግስ፣ ቅጽል፣ ወዘተ. አንዱ የቃል ክፍል ከሌላው የሚለይበትን ባህርይ የሚገልፅ የትምህርት አቀራረብ ተደርጎ የሚታይ መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ሌላው ደግሞ አዛዥ ሰዋስው የሚባለው ነው፡፡ይህ የሰዋስው ዘርፍ ‹‹ይህን በል ይህን አትበል›› በሚል የቋንቋው ልማዳዊ ህግጋት መሰረት አድርጎ የተበየነ ነው፡፡ እንዲሁም ሰዋስው የቋንቋ መዋቅርና ስርዓትን የሚመለከት ተደርጎ ብያኔ ይሰጠዋል፡፡ይህም የሚያሳየው ቃላት በስርዓት ተቀናጅተው ዓረፍተነገርን በሚመሰርቱበት ስርዓትና ህግ ላይ ያተኮረ መሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ሰዋስው ድምጾችና ምእላዶች እንዴት ተቀናጅተው ቃላትን እንደሚመሰርቱ ቃላት ደግሞ በስርዓት ተቀናጅተው ሀረግን እንደሚመሰርቱ ሀረጋት ደግሞ ተቀናጅተው ዓረፍተነገር እንዴት እንደሚመሰርቱ መዋቅራቸውን ተንትኖ የሚያሳይ ነው ተብሎ የሚበየን መሆኑን የሚያስገነዝብ ነው፡፡

ምሁሩ አያይዘውም ሰዋስው በተለያየ መልኩ እየተፈረጀ ብያኔ ቢሰጥበትም ብያኔዎቹ ግን ስለሰዋስው ምንነት መነሳት ያለባቸውን ጉዳዮች አጠቃለው ያልያዙ በመሆናቸው ስለሰዋስው ሙሉ ሀሳብን ያላካተተ መሆኑን አስረድተዋል፡፡ በመሆኑም የሰዋስውን ምንነት ለመበየን ከስነልሳን ንድፈሀሳብ አንፃር ሰፋ አድርጎ ማየት እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡ ከዚህ በመነሳት ‹‹ሰዋስው ‹ይህን በል ይህን አትበል› በሚል አዛዥ ተደርጎ ብያኔ መስጠቱ የስነልሳንን ጥናት መሰረት ያላደረገ ልማዳዊ ተቀባይነትን ብቻ የሚከተል መሆኑን ያሳያል፡፡ ሌላው ሰዋስው

የንግግር ክፍሎች መለያ ባህሪን የሚያሳይ የቋንቋ ትምህርት ተደርጎ መበየኑም መዋቅር፣ ፍች እና አጠቃቀም ያላቸውን ሰዋስዋዊ ተግባራት ዋጋ የሚያሳጣ ይሆናል፡፡ እንዲሁም ሰዋስው በቋንቋ መዋቅር ላይ ብቻ ያተኮረ ተደርጎ መበየኑም ለቋንቋው አገልግሎትና አጠቃቀም ቦታ አልሰጠም፡፡›› በማለት ለሰዋስው የተሰጡት ብያኔዎች ድክመት እንዳለባቸው ለማብራራት ሞክረዋል፡፡

ከዚህ ብያኔ መረዳት የሚቻለው ብያኔዎቹ ወጥነት የሌላቸውና የሰዋስውን ውሱን ምንነት ብቻ የሚገልጹ፣በይበልጥም ቅርጽ ላይ ያተኮሩ መሆናቸውን ነው፡፡ አንዳንዶቹ የሰዋስው ምንነትን ከሰዋስው መጽሐፍ ጋር አያይዘው የሚተረጉሙ መሆናቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ በተናጠል የተሰጡትን ብያኔዎች ስናጤናቸው ከስነ ልሳን ንድፈ ሀሳባዊ መሰረቶችጋር ተጣጥመው መሄድ የማችሉና የሰዋስውን ምንነት በጠባብ ጽንሰሀሳብ ለመግለጽ የሞከሩ ናቸው

ሰዋስው ማለት ቃላት እርስ በእርስ በመቀናጀት ዓረፍተ ነገሮችን የሚያዋቅሩበትን ህግና የመዋቅሮቹን ፍች አካቶ የያዘነው፡፡ስለዚህ ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ቅርጽ ወይም መዋቅር ስርዓትና የመዋቅር ትርጉም ምን እንደሆነ ማስገንዘብ የሚያስችል ነው(Littlewood፣ 2012 ፤ Ur ፣1988፤ Harmer ፣1987፣7)፡፡ በተጨማሪምሰዋስው ገና በህጻንነታችን ቋንቋን ለመልመድ ከምንጥርበት እድሜያችን ጀምሮ አብሮን የሚኖር እውቀት እና ረቂቅ ክስተት ነው (Carter ፣ 1990)፡፡

Greenbaum (1988) እና Kachru (2010) ለሰዋስው ፍች ሲሰጡ ‹‹ሰዋስው የስነልሳን ጥናት አንዱ ክፍል ሲሆን የሚያጠናውም የቃል ክፍሎችን፣የድምጽ አፈጣጠር ሁኔታን፣ቃላቱ በዓረፍተነገር ውስጥ ያላቸውን ግንኙነትና አግባብነት ካለው አጠቃቀም አንጻር ሲሆን አንዳንዴም ጥናቱ በስፋት ከጉዳዩ ጋር ግንኙነት ያላቸውን ስነድምጽን፣ የቋንቋዎች ጥናትን፣ የአጻጻፍ ስርዓትን እና ፍችን ያካትታል፡፡›› በማለት ያብራራሉ፡፡ Celce-Murcia (1991 ፣16) ደግሞ ‹‹ቋንቋ ስርዓት ያለው በመሆኑ ይህንን ስርዓት የሚያሳይ እሳቤ ሰዋስው ይባላል፡፡›› ይላሉ፡፡ Richards & Schimdit (2002) እንደሚያስረዱት ሰዋስው ቃላት እየተዋቀሩ ዓረፍተነገር የሚመሰርቱበት ህግና ተግባር የሚያጠና ነው፡፡

ከዚህ በላይ የቀረቡት ብያኔዎች እንደሚያስረዱት ሰዋስው ቃላት በስርዓት ተቀናጅተው ዓረፍተነገሮችን የሚያዋቅሩበትን ህግና ስርዓት ያለውና መዋቅሮቹን ከተግባራቸው ጭምር የሚያጠና መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ሰዋስው የሰው ልጆች በቋንቋ መግባባት ከጀመሩበት

ወቅት ጀምሮ ከሰዎች እድሜ ጋር አብሮ የሚያድግ መሆኑን ያስረዳል። ሌላው የሀገራችን የስነ ልሳን ምሁራን ስለሰዋስው ምንነት የሚከተለውን ብያኔ ሰንዝረዋል።

ባዬ (2000፣xxi) ‹‹ሰዋስው የአንድን ቋንቋ ስርዓት ከድምጽ አሰካኩ እስከ ዓረፍተነገር አመሰራረቱ ድረስ የሚያሳይ ሳይንስ ነው። ዋና አላማው በቀጥታ አራቱን የቋንቋ ክሂሎች ማለትም የማንበብ፣የመጻፍ፣የማዳመጥና የመናገር ችሎታን ማዳበር ሳይሆን በሚነበበውም ሆነ በሚነገረው ቃል፣ሐረግ፣ዓረፍተነገርና ድርሰት ጀርባ የሚገኘውን ረቂቅ ስርዓት ደረጃ በደረጃ ለተማሪው ማሳየት ነው።›› ይላሉ።አክለውም ባዬ(2010 ፣ 5-6) ስለሰዋስው ምንነት እንደሚከተለው ያብራራሉ።

> *ሰዋስው የሚለው ቃል በግእዝ መሰላል ማለት ነው። መሰላል ከአንድ አነስተኛ ደረጃ ወደ ከፍተኛ ደረጃ ቀስ በቀስ ለመውጣትና ለመውረድ የሚያስችል መሳሪያ ነው። የአማርኛ ሰዋስው ሲባል የአማርኛን ድምጾች አይነት፣አፈጣጠርና አቀነጃጀት፣የአማርኛን ቃላት አይነት፣አመሰራረትና አቀነጃጀት፣ እንዲሁም የሀረጋቱን አይነትና የአወቃቀር ስርዓት ደረጃ በደረጃ የሚያሳይ የእውቀት ዘርፍ ማለት ነው። ድምጽ ከድምጽ ጋር ተቀናጅቶ ቃልን፣ ቃል ከቃል ጋር ተጋጥሞ ሀረግን፣ እንዲሁም ሀረግ ከሀረግ ጋር ተዋቅሮ ዓረፍተነገርን ደረጃ በደረጃ የሚፈጥርበትን ስርዓት የሚመለከት ጥበብ ነው። መሰላልነቱ ከድምጽ ጀምሮ እስከ ዓረፍተነገር ድረስ ላለው አጠቃላይ የቋንቋ ስርዓት ስለሆነ ያሁኑ የሰዋስው ግንዛቤ ከበፊቱ ሰፊ ነው።*

ስለሰዋስው ምንነት ምሁራኑ ያስቀመጧቸውን ብያኔዎችቀደም ሲል ከተገለጹት ብያኔዎች ጋር ስናነጻጽራቸው ሰፊ ጽንሰሀሳብን የያዙ እና ጠለቅ ያለ ግንዛቤን የሚያስጨብጡ ናቸው። በመሆኑም ሰዋስው ማለት በአንድ ቋንቋ ውስጥ ካለ ቅንጣት ጀምሮ እስከ ትልቁ የቋንቋ መዋቅር ድረስ ያሉትን የድምጽ፣የምዕላድ፣ የቃላት፣ የአገባብ፣ የፍች እና የአጠቃቀም ስርዓትን አጠቃሎ የሚይዝ መሆኑን ያስገነዝባል።

ከላይ የተጠቀሱትን ብያኔዎች መሰረት በማድረግ ሰዋስው የቋንቋ ስርዓትና እውቀት በማለት በሁለት አሻሚ መንገዶች መክፈል ይቻላል። አሻሚነቱን በተመለከተ ጌታሁን(2011፣xi) እንደሚከተለው ይገልጻሉ።

የቋንቋ ጥናት በአጠቃቀም፣ በለውጥ፣ በስርዓት፣ወዘተ. ላይ ሊያተኩር ይችላል። ሰዋስው ከቋንቋ ጥናቶች ውስጥ ስርዓትን የሚመለከተው ክፍል ነው።በአሁኑ ወቅት ሰዋስው የሚለው

ቃል ሁለት አሻሚ ፍችዎችን ይዞ ይገኛል፡፡አንደኛው ፍች የሰው ልጅ የሚጠቀምበትን ቋንቋ ‹እውቀት› የሚጠቁመውና በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለው ችሎታ ነው፡፡በዚህ ንድፈ ሀሳባዊ እይታ የሰው ልጅ ቋንቋውን ሊያውቅና ሊጠቀምበት የሚችለው ይህ ችሎታ ስላለው ነው፡፡ከዚህ አንጻር ሲታይ ሰዋስው አእምሯዊ እሳቤ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ተመራማሪዎች ስለ ቋንቋ ስርዓትና መዋቅር የሚያደርጉትን ከስነ ድምጽ እስከስነሀረግ ያለውን ገለጻ የሚጠቁመው ነው፡፡ይህ ፍች ከመጀመሪያው ፍች ጠባብ ነው፡፡

ምሁሩ ከሰጡት ብያኔ መገንዘብ እንደሚቻለው ሰዋስው የሚለው ቃል ሁለት አሻሚ ፍችዎች የያዘ መሆኑ ነው፡፡ ይህም የመጀመሪያው የሰው ልጅ ስለሚግባባበት ቋንቋ እውቀት መኖሩን ነው፡፡ ይህ የቋንቋ እውቀትም በተፈጥሮ ያገኘው ወይም ሲወለድ ይዞት የሚመጣው (የሚወለደው) ቋንቋን ለመልመድ የሚረዳው ችሎታ መሆኑን የሚያመለክትነው፡፡ ይህም ሰዋሰው አእምሯዊ እሳቤ መሆኑን ይጠቁማሉ፡፡ ሁለተኛው ደግሞ የሰው ልጅ ስለሚጠቀምበት የቋንቋ ስርዓት ማለትም የድምፆች፣ የምእላዶች፣ የቃላት፣ የሀረጋት እና የዓረፍተነገሮች አወቃቀርና አደረጃጀት የሚመለከት ነው፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በቀረቡት ብያኔዎች መሰረት ሰዋስው በአንድ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙ ተዋቃሪዎች የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው መሰረት ማቀናጀትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ ምክንያቱም ሀሳብን በተሟላ ሁኔታ በቋንቋ መግባባት የሚቻለው የአንድ ቋንቋ ተዋቃሪዎች በዘፈቀደ በመጠቀም ሳይሆን ስርዓት ባለው መንገድ በማደራጀትና ትርጉም የሚሰጥ መዋቅር በመፍጠር ነው፡፡

## 2.2 . በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊነት

የሰዋስው ትምህርት አላማ ተማሪዎች ከሚኖራቸው የቋንቋ ክሂል ጎንለ ጎን የቋንቋውን ስርዓት እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው፡፡ የሰዋስው ትምህርት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተጣምሮ ቢሰጥ በመማር ማስተማር ሂደት ላይ የበለጠ ውጤት ለማግኘት ይጠቅማል፡፡ በመሆኑም በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የቋንቋ ክሂሎች በሚገባ ተግባራዊ ይደረጉ ዘንድ የቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓትን ማወቅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ የሰዋስዋዊ እውቀት ደግሞ የሰዋስው ትምህርት አስፈላጊ እንደሆነ ጌታሁን (2011 ፣ xi-xii) እንዲህ ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

*በአንድ ቋንቋ አፍፌት የሆነ ሰው ትክክለኛ የሆነ ዓረፍተነገርን ትክክል ካልሆነው ለይቶ ሊነግረን ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ትክክለኛ ዓረፍተነገር ነው ያለውን ትክክል ለመሆኑም ሆነ፣ ስህተት ነው ያለውን ስህተት የሆነበትን ምክንያት ሊናገር አይችልም፡፡ ምክንያቱም ይህን ሊናገር የሚችለው ቋንቋውን አቀላጥፎ መናገር የሚችለው ሰው ሳይሆን፣ የቋንቋን ስርዓት የሚያውቀው ባለሙያ ብቻ ስለሆነ ነው፡፡ ለዚህም ነው፤ቋንቋን መናገር መቻልና ስለቋንቋ ማወቅ የተለያዩ ናቸው የሚባለው፡፡ስለቋንቋው ለማወቅ የሚያበቃው ደግሞ የስርዓት ትምህርት ነው፡፡ ለዚህ መሰረታዊ ጉዳይ ሲባል ነው፤ የቋንቋ ትምህርት የክሀሎትም የስርዓትም ችሎታን የሚያዳብር መሆን አለበት የሚባለው፡፡ ይህን ግብ ለማሳካትም የቋንቋ መምህራን ለክህሎቱ ብቻ ሳይሆን ለዘመናዊ የስርዓት ትምህርቱም ራሳቸውን ማስተዋወቅ አለባቸው፡፡ ክህሎትንና ስርዓትን አቀናጅቶ ያስተማረ መምህር ቋንቋውን በተሟላ ሁኔታ አስተምሯል፤ ተማሪውም የተሟላ እውቀት አግኝቷል ማለት ይቻላል፡፡*

የምሁሩ ገለጻ የሚያስረዳው ቋንቋን የማስተማር አላማ መመስረት ያለበት በክህሎት ትምህርት ላይ ብቻ ሳይሆን በቋንቋው ስርዓትና ህግም ላይ ጭምር መሆን እንዳለበትነው፡፡በተጨማሪም የቋንቋውን አጠቃቀም እውቀት ኖሮት ትምህርት ቤት ገብቶ የቋንቋውን ስርዓት የተማረ ሰው ቋንቋውን በልምድ ከሚያውቀው ሌላ ሰው የተሻለ እውቀት ይኖረዋል፡፡ በሌላ በኩል አንድ ሰው ምንም እንኳ ሰዋስው ሳይማር በቋንቋው ለመጠቀም የሚያስችል ችሎታ ቢኖረውም ለምን እንደዛ እንደተጠቀመ ስርዓቱን የማስረዳት ችሎታ ግን የለውም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት በሚገባ ለማወቅ ሰዋሰውን መማር አስፈላጊ እንደሆነ ከምሁራኑ ብያኔ መረዳት ይቻላል፡፡

የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በርካታ አመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም ትኩረቱ ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ የተለያየ ነበር፡፡ ምክንያቱም በሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ በየዘመኑ የተነሱ ፍልስፍናዎችና ከእነሱ የመነጨት የማስተማሪያዘዴዎችናቸው (Richards & Rodgers 1995 ፣3)፡፡

እ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ አካባቢ የሁለተኛ ቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ግብ ‹ተግባቦት› መሆን አለበት የሚል አስተሳሰብ በስልሳን ባለሙያዎች መራመድ በመጀመሩ ለሰዋስው ትምህርት የሚሰጠው ትኩረት ነቀፌታ እየገጠመው መጣ (Richards & Rodgers 1995፣64)፡፡እንደ ተግባቦታዊ የቋንቋ ማስተማር ዘዴ አመለካከት የስነ ልሳን እውቀት የሚገኘው ሰዋስውን በማስተማር ሳይሆን በተግባቦት ነው (Adugna ፣ 2008)፡፡

ከዚህም በተጨማሪ Krashen (1995) ‹‹ተማሪዎች የሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ በተገቢው ሁኔታ የሚያከናውኑት በሰዋስው ላይ ትኩረት በማድረግ ሳይሆን በትርጉም ወይም በተግባቦት ላይ ትኩረት ሲያደርጉ ነው፡፡›› በማለት ያብራራሉ፡፡

እንደ Mirsolow (2004) አባባል ‹‹ያለ ሰዋስው በተግባቦታዊ አቀራረብ ብቻ ተማሪዎች መሰረታዊ የሰዋስው ህግጋትን መለየት ካለመቻላቸውም በተጨማሪ የሰዋስው እውቀታቸው ከፍተኛ ደረጃ ላይ ሊደርስ አይችልም፡፡ይህንን ሊያደርጉ የሚችሉት በተግባቦት ውስጥ የሰዋስው ትምህርትን ሲማሩ ነው፡፡›› ይላሉ፡፡አክለውም "የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ የሚካተተው የተማሪዎችን የቋንቋ ለመዳስ ለሚያፋጥንና ከፍተኛ ውጤት እንዲያመጡ ስለሚያግዝ ነው፡፡"በማለት ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም Widodo (2006) እና Taylor (2008) እንደሚሉት "በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሰዋስው ትምህርትን ለተማሪዎች ማስተማር ተማሪዎቹ ቋንቋውን በጥሩና በተለየ መንገድ እንዲጠቀሙ ከማድረጉም ባሻገር የቋንቋ ችሎታቸውንም ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያደርሳቸዋል፡፡ የሰዋስው ትምህርት የሚያስፈልገው የተማሪዎቹን የቋንቋ ለመዳና አጠቃቀም ስለሚያፋጥን ብቻ አይደለም፡፡ እንደውም የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋ ክሂሎችም መዳበር በር ከፋች ነው፡፡ በንግግርና በማዳመጥ ወቅት የሰዋስው ትምህርት እውቀት መኖሩ የንግግሩን ሀሳብ በሚገባ ለመረዳትና ተቀባይነት ያላቸውን የንግግር ቃላት ተጠቅሞ ለመናገር ይረዳል፡፡በንባብ ወቅትም ተማሪዎች በሚያነቡት ምንባብ ውስጥ ያሉትን ዓረፍተ ነገሮች የእርስ በእርስ ግንኙነት በማጤን የአንቀጹንና የምንባቡን ሀሳብ በቀላሉ እንዲረዱ ይጠቅማል፡፡ በተጨማሪም በጽህፈት ክሂል ጊዜም የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች ሀሳባቸውን በትክክልና ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲያስቀምጡ በማድረግ ውጤታማ የሆነ የጽሕፈት ተግባቦት እንዲያከናውኑ ያደርጋል፡፡ "በማለት በሰፊው ያብራራሉ፡፡

ከዚህ የምንረዳው የሰዋስው ትምህርትን በተናጠል ከማስተማር ይልቅ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አጣምሮ ቢሰጥ ተማሪዎችን በተግባቦት የዳበረ እውቀት እንዲያካብቱ ወይም እንዲያዳብሩ የሚያደርጋቸው መሆኑን ነው፡፡

በሌላበኩል Ur (1988፣4) እና Littlewood (2012) የሰዋስው ትምህርትን ጠቀሜታ ሲገልጹ "ለአንድ የቋንቋ ተማሪ ሰዋስውን መማር በጣም ጠቃሚ ነው፡፡ ምክንያቱም ሰዋስውን መማር የሚማረውን ቋንቋ በሚገባ ለመካን የሚረዳው ነውና፡፡ በተጨማሪም የሰዋስው ስርዓቶችን

ወይም ህግጋት ማወቅ ያለጥርጥር የታላሚውን ቋንቋ ለማወቅ ይጠቅማል። እንዲሁም ተማሪዎች ቃላት እንዴት አንድ ላይ እንደሚጣመሩና እንደሚደረደሩ ህጉንና ስርዓቱን ካላወቁ ቃላትን እንኳ ሊጠቀሙ አይችሉም። በተጨማሪም Harmer (1987) "ቋንቋን ለመማር ቀጥተኛም ሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ የቋንቋ ህግጋት እውቀት ማግኘት ጠቃሚ መሆኑ የማያከራክር ጉዳይ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች የቃላትን አወቃቀር ስርዓት ሳይገነዘቡ በቃላት መገልገል (መግባባት) አይችሉም።"ይላሉ።

ሌላው Ellis(1997፣92) የሰዋስው እውቀት አስፈላጊነትን ሲገልጹ ‹‹ተማሪዎችበለጋእድሜያቸው በስፋት ለሰዋስው ትምህርት የማይጋለጡ ከሆነ በታላሚው ቋንቋ አንደበተርቱዕ የመሆን አቅም ስለማይኖራቸው ተጠቃሚ ይሆኑ ዘንድ ቋንቋውን ተግባቦታዊ በሆነ መንገድ መማር አለባቸው፡ ፡›› ይላሉ።

በተጨማሪም የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካቶ መቅረብ እንዳለበት መሰሉ(1994፣58) በሚከተለው ሁኔታ ያብራራሉ።

> *ቋንቋ በህግ የሚገዛ ነው። ህጉ ደግሞ ሰዋስው ነው።ስለዚህ ቋንቋን ከሰዋስው ለይቶ ማየት አይቻልም። ምክንያቱም ድምጾችና ምእላዶች ስርዓት ይዘው ካልተዋቀሩ በስተቀር ትርጉም አዘል ቃላትን አይመሰርቱም።ቃላትም በስርዓት ካልተዋቀሩ በተወሰነ አውድ ውስጥ የሚኖራቸውን ፍች ያጣሉ።ስለዚህ ትክክለኛውን የአወቃቀር ስርዓት ተጠቅሞ ያለ እንቅፋት በቋንቋው ለመግባባት ህጉን ማወቅ ያስፈልጋል።*

ከዚህ ብያኔ መረዳት የሚቻለው ሰዋስው የቋንቋ ስርዓት ወይም ህግ ነው።ቋንቋ ደግሞ በህግ የሚገዛ ነው።ስለዚህ የቋንቋው ስርዓት በሚፈቅደው እና በቋንቋው ተናጋሪ ማህበረሰብ ዘንድ ተቀባይነት ባለው መልኩ ለመግባባት የሚያስችል ችሎታን ተማሪዎች እንዲያዳብሩ (እንዲያጎለብቱ) ከተፈለገ በቋንቋ ትምህርቱ ውስጥ የሰዋስው ትምህርትን ማካተት አስፈላጊ ነው።ጌታሁን (1997) እና Wilkns (1976) የሰዋስውን ትምህርት አስፈላጊነት እንደሚከተለው ያስረዳሉ።

ተማሪዎች የቋንቋ ክሂሎችን መተግበር የሚያስችላቸውና የተፈለገው የትምህርት ግብ ላይ መድረስ የሚችሉት የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርአት ማወቅ ሲችሉ ነው፡፡ ሰዋስው በቋንቋ ክሂሎች ውስጥ የሚከሰት ማዕከላዊ ጉዳይ እስከሆነ ድረስ ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው የትምህርት ይዘት መሆኑን እና ክሂሎችን ከሰዋስው ነጥሎ ማስተማር ዝቅተኛ የቋንቋ እውቀትን ቢያስገኝ እንጂ የተሟላ የቋንቋ እውቀትን ማጎናጸፍ አይችልም፡፡

በሌላ በኩል Ur (1988) ‹‹የተግባቦት ብቃት ያለሰዋስው እውቀት እውን ሊሆን ስለማይችል ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚተገብሯቸው ክንውኖች በሙሉ ከሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ጋር ተሳስረው ቢቀርቡ የታቀደውን የትምህርት አላማ ከግብ ለማድረስ ጠቀሜታ አለው፡፡›› በማለት የሰዋስውን ትምህርት አስፈላጊነት ያስረዳሉ፡፡

Michal (2007) ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የንግግርም ሆነ የጽሁፈት ክሂል ከሰዋስው እውቀት ጋር በማጣመር የቋንቋ ደረጃቸውን ከግምት ያስገባ የትምህርት አቀራረብ የሚያስፈልግ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡ አክለውም የቋንቋ ትምህርት ከማህበራዊ አውድ ጋር ተቀናጅቶ መቅረብ እንዳለበት እና ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ተገንዝበው በቋንቋ የመጠቀም ብቃት እንዲኖራቸው በሚያስችል ተግባራዊ ክንውን ውስጥ ማለፍ እንደሚገባቸው ያስረዳሉ፡፡

የምሁራኑ ገለጻ የሚያስረዳው ተማሪዎች የሚጠቀሟቸው ዓረፍተነገሮች ከተለያዩ ሰዋስዋዊ አሀዶች(ቅንጣቶች) የተገነቡ በመሆናቸው ቋንቋውን ለአገልግሎት ማዋል የሚችሉትን የአሀዶቹን ሰዋስዋዊ ባህርይተረድተው የቋንቋውን ስርዓት (ህግ) የጠበቁ ዓረፍተነገሮችን በመመስረት ሀሳባቸውን መግለጽ እንደሚችሉ ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ቋንቋውን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የተማሪዎችን የንግግርም ሆነ የጽሑፍ ክሂሎች ከሰዋስው እውቀት ጋር በማጣመር በክፍል ውስጥ ማቅረብ ወይም ማስተማር ያስፈልጋል፡፡

በተጨማሪም Bygate, etal. (1994) እንደሚገልጹት በአንድ ቋንቋ መዋቅር ውስጥ ያሉ ቃላት፣ሀረጋት እና ዓረፍተነገሮች በአገባብ ወይም በምእላዶቹ ተግባር ምክንያት ፍችን ወይም የቋንቋ አጠቃቀምን ሊወስኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ የአንድን ቋንቋ ተግባቦታዊ ብቃት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት ከማወቅ ጋር የሚተሳሰር በመሆኑ የሰዋስው ትምህርት መሰጠቱ አስፈላጊ ነው በማለት ያብራራሉ፡፡

ከላይ የቀረቡት የምሁራን ሀሳቦች የሚያስረዱት የሰዋስው ትምህርት ሲሰጥ በህግጋት ላይ ብቻ ትኩረት ተሰጥቶ ማስተማር አስፈላጊ አይደለም።መምህራን በህግጋቱ ላይ ብቻ ትኩረት ሰጥተው የሚያስተምሩ ከሆነ የሰዋስው ትምህርት ጠቀሜታዎችን ማግኘት አስቸጋሪ ይሆናል። ይሁንና የቋንቋ ትምህርትን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚቻለው ህግጋቱን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ተግባቦታዊ በሆነ መልኩ ማስተማር ነው። በተጨማሪም የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋ ተማሪዎች ጠቃሚ ጉዳይ እንደሆነና ስርዓትና ህጉን አውቀው ቃላትን በተገቢው መንገድ አቀናጅተው በመጠቀም ተግባቦትን መፍጠር ይችላሉ፤ህጉን ካላወቁ ግን በቃላት መጠቀም አይችሉም።

በአጠቃላይ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ እና ለተማሪዎች ከቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ ነው። ምክንያቱም በቋንቋ ትምህርት ወቅት ሰዋስውን ማስተማር የቋንቋ ተማሪዎች የቀረበላቸውን የሰዋስው መዋቅር በአግባቡ እንዲማሩ እና እንዲገለገሉበት ስለሚያስችላቸው ነው። ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለመግለጽ የሰዋስው ትምህርት በሶስት መልኩ ለማየት ተችሏል።

ይህም የመጀመሪያው የቋንቋ ትምህርት ሰዋስው ላይ ብቻ ማተኮር አለበት የሚል ነው። ይህ በቋንቋ ህግ ላይ ብቻ ያተኮረ አቀራረብና ከቋንቋ ትምህርት ጽንሰሀሳብ አንጻር ሲታይ ለፍች እና ለአጠቃቀም ትኩረት ያልሰጠ ነው። ይህ ደግሞ ዝቅተኛ የቋንቋ እውቀትን የሚያስጨብጥ በመሆኑ ተማሪዎቹን ብቁ አያደርጋቸውም፤የተሟላ የቋንቋ እውቀትን እንዲያዳብሩ አያስችላቸውም፤ጥሩ የተግባቦት ብቃትም እንዲኖራቸው አያደርግም። ይህም በመሆኑ ድክመት ይታይበታል። ሁለተኛው ደግሞ የቋንቋ ትምህርት ተግባቦት ላይ እንጂ ህግ ላይ ማተኮር የለበትም የሚል ነው። ይህ ደግሞ ጭራሹኑ ለሰዋስው ቦታ አልሰጠም። እንደውም በተቃራኒው የሰዋስው ትምህርት በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ መሆኑን ከላይ የተለያዩ ምሁራን በሰፊው አብራርተውታል። ይሁን እንጂ ይህ ሀሳብ ሰዋስው ለቋንቋ ትምህርት ያለውን ሚና ዝቅ አድርጎታል። በሌላ በኩል ሶስተኛዎቹ ወገኖች የሁለቱንም ተቃራኒ ሀሳብ በማስታረቅ የቀረቡ ናቸው። ይህ በመጨረሻ የምናየው የቋንቋ ትምህርት የሰዋስው ትምህርት እና ተግባቦትን አጣምሮ የያዘ በመሆኑ ተቀባይነት ያለው ሀሳብ ነው። ይህ ሃሳብ ተማሪዎች በሁለቱም ማለትም በሰዋስው እና በተግባቦት የዳበረ እውቀት እንዲጎናጸፉ የሚያደርግ መሆኑን ከተለያዩ የምሁራን ገለጻ መገንዘብ ተችሏል።

ሰዋስው ሰፊ ጽንሰሀሳብን የያዘ እና በተለያዩ ንዑሳን ክፍሎች የተከፋፈለ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል፡፡እነዚህ የሰዋስው ክፍሎች እንደ ትኩረት አቅጣጫቸው የራሳቸውን አላማ የያዙ በመሆናቸው ከዚህ ጥናት አላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው የሰዋስው ክፍል የትኛው እንደሆነ መለየት ያስፈልጋል፡፡የዚህ ጥናት ታላሚ በሆኑት በ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብናአተገባበር ምን እንደሚመስል ለመገምገም እንዲሁም የሰዋስው ትምህርት ከሚከተላቸው መርሆች ጋር መጣጣም አለመጣጣሙን ለመመርመር የሚያስችሉ የመነሻ ሀሳቦችን ለማግኘት ያስችላል፡፡ በመሆኑም የተለያዩ ምሁራን ሰዋስውን በተለያየ መልኩ ይከፍሏቸዋል፡፡ከነዚህም ውስጥ Chalker(1994፣33) Greenbaum (1988) ን ጠቅሰው የሰዋስው አይነቶችን በአራት (4) ዋና ዋና ክፍሎች ከፋፍለው ማስቀመጣቸውን ጠቅሰዋል፡፡ እነሱም፡- ማጣቀሻ፣ ሥነትምህርታዊ፣ እራስህን አስተምር እና ንድፈሀሳባዊ ሰዋስው ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ Crystal (1987) ሰዋስውን በስድስት(6) ዋና ዋና ክፍሎች ከፋፍለው እንዳስቀመጡት Chalker (1994) ይገልጻሉ፡፡ እነሱም ፡-

| | |
|---|---|
| - ገላጭ | - ማጣቀሻ |
| -ሥነትምህርታዊ | - ንድፈሀሳባዊ እና |
| -አዛዥ | -ጥንታዊ ሰዋስው ናቸው፡፡ |

ከላይ ምሁራኑ በተለያየ መንገድ የከፋፈሏቸው የሰዋስው አይነቶች የራሳቸው ንድፈሀሳቦች፣ አላማ እና የትኩረት አቅጣጫ ያላቸው መሆናቸውን ለማየት ከተቻለ ከዚህ ቀጥሎ ይህ ጥናት ይዞ ከተነሳው አላማ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባለው የሰዋስው አይነት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡፡ ይህም በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ላይ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት በማሳየት ተግባቦትን እንዴት ማከናወን እንደሚቻል ስለሚያሳውቀው ሥነትምህርታዊ ሰዋስው ብቻ ትኩረት በመስጠት ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

## 2.3. የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ምንነት

ስለሥነትምህርታዊ ሰዋስው እሳቤ መፈጠር ምክንያት የሆነው ጉዳይ የሚደርስባቸው ግኝቶች በቋንቋ ትምህርት ውስጥ በቀጥታ ሊቀርቡ አይገባም የሚለው የቋንቋ ምሁራን አስተያየት እንደሆነ Stern (1991፣175)ይገልጻሉ፡፡እንደሙሁራኑ አገላለጽ በአንድ ቋንቋ ላይ በተደረገ

ሳይንሳዊ ምርምር የተገኙ ውጤቶችን በሙሉ በትምህርትነት በክፍል ውስጥ ማቅረብ ተገቢ አይደለም፡፡ይልቁንም እንደ የቋንቋ ትምህርቱ አላማ አጣጥሞ ማቅረብ አስፈላጊ ነው፡፡በመሆኑም በተለያዩ የሰዋስው ጥናት ዘርፎች የተገኙ ውጤቶችን (ግኝቶችን) በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ስነልቦናዊ እና ማህበረሰባዊ ሁኔታዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት ሰዋስዋዊ ይዘቶችን አጣጥሞ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡የዚህ አይነት የሰዋስው የጥናት ዘርፍም *ሥነትምህርታዊ* ሰዋስው በመባል ይታወቃል፡፡

ከላይ የሰዋስው አይነቶችን በተመለከተ እያንዳንዱ የሰዋስው ጥናት ዘርፍ የራሱ የሆኑ የጥናትአቅጣጫዎች እና አላማዎች አሉት፡፡ለምሳሌ፡-የተወሰኑትን ብንመለከት አዛዥ ሰዋስው ትክክለኛ የሆኑ እና ያልሆኑ የቋንቋ አጠቃቀሞችን ለይቶ ለማስቀመጥ ጥረት የሚያደርግ ነው፡፡ ንድፈሀሳባዊ ሰዋስው ደግሞ ስለቋንቋ አፈጣጠር፣ስለቋንቋ ባህርይ እንዲሁም ስርዓት፣ ወዘተ. ትውረታዊ እሳቤዎችን በማቅረብ የሚዘረዝር ነው፡፡እንዲሁም ገላጭ ሰዋስው አንድን ቋንቋ እየነጣጠለ ገለጻ ያደርጋል፡፡ጥንታዊ ሰዋስውም ይህን አድርግ፤ ይህን አታድርግ፤ በማለት በቃል ከሚጠና ህግጋት ጋር ዝምድና ያለው ነው፡፡ ይሁንና ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን የሰዋስው ዘርፎች አንድ በአንድ ማየቱ አዳጋች በመሆኑ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆነውን በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ላይ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት በማሳየት ተግባቦትን እንዴት ማከናወን እንደሚቻል የሚያሳውቀውን *ሥነትምህርታዊ* ሰዋስው ብቻ ለይቶ መዳሰስ አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ምክንያቱም ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው *ሥነትምህርታዊ* ሲሆን ይህም በመደበኛው የቋንቋ ትምህርት ውስጥ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ስላለው ነው፡፡

*ሥነትምህርታዊ* ሰዋስው በትምህርት ሂደት ውስጥ የታላሚውን ቋንቋ ውስብስብ ህግጋት በማቅረብ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ለመዳ ወቅት ውጤታማ ይሆን ዘንድ ታስቦ የተዘጋጀ እና ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎችም ሆነ ለመምህሩን የሚያገለግል የሰዋስው አይነት ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ የሰዋስው አይነት አዛዥ፣ገላጭ፣ማጣቀሻ ወይም መማሪያ የሰዋስው ዘርፎችን የያዘ ነው፡፡

*ሥነትምህርታዊ* ሰዋስው በተግባቦት ወቅት ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ቋንቋን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል እና የቋንቋውን የሰዋስው ትምህርት አላማ ማሳካትን የሚመለከት ጉዳይ ነው፡፡ *ሥነትምህርታዊ* ሰዋስው ተማሪዎች ቋንቋን በምን አይነት ሁኔታ መማር እንዳለባቸው ለመገመት እንዲሁም በሚሰጡት ገለጻ ላይ ስነልሳናዊ አጠቃቀማቸውን ለመከታተል እና በተግባቦት ወቅት ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ቋንቋ እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ለመጠቆም

ያግዛል፡፡ ስለዚህ የሥነትምህርታዊ ሰዋስው ዋና አላማ ተማሪዎች ሰዋስዋዊ ስርዓቱን እና አጠቃቀሙን ጠብቀው እንዲናገሩ እና እንዲጽፉ ማድረግ ነው(Chalker 1994፣34፤ Littlewood ፣1984)፡፡

ከላይ ከቀረቡት ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው ሥነትምህርታዊ ሰዋስው የቋንቋን ስርዓት በትክክል መጠቀም የሚችሉበትን እና ተግባቦት የሚፈጽሙበትን ሁኔታ የሚመለከት መሆኑን ነው፡፡ይህ የሰዋስው ዘርፍ አብዛኛውን ጊዜ ሁለተኛ ቋንቋን ለማስተማር የሚጠቅም ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የአንድ ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቀ ቋንቋ እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ የሚረዱበትን መንገድ ይጠቁማል፡፡ በተጨማሪም ይህ የሰዋስው ዘርፍ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት የሚማሩበትን እድል በመፍጠር ትክክለኛነት ያለው ተግባቦት የሚያደርጉበትን መንገድ ያሳያል፡፡ስለዚህ ሥነትምህርታዊ ሰዋስው በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋ ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን የቋንቋ ችሎታን ከማዳበር እና እውቀትን ከማስጨበጥ አኳያ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡

ሥነትምህርታዊ ሰዋስው የተለያዩ የሰዋስው ዘርፎችን እና እሳቤዎችን የያዘ ጠለቅ ያለ ባህርይ ያለው እና በቋንቋ ትምህርት ውስጥ የቋንቋውን መዋቅር ከቋንቋ አገልግሎት ጋር በቅንጅት በማቅረብ የቋንቋ ትምህርቱን ውጤታማ ከማድረግ አኳያ ትልቅ ሚና አለው፡፡ ይሁን እንጂ የሰዋስው ትምህርት ውጤታማ ሊሆን የሚችለው የተለያዩ የአቀራረብ ስልቶችን፣ ዘዴዎችን እንዲሁም መርሆችን ተከትሎ የትምህርት ይዘቱን ማቅረብ ሲቻል ነው፡፡በሌላ በኩል Greenbaum (1988) ስለ ሥነትምህርታዊ ሰዋስው ብያኔ ሲሰጡ "ሥነትምህርታዊ ሰዋስው ማለት ስለቋንቋ ሳይሆን ቋንቋን ለማስተማር ተብሎ የሚዘጋጅ የሰዋስው መጽሐፍ ሆኖ ተማሪዎች ምን መናገር እና መጻፍ እንደሚገባቸው የሚያሳይ የአዛዥ ሰዋስው ባህርይ ያለው ነው፡፡"በማለት ያስረዳሉ፡፡ከዚህ ሀሳብ ጋር አያይዘው Nordquist (2006)ሥነትምህርታዊ ሰዋስው "ይህን በል ይህን አትበል" ከሚለው አዛዥ ሰዋስው እና የቋንቋውን መዋቅራዊ ስርዓት ከሚተነትነው ከገላጭ የሰዋስው አይነት ጋር የተገናኘ ነው፡፡ከዚህም የተነሳ ሥነትምህርታዊ ሰዋስው የገላጭ እና የአዛዥ ሰዋስው ባህርይ ያለው እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ጠቅለል ባለ መልኩ ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ሰፋ ያለ ጽንሰሀሳብን የያዘ እንደሆነ ከዚህ በታች የቀረቡት ሀሳቦች መገለጫዎቹ እንደሆኑBygate,etal.(1994) Greenbaum (1988)ን ዋቢ በማድረግ ያስረዳሉ፡፡

- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች ተግባራዊ ልምምዶችን በማድረግ የቋንቋውን ስርዓት በአገልግሎት ላይ እንዲያውሉ የሚያደርግ ነው፡፡
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የሁለተኛ ቋንቋንም ሆነ የአፍ መፍቻ ቋንቋን ሰዋስዋዊ ህግጋት ግንዛቤ ለማስጨበጥ የሚያስችል መሆኑ ነው፡
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ሰፊ የቋንቋ እውቀትን የያዘና ዘመናዊነትን የተላበሰ የትምህርት አቀራረብ ያለው ነው፡፡
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የስነ ልቦናዊ ስነልሳን መሰረትነት ያለው እና የተማሪውን ሁኔታ ከግምት ያስገባ አቀራረብን የሚከተል ነው፡፡
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ገላጭ እና አዛዥ የሰዋስው ትምህርትን አጣምሮ ማቅረብ የሚችል መሆኑ ነው፡፡
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ደረጃ በደረጃ የሚያቀርብ ነው
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ትኩረት ሰጥተው እንዲማሩ ያደርጋል፡፡
- ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ለመምህሩም ሆነ ለተማሪዎች እውቀታቸውን ለማዳበር ትልቅ ጥቅም የሚሰጥ መሆኑ ነው፡፡

በመጨረሻም Corder(1975)፣ Rieger(2009 )እና Jean& Simard (2011) ሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው የምንለው መምህሩ ሰዋስውን እንዴት ባለ መንገድ ማስተማር እንደሚገባው እገዛ የሚያደርግለት ነው በማለት ብያኔ ይሰጣሉ፡፡

ከዚህ በላይ ከቀረቡት ብያኔዎች መረዳት እንደሚቻለው ሥነትምህርታዊ ሰዋስው የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ንድፈ ሀሳቦችን የያዘና እንዲሁም ገላጭና አዛዥ የሰዋስው ትምህርትን አጣምሮ በማቅረብ ተመጣጣኝ እና ምቹ የመማር ማስተማር ሂደትን በመፍጠር ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እና የታቀደውን አላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችል የሰዋስው ዘርፍ መሆኑን ነው፡፡ በተጨማሪም ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ስርዓት ተገንዝበው ቋንቋውን ለተግባቦት የሚያውሉበትን መንገድ የሚያመቻች ነው፡፡ ከዚህም ባሻገር የሰዋስው ትምህርት የቋንቋን መዋቅራዊ ስርዓት ከአጠቃቀም፣ ከፍች እና ከአውድ ጋር አስተሳስሮ (አጣምሮ) መቅረብ አለበት የሚለውን ዘመናዊ የቋንቋ ትምህርት እሳቤ መሰረት ያደረገ ነው፡፡ በሌላ በኩል አፍፊት የሆኑ ተማሪዎችም ስለቋንቋቸው ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያግዝ መሆኑን ያስረዳል፡፡

## 2.4. የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች

መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት የሰዋስው ትምህርቱን መዋቅር እና በውስጡ ስለሚያካትታቸው ይዘቶች ሊያውቁ ይገባል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ መዋቅሮች ከተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የሚመሳሰሉ እና በቀላሉ ሊታወቁ የሚችሉ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ሙሉ በሙሉ የተለያዩ እና ተማሪዎች ወዲያው ሊገነዘቧቸው የማይችሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ መምህራን የሰዋስው ትምህርትን በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው አስቀድመው የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በቂ ጊዜ ወስደው ሊዘጋጁበት ይገባል (Ur 1988፣5)፡፡

በተጨማሪም Nunan (1991) እንደሚገልጹት ሥነትምህርታዊ ሰዋስው ተማሪዎች ዘመናዊ እና ተቀባይነት ባላቸው የሰዋስው ትንታኔዎች መነሻነት ስለታላሚው ቋንቋ ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲኖራቸው ለማድረግ የሰዋስው ይዘቶችን በአውድ አስደግፎ በማቅረብ ተማሪዎች ተጨባጭ የሆነ ትግበራ አድርገው የቋንቋውን ሰዋስዋዊ አጠቃቀም እና ፍች እንዲገነዘቡ የሚያደርግ የመማር ማስተማር ሂደትን አቀላጥፎ ማቅረብ የሚያስችል መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ በተጨማሪም የቋንቋ መርሃ ትምህርትን፣ የመማሪያ መጽሐፍ እና አጋዥ መጻህፍትን ከሰዋስው ትምህርት አኳያ ለመምህራንም ሆነ ለተማሪዎች ምቹ አድርጎ የሚያቀርብ መሆኑን ይገልጻሉ፡፡

Newby (2000) እና Rattya (2014) የሥነትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶችን አስመልክቶ የሚከተለውን ሀሳብ እንዲህ ሲሉ ገልጸዋል፡፡ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ላይ የሚኖራቸው አእምሯዊ ግንዛቤ ቋንቋውን ለማወቅ ትልቅ እገዛ ያደርግላቸዋል በማለት ይገልጻሉ፡፡ከዚህም በተጨማሪ የሰዋስው ትምህርት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት መሰረት ያደረገ መሆን እንደሚገባው እንዲሁም ከፍች እና ከአጠቃቀም ጋር አቀናጅቶ በማስተማር ተማሪዎች የቋንቋውን ስርዓት ተከትለው የተለያዩ ሀሳቦችን በራሳቸው ማፍለቅ (ማመንጨት) እንዲችሉ እና ዓረፍተነገሮችን በራሳቸው እያቀናጁ እንዲመሰርቱ የሚያግዙ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች መቅረብ እንዳለባቸው በሰፊው ያብራራሉ፡፡ከዚህም ባሻገር ይዘቶቹ በጥሩ ሁኔታ የተደራጁ እና የመማር ማስተማሩን ሂደት የተቀላጠፈ እና ፈጣን እንዲሆን የሚያግዙ መልመጃዎች እና ክንውኖች ላይ የተመሰረቱ መሆን እንዳለባቸው አስረድተዋል፡፡

## 2.5. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማቅረቢያ ባህርያት

የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ለማቅረብ ይዘቶቹ የቋንቋ መማር ማስተማር ሂደትን የተሟላ የሚያደርጉ እና አላማን የሚያሳኩ መሆን አለባቸው፡፡ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር Harmer (1987፥18)“የሰዋስው ትምህርትን በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ክፍል ውስጥ ስናቀርብ የሚከተሉትን ባህርያት የሚያሟሉ ከሆነ የምናስተምረው ሰዋስው ተማሪዎቻችን ትምህርቱን ከተማሩ በኋላ የምንጠብቀውን ውጤት እናገኛለን፡፡” በማለት ይገልጻሉ፡፡ በተጨማሪም Bygate,etal.(1994፥45)በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የሚከተሉትን መስፈርቶች አሟልተው መቅረብ እንዳለባቸው ያስረዳሉ::

### 2.5.1. ትክክለኛነት

በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ የሰዋስው ህጎች ትክክለኛ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ምክንያቱም ለተማሪዎች እውነተኛ እና ተጨባጭ የሆነውን የሰዋስው ህግ በማስተማር የቋንቋ እውቀታቸውን አስተማማኝ ማድረግ ስለሚያስፈልግ ነው፡፡የሰዋስው ትምህርት ህጎች ትክክለኛ መሆን ለትምህርቱ ግልጽነትን፣ ቅለትን፤ተጨባጭነትን እና ተገቢነትን ከማላበስ አንጻር ትልቅ ሚና አለው፡፡በእርግጥ አንድ የስነልሳን ጥናት በአንድ ወቅት ትክክል ነው ቢባልም በሌላ ጥናት ሊተችና ውድቅ ሊሆን ይችላል፡፡የሰዋስው ይዘቶችን ከስህተት የጸዱ ለማድረግ ተቀባይነት ያላቸውን የጥናት ውጤቶች መቃኘት አስፈላጊ ነው፡፡ስለዚህ ትክክለኛ የሆነ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን በማቅረብ ተማሪዎችን ከትክክለኛው የቋንቋ ስርዓት ጋር ማስተዋወቅ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል Westney (1994) “ትክክለኛ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ እውነት መሆን አለበት፡፡በትምህርት የሚቀርበው ሰዋስው ከቋንቋ ህግ ማፈንገጥ የለበትም፡፡”በማለት ገልጸውታል፡፡

### 2.5.2. ግልጽነት

የሰዋስው ትምህርቱን ለተማሪዎች በምናቀርብበት ወቅት ተማሪዎቹ ትምህርቱ የቀረበበትን ሁኔታ ከመረዳት አንጻር ግራ መጋባት የለባቸውም፡፡ማለትም በክፍል ውስጥ የሚቀርቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ግልጽ መሆን ይገባቸዋል፡፡የሰዋስው ህጎችንም ግልጽ ለማድረግ የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት አሻሚ የሆኑ አገላለጾችን ማስወገድ እና ሌሎች ግልጽነትን የሚያመለክቱ ሁኔታዎችን መከተል ያስፈልጋል፡፡ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን መልመጃዎችና

ተግባራትን ተገንዝበው መስራት እንዲችሉ የሚቀርቡላቸው የመልመጃዎቹ ትእዛዞች እና ማብራሪያዎች በግልጽ መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡በተጨማሪም የቀረበውን ቋንቋ የሰዋስው ይዘት ምንነት በግልጽ መረዳት መቻል አለባቸው፡፡

### 2.5.3. አፍላቂነት

የሰዋስው ትምህርት አላማ ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ህግጋት እና መዋቅር ተጠቅመው ተግባቦትን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡ይህንንም ለማድረግ የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት በቂ እና ተማሪዎች የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ህግጋት በመጠቀም ሀሳባቸውን እንዲያፈልቁ እና ትክክለኛ ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ የሚያስችሉ ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.5.4. ተመጣጣኝነት

በመማር ማስተማር ሂደት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከሁሉም የሰዋስው ትምህርት ዘርፎች የተመጣጠኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡እነዚህ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ከስነድምጽ እስከ ስነፍች ድረስ ያሉትን የሚያጠቃልሉ ሲሆኑ ተማሪዎች በእነዚህ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ላይ በሚኖራቸው ግንዛቤ አማካኝነት የቋንቋውን ስርዓት እና አገልግሎት አቀናጅተው በመማር የተግባቦት ብቃትን እንዲያዳብሩ የሚያስችላቸው ሆነው መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.5.5. ተገቢነት

ጥሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በተመረጡት የቋንቋው ሰዋስዋዊ ይዘቶች እና ቋንቋውን በሚማሩት መካከል ያለውን ተገቢነት ከግምት ያስገባ መሆን ይኖርበታል፡፡ይህም ማለት የቀረቡት የሰዋስው የትምህርት ይዘቶች የትምህርቱን አላማ ለማስፈጸም ወይም ከግብ ለማድረስ ተገቢነት ያላቸው መሆን አለባቸው፡፡የተማሪዎችን እድሜ፣ የቋንቋ ችሎታ እና የቀደመ እውቀት መሰረት ያደረጉ መሆናቸውን መመልከት ያስፈልጋል፡፡በአጠቃላይ የይዘት ተገቢነት ስንል የሚቀርበው ይዘት ስለሰዋስው ምንነት እና አጠቃቀም የሚያስገነዝብ መሆን አለበት፡፡

### 2.5.6. አሳታፊ እና አስደሳችነት

በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አይረሴ እንዲሆን ተማሪዎችን የሚያሳትፍ እና አስደሳች ወይም ሳቢ ሆኖ መቅረብ አለበት፡፡የሰዋስው ትምህርት

አሳታፊ እና አስደሳች ሆኖ የሚቀርብ ከሆነ ተማሪዎች የተማሩትን የቋንቋ ትምህርት በቀላሉ ማስታወስ እንዲችሉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክትላቸዋል፡፡

### 2.5.7. ገደብ (ውስንነት)

በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ እና ውጤታማ እንዲሆን የሰዋስው ይዘቶችን ውስን አድርጎ ማቅረብ ያስፈልጋል፡፡መምህራን በቋንቋ ትምህርቱ ትኩረት ያደረገበትን ንዑስ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማሳወቅ እና በዚያው ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ምሳሌዎችን፣ መልመጃዎችን እና የተለያዩ ተግባራትን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡እዚህ ላይ ተማሪዎች በአንድ ክፍለጊዜ የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን እንዲማሩ ማድረግ አስፈላጊ አይደለም፡፡ ለታቀደው የትምህርት አላማ ማስፈጸሚያ ወይም ማሳኪያ እንዲሆኑ ተደርገው የተመረጡ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ብቻ በቅደምተከተል መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ለምሳሌ፡-የትምህርቱ አላማ የቃል ክፍሎችን እንዲለዩ ማድረግ ቢሆን የትምህርቱም አቀራረብ በዚሁ ርዕስ ዙሪያ የሚያጠነጥን መሆን ይኖርበታል፤ ወደ ሌላ ይዘት ማለፍ የለበትም ማለት ነው፡፡

### 2.5.8. ጽንሰ ሀሳብን ማስጨበጥ

በሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ውስጥ የተለያዩ ሀሳቦችን ለመግለጽ በጥቅም ላይ የሚውሉትን ቃላት ተማሪዎች የማይረዱት ከሆነ የመማር ማስተማሩ ሂደት የተሳካ እና ውጤታማ ሊሆን አይችልም፡፡ምክንያቱም በአንባቢ እና በጸሐፊ እንዲሁም በተናጋሪ እና በአድማጭ መካከል መልካም ተራክቦ የሚኖረው መልዕክት አስተላላፊው መልእክቱን ለሚያደርሰው አካል በአግባቡ ማስተላለፍ ሲችል ብቻ ነው፡፡በቋንቋ ትምህርት ውስጥ መምህራን የሚጠቀሟቸው ቃላት ከባድ ከሆኑ ተማሪዎች ፍቻቸውን ካለመረዳት የተነሳ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልእክት ለመረዳት አስቸጋሪ ይሆንባቸዋል፡፡ስለዚህ የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ጽንሰሀሳብን የሚያስጨብጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

## 2.6. የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች አቀራረብ

የሰዋስው ትምህርት አላማ ተማሪዎች የሰዋስውን ህግ በተግባቦታዊ አገልግሎቱ ተጠቅመው መልካም የሆነ መስተጋብር እንዲፈጥሩ ማድረግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንዶ የሰዋስው ትምህርቱን አሰጣጥ በተዛባ መንገድ በመተርጎም ለተማሪዎች የሰዋስው ህጉን እና ቅርጹን ብቻ በማስተማር ብቁ የሆኑ የቋንቋ ተማሪዎችን ለማፍራት ጥረት ሲያደርጉ ይታያሉ፡፡ በዚህ

ጉዳይHarmer (1987፣18) ስለሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ሲያስረዱ፤“የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ በተማሪዎች ላይ ችግር የማይፈጥር፣ ውጤታማ፣ተወዳጅ እና ተማሪዎችን የሚስብ ይዘት መሆን አለበት።”ይላሉ።

አክለውም Harmer (1987)“ጥሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ውጤታማ ሊሆን ይገባል። ይህም ማለት መምህራን ትምህርቱን የሚያቀርቡበት ሁኔታ ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን ይዘት መሰረት በማድረግ የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን ሊያፈልቁ የሚያስችላቸው መሆን አለበት። በተጨማሪም ጥሩ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ምሉዕ መሆን አለበት። የሰዋስው መዋቅር ትምህርት የሚቀርብበት አላማው ተማሪዎቹ የቋንቋውን መዋቅር ተምረው እንዲገለገሉበት ማስቻል በመሆኑ አቀራረቡም ተማሪዎች ከታቀደው አላማ እንዲደርሱ ለማድረግ የሚያስችላቸ<ውን የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችየሚቀርቡበት መሆን አለበት። በተጨማሪም በማንኛውም ጊዜ አንድ አዲስ የቋንቋ ትምህርት ይዘትን ስናስተዋውቅ የሰዋስውን ቅርጽ እና ህግ ብቻ ሳይሆን ተግባሩን፣ ፍቺውን እና አጠቃቀሙን ጭምር በግልጽ ማስተዋወቅ እና ማስተማር ተገቢ ነው።”ይላሉ።ስለዚህ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በቅንጅት በመስጠት ስርዓቱንም በማሳወቅ ተማሪዎች በቋንቋው የዳበረ እውቀት እንዲኖራቸው ይረዳል።

በቋንቋ ትምህርቱ  የተማሪዎች እውቀት እያደገ እና እየበለጸገ መሄዱ ደግሞ በቋንቋዎች መካከል ያለውን ልዩነት እየተገነዘቡ እንዲሄዱ ያግዛቸዋል።እንደ Stern(1991፣128) አገላለጽ የሰዋስው ትምህርት በተለያዩ የትምህርት አቀራረብ ዘዴዎች ላይ ሊመሰረት ይገባል። ምክንያቱም የቋንቋ አውድ በሌላ  መንገድ ከመቀጠል ይልቅ አላማ እና ስርዓት ባለው ሁኔታ ማስተማር ይቻላል።አላማ ያለው የሰዋስው ትምህርት ልምምድ እለት ተእለት ተግባር ወይም ተሞክሮ ከሚሻሻል እውቀት መለየት ያስቸግራል በማለት ያስረዳሉ።ከዚህም ባሻገር የቋንቋውን ስርዓት እና የትኩረት አቅጣጫውንም ለይቶ ማወቅ ያስፈልጋል።ሌላው የሰዋስው ትምህርት በሚሰጥበት ወቅት ርዕሱን ከማስተዋወቅ ጀምሮ ትምህርቱን በግልፅ ማቅረብ አስፈላጊ ነው።

በሌላ በኩል Odlin (1994)ስለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ሲገልጹ ጥሩ የሰዋስው ትምህርት የማይረሳ መሆን አለበት።ለተማሪው የሚቀርበውን አዲስ ጽንሰሀሳብ የሰዋስው ይዘት በበቂ ማብራሪያ የተደገፈ እና በተማሪው አእምሮ በመስረጽ የማይረሳ መሆን እንዳለበት ያስረዳሉ።

ከዚህ በላይ የቀረቡት የምሁራን ሀሳብ የሚያስረዱት አግባብነት ያለው የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ የተማሪዎቹን የመማር ፍላጎት የሚጨምርና ለትምህርቱ ተነሳሽነትን የሚፈጥር መሆን እንዳለበት፡፡የሰዋስው ትምህርቱም በሚቀርብበት ጊዜ ተማሪዎቹ በትምህርት ሂደት ተሳታፊ እንዲሆኑ አቀራረቡ ማራኪና ሳቢ እንዲሁም አስደሳች መሆን ይኖርበታል፡፡ የትምህርቱ አቀራረብ ማራኪ (ሳቢ)ሆኖ መቅረብ ደግሞ ተማሪዎቹ የሚቀርብላቸውን የቋንቋ መዋቅር አይረሴ ያደርገዋል፤በቀላሉ ማስታወስ እንዲችሉ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረክታል፡፡በሌላ በኩል የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥ ሲሰጥ በህግና በቅርጽ ላይ ብቻ በማተኮርና በተናጠል ከማስተማር ይልቅ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በቅንጅት የሰዋስው ስርዓቱንም በማሳወቅ ተማሪዎች ቢማሩ በቋንቋው ላይ ብቁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል፤ የዳበረ እውቀትና ችሎታ እንዲኖራቸውም ከፍተኛ ሚና ይኖረዋል፡፡

በአጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ እንደ ትምህርቱ ውስብስብነት እና እንደ ተማሪው ማንነት (ዳራ) ታይቶ በተግባር ላይ የሚውል ነው እንጂ ዝም ብሎ ከተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች አንዱን መርጦ በዘፈቀደ መጠቀም አስፈላጊ አይደለም፡፡ ምክንያቱም ዘመናዊው የሰዋስው የማስተማር ስልት የተውጣጣ አቀራረብን በመጠቀም ማስተማር የተሻለ እና ተማሪዎችን ውጤታማ የሚያደርግ እና ለስኬት የሚያበቃ ስለሆነ ነው፡፡ በተጨማሪም የሰዋስው ትምህርት አቀራረቦች በአዲሱ የሰዋስው ትምህርት ማለትም የድምጾች፣ የምእላዶች፣ የቃላት እና የስነአገባብ፣ ወዘተ. ይዘቶች ተማሪዎች ከሚወዷቸው የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች ጋር ተጣጥመው ሊቀርቡላቸው ይገባል፡፡ እንዲሁም ይዘቶቹ ከተማሪዎቹ ፍላጎት እና የእውቀት ደረጃ ጋር ተስማምተው (ተጣጥመው) መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.7. የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ዘዴ

የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ በተለያዩ የቋንቋ ባለሙያዎች ዘንድ ተቀራራቢነት ባላቸው ጽንሰሀሳቦች ዙሪያ የሚያጠነጥን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ የተለያየ መሆኑን ማየት ተችሏል፡፡እንደ Batstone (1994፤5) ገለጻ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ዘዴ አንደኛው እንደ ውጤትተኮር ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እንደ ሂደትተኮር ዘዴ ነው፡፡ውጤትተኮር የሰዋስው አቀራረብ ዘዴ አብዛኛው በመምህራን የሚተገበር ሲሆን የሰዋስውን ትምህርት ለምሳሌ፡- ስም፣ ቅጽል፣ግስ፣ተውሳከ ግስ፣ ወዘተ.በማለት በየቃል ክፍላቸው በመመደብ በገለጻ

መልክ የሚቀርብ ነው።ሂደትተኮር የሰዋስው ትምህረትት አቀራረብ ዘዴ ደግሞ የሰዋስው ትምህርትን በቋንቋ ይዘት በሂደት ማስተማር እንደሆነ አብራርተዋል።

በሌላ በኩል Bygate, etal.(1994፣22)፣ Larsen (1991፣292) እና Harmer (1991፣18) ስለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብ ሲያስረዱ አራት አይነት የአቀራረብ መንገዶች (ዘዴዎች) እንዳሉ ይጠቁማሉ።እነሱም፡-ውጤትተኮር የአቀራረብ ዘዴ፣ሂደትተኮር አቀራረብ፣ ሰዋስውን እንደ ክሂል ማቅረብ እና ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በሆኑ መንገዶች ማቅረብ እንደሚቻል ገልጸዋል።

## 2.7.1. ውጤት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ

የውጤትተኮር አቀራረብ ዘዴ ዋና አላማ የቋንቋ መምህራን ቃላትን፣ ሀረጋትን እና ዓረፍተነገሮችን እንደ ምሳሌ እያቀረቡ በገለጻ መልክ አወቃቀሩን አንድ በአንድ ማስተማር እንዲችሉ ማድረግ ነው።ይህም ተማሪዎቹ መምህራን በሰጧቸው ምሳሌ መሰረት የተለያዩ ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ ያደርጋል።በተጨማሪም ይህ አቀራረብ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ላይ በማተኮር የቃላት እና የዓረፍተነገር አመሰራረት ችሎታ እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው።በቋንቋው መዋቅራዊ ስርዓት ትክክለኛነት ላይ በመመስረት የሰዋስው አሀዶችን በተናጠል በመተንተን ተማሪዎች በቋንቋው ህግ ተመስርተው ትክክለኛ ዓረፍተነገሮችን እንዲያፈልቁ የሚያስችል ነው።ይህንን ሀሳብ በማጠናከርBygate,etal.(1994) ሲገልጹ፣ ‹‹ይህ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ ሁለት ደረጃዎችን የያዘ ነው። የመጀመሪያው ደረጃ ተማሪዎች በሚቀርቡላቸው ግብዓቶች አማካኝነት የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግበት ሲሆን ሁለተኛው ደረጃ ደግሞ ተማሪዎች በተረዱት መሰረት የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት በጠበቀ ሁኔታ የራሳቸውን ዓረፍተነገር እንዲያፈልቁ በማድረግ ሊከወን (ሊተገበር) የሚችል ነው።›› በማለት ያስረዳሉ።

እንደTopkins (1995) አባባል ውጤትተኮር የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ልማዳዊ የሆነ የትምህርት አቀራረብ በመጽሐፍ ላይ ብቻ የተመሰረተ እና የቋንቋ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ህግጋት እና ብያኔዎችን እንዲያጤኑ ቃላት እና ዓረፍተነገሮችን እንዲመሰርቱ በማድረግ ላይ ትኩረት የሚያደርግ መሆኑን ያስረዳሉ። በውጤትተኮር የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት አላማም ተግባቦት ላይ ሳይሆን ተማሪዎች የቋንቋውን ቃላት በቃል ክፍላቸው ማለትም ስም፣ ግስ፣ ቅጽል፣ ወዘተ. በማለት እንዲለዩ እና ቃላትን፣ሀረጋትን እና

ዓረፍተነገሮችን በተናጠል እንዲመሰርቱ እንጂ የቋንቋውን ቅርጽ ከተግባቦት ጋር በማቀናጀት እንዲለማመዱ የሚያግዝ ዘዴ እንዳልሆነ ይገልጻሉ፡፡

በአጠቃላይ ይህ የማስተማር ዘዴ በይበልጥ ትኩረት የሚያደርገው የሰዋስውን ህግ በመተንተን ማስተማር ላይ ስለሆነ የተማሪዎችን የተግባቦት ብቃት የማያዳብር በመሆኑ ከጥንካሬው ይልቅ ደካማ ጎኑ ያመዘነ ዘዴ ነው፡፡

## 2.7.2. ሂደት ተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ

የዚህ ዘዴ ዋና አላማ ሰዋስውን ለተግባቦታዊ አገልግሎት የማዋል ተግባርን የሚመለከት ነው፡፡ ሂደትተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት የሚያውቁት በተለያዩ ተግባራዊ ልምምዶች ውስጥ ሲያልፉ ነው፡፡ስለዚህ ለቋንቋ ቅርጽ ትኩረት ሰጥቶ ከማስተማር ይልቅ ተማሪዎች ከሚያከናውኗቸው የተለያዩ ተግባራት የታላሚውን ቋንቋ ስርዓት በሂደት ሊደርሱበት የሚችሉበትን የመማር ማስተማር ተግባር ላይ ያተኩራል፡፡ይህ የአቀራረብ ዘዴ ዋና ትኩረቱን በመዋቅር ፍች ላይ ያደረገ በመሆኑ ተማሪዎች ውይይቶችን፣ መልሶችን፣ ክርክሮችን፣ወዘተ.በማድረግ የቋንቋ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ የሚያግዝ አቀራረብ ነው (Bygate,etal.1994)፡፡ሂደትተኮር የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስዋዊ ይዘቶችን ከማህበራዊ ሁኔታዎች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ ሌላው የዚህ ዘዴ ጠቃሚ ጉዳይ ነው፡፡ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ Thornbury (1999) ተማሪዎች እያዳመጡ፣ እየተናገሩ፣እያነበቡ እና እየጻፉ ሰዋስዋዊ መዋቅርን እንዲማሩ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብ እና ከመጻፍ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ አስፈላጊ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

ከዚህ በላይ የቀረበው የምሁራኑ ገለጻ የሚያስረዳው የሰዋስው ትምህርትን ከክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማቅረብ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ነው፡፡ተማሪዎች ከራሳቸው የህይወት ገጠመኝ በመነሳት ህጉን በራሳቸው ጥረት እንዲያውቁ ይደረጋል፡፡ይህም ማለት ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍች እና አውዳዊ አጠቃቀም ተገንዝበው በቋንቋው መገልገል እንዲችሉ ያደርጋል፡፡ማለትም ተማሪዎቹ ታላሚውን ቋንቋ ለተግባቦታዊ መጠቀሚያ ያውሉታል ማለት ነው፡፡

በሌላ በኩል ንጥል ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በማስተማር ተማሪዎች በቋንቋው በአግባቡ እንዲገለገሉበት ማስቻሉ ቀላል አይሆንም፡፡ስለዚህ የሰዋስው ይዘቶቹን በንጥል ከማስተማር ይልቅ በአውድ ውስጥ በማቅረብ ተማሪዎችቀጥተኛበሆነ መንገድ የቀረበላቸውን የሰዋስው መዋቅር በተዘዋዋሪ መንገድ እንዲገነዘቡ ይረዳቸዋል፡፡ሰዋስዋዊ መዋቅሮችን በአውድ ውስጥ ለማቅረብ ምንባብን መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡በሰዋስው እና በማህበራዊ ሁኔታ መካከል የሚኖረውን ተዛምዶ ከግምት ውስጥ በማስገባት ለሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ አመቺ ከሆኑት የማስተማሪያ ስልቶች ውስጥ አንዱ ሚና ጨዋታ ነው፡፡ ትምህርቱ በሚና ጨዋታ ከቀረበ በሰዋስዋዊ መዋቅር እና በማህበራዊ አገልግሎት መካከል ያለውን ግንኙነት እንዲረዱ እና በቋንቋው በተለያዩ ተግባቦታዊ አውዶች ውስጥ እንዲገለገሉበት ይረዳቸዋል (Celce Murcia & Sharon 1988)፡፡

የምሁራኑ ሃሳብ የሚያስረዳው የሰዋስው ትምህርቱን በሚና ጨዋታ መልክ ማቅረብ የተማሪዎችን ፍላጎት የሚያነሳሳ (የሚያነቃቃ) እና የሚቀርብላቸውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በተጠናከረ እና ውጤታማ በሆነ መልኩ እንዲለማመዱ ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ነው፡፡በሚና ጨዋታ እያንዳንዱ ተማሪ የሌላ ሰው ሚና በመውሰድ ተግባቦታዊ ልምምዱን በደስታ ያከናውናል፡፡

### 2.7.3. ሰዋስውን እንደክሂል ማቅረቢያ ዘዴ

የዚህ ዘዴ ዋና አላማ ውጤትተኮር እና ሂደትተኮር አቀራረቦችን በማጣመር በመካከላቸው ያለውን ክፍተት በመሙላት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ከክሂል ጋር አቀናጅተው እንዲማሩ እና የቋንቋ እውቀታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ነው፡፡ይህም ማለት ሰዋስውን ነጥሎ ማስተማር(ማቅረብ)ሳይሆን የቋንቋ ክሂሎችን ለማዳበር እንዲያዳምጡ፣ እንዲናገሩ፣ እንዲያነቡ እና እንዲጽፉ በማድረግ የቋንቋውን ቅርጽ የበለጠ ተጨባጭ በሆነ መንገድ ልምምዶችን እያደረጉ ተግባቦታዊ ተግባራትን በማከናወን በቋንቋው እንዲገለገሉ ማስቻል ነው፡፡

ተማሪዎች በውጤትተኮር አቀራረብ የሚማሩትን የቋንቋ ቅርጹን በይበልጥ ተጨባጭ ለማድረግ ተግባራዊ ልምምዶችን በአገልግሎት ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡ክሂሎች የተማሪዎችን በቋንቋ የመጠቀም ተጋላጭነት ስለሚያመቻቹ ሰዋስውን እንደ ክሂል ማቅረብ ውጤትተኮር እና ሂደትተኮር አቀራረቦችን በማስተሳሰር (በማጣመር) በመካከላቸው ያለውን ክፍተት ለመሙላት የሚያስችል አቀራረብ ነው (Batstone፣1994)፡፡

ይህ ገለጻ የሚያስረዳው የሰዋስው ትምህርቱን በውጤትተኮር ማለትም ሰዋስዋዊ ይዘቱን በቀጥታ በማብራራት ማስተማር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በየትኛውም የትምህርት ደረጃ ለጀማሪ ተማሪዎች ዋና ዋና ችግሮች በሆኑት የሰዋስው ህጎች ላይ በቂ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡ ፡ለዚህ ደግሞ የቋንቋ መምህራን በሳል የሰዋስው እውቀት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ምክንያቱም መምህራን በሳል የሰዋስው እውቀት ከሌላቸው ለተማሪዎቹ የሚቀርበው ይዘት በቀላሉ ለማቅረብ እና ማብራሪያ ለመስጠት ይቸገራሉ፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን ሰዋስዋዊ ይዘቱን በቀጥተኛ መንገድ ለማቅረብ የሚያስችል እውቀት ኖሯቸው ተማሪዎች በጥሩ መንገድ እንዲለማመዱ ማድረግ አለባቸው፡፡

## 2.7.4. ከዝርዝርወደ አጠቃላይ፣ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር የሚሄድ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ዘዴ

ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ የሚሄደው የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ተማሪዎቹ ከቋንቋው ዝርዝር ተነስተው ወደ አጠቃላይ የቋንቋ ህግ እንዲሸጋገሩ የሚያስችል ነው፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች ስለታላሚውቋንቋህግ በቀጥታ ከመማራቸው በፊት ከዝርዝር (ከንጥል) ተነስተው በራሳቸው ጥረትና ግንዛቤ የቋንቋውን ህግ ሊያውቁ የሚችሉበት አቀራረብ ነው፡፡ በዚህ አቀራረብ ተማሪዎቹ ለታላሚው ቋንቋ ተጋላጭ እንዲሆኑ እና በተለያዩ አውዶች ውስጥ ገብተው እንዲያዳምጡ እና እንዲያነቡ የተለያዩ ሁኔታዎችን መፍጠር ያስፈልጋል፡፡ይህ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ለተቀባይ ክሂሎች ማለትም ለማዳመጥ እና ለማንበብ ቅድሚያ በመስጠት የቋንቋውን ህግ ማወቅ ደግሞ ሂደትን ተከትሎ መምጣት ያለበት ጉዳይ ነው(Bygate, etal.1994 ፤ Nunan 1991 እና Larsen፣ 1991)፡፡

በሌላ በኩል ከአጠቃላይ (ከጥቅል) ወደ ዝርዝር (ንጥል) የሚሄደውየሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደግሞ ተማሪዎችመጀመሪያ የታላሚውን ቋንቋአጠቃላይ ህግመነሻ አድርገው ወደ ዝርዝር የቋንቋው ክፍሎች ይሸጋገራሉ፡፡ ይህም ማለት ተማሪዎች በቋንቋው ህግ ላይ ተመስርተው ዓረፍተ ነገሮችን እንዲመሰርቱ ይረዳቸዋል፤ እንዲናገሩም ያስችላቸዋል፡፡ይህም በመሆኑ ለአፍላቂ ክሂሎች ማለትም ለጽህፈት እና ለንግግር ክሂሎች መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረክታል (Bygate, etal.1994፤ Larsen፣ 1991)፡፡

በአጠቃላይ ከጥቅል ወደ ዝርዝር በሚደረግ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ለተማሪዎች ስለቋንቋው መዋቅራዊ ህግ የተወሰነ ገለጻ ከተሰጠ በኋላ በገለጻው መሰረት እንዲማሩ (እንዲያውቁ) የተፈለገው ይዘት ይቀርብላቸዋል (Nunan ፣1991)፡፡

## 2.8. በትምህርትነት የሚቀርቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች

በሥነትምህርታዊ ሰዋስው አማካኝነት ከትምህርት ጋር ግንኙነት ካላቸው ሌሎች የጥናት ዘርፎች ከሚገኙ መረጃዎች ጋር በማጣጣም ለትምህርት አገልግሎት መዋል እንደሚችሉ ይታወቃል፡፡በመሆኑም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተካተው ሊቀርቡ የሚችሉ ሰዋስዋዊ ይዘቶች ከአነስተኛው የቋንቋ ቅንጣት ማለትም ከድምጽ አንስቶ እስከ ከፍተኛው እና ውስብስብ የቋንቋ መዋቅር የሆነው ዓረፍተነገር ድረስ የሚደርሱ ናቸው(አልፋ ዩኒቨርሲቲ፣2006)፡፡እነዚህም የሰዋስው ይዘቶች የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው፡፡

### 2.8.1. ድምጾች

ማንኛውም ቁንቋ መሰረቱ ድምጽ ነው፡፡ያለድምጽ የሚከናወን ቋንቋ ባለመኖሩ የቋንቋ መዋቅሩ ጥናት መነሻ ድምጽ ይሆናል ማለት ነው፡፡ከዚህ ሀሳብ ጋር በተያያዘ ጌታሁን (2011፣ 1)“የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ መልእክት የሚያስተላልፈው የቋንቋውን ድምጾች በስርዓት አቀናጅቶ ቃላትን፣ቃላትን አቀናጅቶ ሀረግን፣ሀረግን አቀናጅቶ ደግሞ ዓረፍተነገርን በመፍጠር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የሰው ልጅ መልእክት ማስተላለፊያና ሀሳብ መግለጫ የሆነው ቋንቋ መሰረቱ የንግግር ድምጽ ነው፡፡ምክንያቱም የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ በቋንቋው መልእክት ለማስተላለፍ ወይም ለመቀበል አገልግሎት ላይ የሚውሉት የቋንቋ ክፍሎች ምስረታቸው ከድምጽ በመሆኑ ነው”በማለት ያስረዳሉ፡፡አክለውም የንግግር ድምጾች ሲጠኑ ሁለት መሰረታዊ ባህርያት ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይናገራሉ፡፡እነሱም ተናጥላዊና ቅንጅታዊ ባህርያት ናቸው፡፡ ተናጥላዊ ባህርይየሚያተኩረው በእያንዳንዱ ድምጽ አፈጣጠር ሁኔታና ከሚፈጠሩበት የአንደበት ክፍሎች ላይ ሲሆን፣ ቅንጅታዊው ደግሞ ድምጾቹ አንዱ ከሌላው ጋር በሚኖረው አቀነጃጀት ሲሆን ይህም ድምጸልሳናዊ ሂደት፣ ንበት፣ ወዘተ. ባህርያትን ያሳያሉ፡፡ይህ በመሆኑ የንግግር ድምጾችን በቋንቋ ውስጥ ተናጥላዊና ቅንጅታዊ ባህርይ መመርመር የሰዋስው ትምህርት አንዱ ትኩረት ነው፡፡

### 2.8.2. ምእላዶች

ምእላድ በሰዋስው ትምህርት ይዘት መካተት ካለባቸው መሰረታዊ ነጥቦች አንዱ ነው፡፡ ምእላዶችን በሁለት ከፍሎ ማየት ይቻላል፡፡እነሱም፡-ነጻና ጥገኛ ምእላዶች ናቸው፡፡ነጻ ምእላድ እራሱን ችሎ የሚቆምና የራሱ ፍች ያለው ሆኖ ወደሌላ አነስተኛ የቋንቋ አካል ሊከፈል የማይችል የመጨረሻው አሀድ ሲሆን ጥገኛ ምእላድ ደግሞ የመጨረሻው የቋንቋ አካል ሆኖ የራሱ የሆነ ፍች የሌለው ነው፡፡ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር ጌታሁን (2011፣ 74) እንደገለጹት፤ "ድምጾች በተናጠል ትርጉም አልባ ናቸው፡፡እነዚህ ትርጉም አልባ ድምጾች ስርዓት ባለው መንገድ ተቀናጅተው ትርጉም ያለውን አሀድ ያስገኛሉ፡፡በዚህ ሁኔታ የሚገኝ ትርጉም ያለው አሀድ ምእላድ ይባላል፡፡ምእላድ ትርጉም አዘል የሆነ የመጨረሻ ንኡስ አሀድ ነው፡፡ምእላድ ትርጉም አዘል ነው የተባለበት ምክንያት ምእላድ ትርጉም ያለው አሀድ በመሆኑ ሲሆን፣ የመጨረሻ የተባለበት ምክንያት ደግሞ አንድ ምእላድ ወደሌላ አነስተኛ ትርጉም ያለው አሀድ ሊከፈል ስለማይችል ነው፡፡"በማለት ያብራራሉ፡፡

ምእላዶችና ቃላት አንድነትም ልዩነትም እንዳላቸው እኚሁ የቋንቋ ምሁር ይገልጻሉ፡፡ እንደ ምሁሩ አባባል አንድነታቸው ሁለቱም ትርጉም አዘል ናቸው፤ቃል ነጻ በመሆኑ ራሱን ችሎ ይቆማል፡፡ይህም ከነጻ ምእላድ ጋር አንድ ያደርገዋል፡፡ልዩነታቸውን በተመለከተ ምእላድ ወደሌላ አነስተኛ ቅንጣት ሊከፈል አይችልም፤ቃል ግን ወደ ትርጉም አዘል አሀዶች ሊከፈል ይችላል፡፡ ቃል የቋንቋው ቃላት ከሚመደቡባቸው የቃል ክፍሎች የአንዱ ክፍል አባል ሲሆን ምእላዶች ግን በተለይ ጥገኛ ምእላዶች ላይመደቡ ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ምእላድ ትርጉም አልባ የሆኑ ድምጾች በስርዓት ተቀናጅተው የሚያስገኙት ትርጉም አዘል አሀድ ሲሆን፣ ቃል ግን አንድም በትርጉም አልባ ድምጾች ቅንጅት አልያም በምእላዶች ቅንጅት ሊመሰረት የሚችል ትርጉም አዘል አሀድ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡ስለዚህ የምእላዶችን ባህርይ እና አገልግሎት መመርመር የሰዋስው ትምህርት አንዱ አካል ነው፡፡

### 2.8.3. ቃላት

ቃል ትርጉም አልባ የሆኑ ድምጾች ቅንጅት ወይም በምእላዶች ቅንጅት ሊመሰረት የሚችል ትርጉም አዘል አሀድ እንደሆነ ጌታሁን (2011፣77)ያስረዳሉ፡፡የአንድ ቋንቋ ቃላት በተለያዩ የቃል ክፍሎች ሊመደቡ የሚችሉ እና የተለያዩ ጥገኛ ምእላዶችን በመውሰድ ወይም

በመጨመር ሊረቡ የሚችሉ ናቸው፡፡በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት የቃላትን አመሰራረት እና አመዳደብ ትኩረት በማድረግ ይመረምራል፡፡

### 2.8.4. ሀረጋት

የአንድ ቋንቋ ድምጾች፣ምእላዶች፣ቃላት በስርዓት ተዋቅረው ወይም ተቀናጅተው የየራሳቸውን መዋቅር ይመሰርታሉ፡፡ይህ ቃላት በስርዓት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ከቃል በላይ የሆነው መዋቅር ሀረግ ይባላል (ጌታሁን 2011፣183፤ባዬ2010 ፣167)፡፡የሀረግ መዋቅር ቃላት የቋንቋውን የመዋቅር ስርዓት ጠብቀው በመቀናጀት የሚፈጥሩት ሰፊ መዋቅር ሲሆን በዚህ ውስጥ አይቀሬው አካል መሪ ነው፡፡ማንኛውም ሀረግ መሪ አለው፡፡መሪው ለሀረጉ ወሳኝ ነገር ስለሆነ የሀረጉን አይነትም ይወስናል፡፡ስለዚህ የሰዋስው ትምህርት የሀረጋትን አመሰራረት እና ያላቸውን ሰዋስዋዊ ተግባራት በትኩረት ይመረምራል፡፡

### 2.8.5. ዓረፍተ ነገሮች

ዓረፍተነገር ከሀረግ በላይ የሆነ እና በአጠቃላይ ከስማዊ እና ከግሳዊ ሀረግ የሚመሰረት ሰፊና ትልቁ የቋንቋ መዋቅር ነው፡፡ይህ ዓረፍተነገር በውስጡ በሚይዛቸው የግስ ብዛት ተራ ወይም ውስብስብ ሊሆን ይችላል፡፡በዚህ አጠቃላይ የመዋቅር ባህርይ የሚመሰረቱ ዓረፍተነገሮች ዝርዝር የሆነ ከመዋቅራዊ ባህርያቸው እና ከአገልግሎታቸው አንጻር ይፈትሻል(ጌታሁን፣ 2011 ፣254)፡፡

## 2.9. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ትኩረት

በጥንታዊው የሰዋስው ትምህርት የቋንቋ ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት አውቀው ትክክለኛ ዓርፍተነገር እንዲመሰርቱ ማስቻል ነው፡፡ በመሆኑም የሰዋስው ትምህርት ትኩረትም በቋንቋው ቅርጽ እና መዋቅር ላይ ሲሆን ይህም መምህር-ተኮር የትምህርት ሂደትን በመከተል ተማሪዎች በሚሰጣቸው ገለጻ የታላሚውን ቋንቋ ህግጋት በሙሉ ጠንቅቀው እንዲያውቁ ማድረግ ነበር፡፡የተማሪዎች የቋንቋ ብቃት ተደርጎ የሚታየው ቃላትን በስርዓት አቀናጅተው ዓረፍተነገሮችን በትክክል መመስረት መቻላቸው ነው፡፡ እንደ Cook(2001)አገላለጽ፤“በዘመናዊው የሰዋስው ትምህርት እሳቤ ሰዋስዋዊ ቅርጾችን እና ህግጋትን ብቻ ማስተማሩ ተቀባይነት የለውም፡፡የሰዋስው ትምህርት ትኩረት በቋንቋው ቅርጽ እና መዋቅር፣ ፍች እና አጠቃቀም ላይ መሆን ይገባዋል፡፡ የቋንቋ ቅርጽ ወይም መዋቅር አንድ

የቋንቋ ክሂል እንዴት እንደተዋቀረ ያሳያል፤ፍችም እንዲሁ የመዋቅሩን ትርጉም ያስጨብጣል፡፡ የአንድን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍች ማወቅ ደግሞ ቋንቋው በአገልግሎት ላይ ሲውል በተገቢው መንገድ ለመጠቀም የሚያስችል እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡

Palmer (1984) ስለሰዋስው ትምህርት ይዘቶች ትኩረት እንደሚሉት ደግሞ "የሰዋስው ትምህርት ይዘት ትኩረት ተማሪዎች በቋንቋው ሰዋስዋዊ እውቀት ላይ የተመሰረተ የተግባቦት ብቃት እንዲኖራቸው ማስቻል ነው፡፡ተማሪዎች የቋንቋውን ቅርጽ ከፍች እና ከአጠቃቀም ጋር አጣምረው (አቀናጅተው) እንዲማሩ እና ተገቢ የሆኑ ዓረፍተነገሮችን በራሳቸው አፍልቀው እንዲጽፉ ወይም እንዲናገሩ እንዲሁም አዳምጠው ወይም አንብበው እንዲገነዘቡ (እንዲረዱ) የሚያስችል የትምህርት ሂደትን የሚከተል መሆን አለበት፡፡" በማለት ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም Ellis (2000) ስለሰዋስው ትምህርት ይዘት ትኩረት ሲያስረዱ፣‹‹የሰዋስው ትምህርት ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ባህርያት በሚገባ ተገንዝበው በተግባቦት ሂደት ጥቅም ላይ የሚያውሉበትን ስርዓት የሚያሳይ ቢሆንም ሰዋስው እና ተግባቦት ተለያይተው መታየት የለባቸውም፡፡አንድ የቋንቋ ቅርጽ የያዘውን ቃላዊም ሆነ ሰዋስዋዊ ፍች መረዳት ለተግባቦቱ የሚሰጠው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው፡፡ስለሆነም የሰዋስው ትምህርት ለቋንቋው ቅርጽ፣ ፍች እና አጠቃቀም ትኩረት መስጠት አለበት፡፡" በማለት ያብራራሉ፡፡

ከላይ የምሁራኑ ገለጻ እንደሚያስረዳው ቅርጽ፣ ፍች እና አጠቃቀም በሰዋስው ትምህርት ይዘት ውስጥ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ጉዳዮች መሆናቸው ነው፡፡በሰዋስው ትምህርት ይዘት ቅርጽ፣ፍች እና አጠቃቀም የተሳሰሩ በመሆናቸው ተነጣጥለው መታየት እንደሌለባቸው ነው፡፡ በአጠቃላይ እነዚህ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች የተያያዙ እና ለቋንቋ ትምህርቱ አላማ መሳካት የጎላ ሚና እንዳላቸው መገንዘብ ተችሏል፡፡

## 2.10. የሰዋስው ትምህርት ዝግጅት

የሰዋስው ትምህርት ዝግጅትን አስመልክቶ መምህራን የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካ እና ውጤታማ እንዲሆን በሰዋስው ትምህርት ይዘት ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት የቋንቋ ይዘቱን መዋቅር እና ስለሚያካትታቸው ይዘቶች ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ ምክንያቱም አንዳንድ የሰዋስው መዋቅሮች ከተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር ተመሳሳይ እና በቀላሉ ሊገነዘቧቸው የሚችሉ

ሲሆን አንዳንዱ ግን ሙሉ ለሙሉ የተለያዩ እና ተማሪዎቻችን ቶሎ ሊረዷቸው የማይችሉ ናቸው፡፡ስለዚህ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት በቂ ጊዜ ወስደው ሊዘጋጁበት ይገባል (Ur 1988፣5)፡፡በዝግጅት ወቅትም መምህራን የሚከተሉትን ነጥቦች ከግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.10.1. ዓላማ

ዓላማ ተማሪዎች አንድን የትምህርት ይዘት ከተማሩ በኋላ መጨረሻ ላይ ከተማሪዎች የሚጠበቀው ግብ ነው፡፡በመሆኑም መምህራን አንድን የትምህርት ይዘት ሲያዘጋጁ ከትምህርቱ በኋላ ከተማሪዎች የሚጠበቀውን ግልጽ የሆነ አላማ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡ የሰዋስው ትምህርት ዋና አላማ ተማሪዎች ተግባቦታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ (እንዲተገብሩ) የሚያደርግ መሆን አለበት፡፡ይሁንና የሰዋስው ትክክለኛነት ላይም በመጠኑ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡ይህን ሀሳብ በተመለከተ Ur(1988)“የሰዋስው ልምምዱ ተፈላጊውን የቋንቋ ትምህርት ውጤት ሊያስገኝ የሚችለው በሰዋስው ትክክለኛነት እና በተግባቦታዊ ክንውን ላይ የተመሰረቱትን ሁለቱንም አላማዎች መሠረት በማድረግ የተዘጋጀ እንደሆነ ነው”በማለት ይገልጻሉ፡፡ይህም በመሆኑ መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ሲያዘጋጁ ሁለቱንም ማለትም ትክክለኛነትን እና ተግባቦታዊ ተግባራትን ከግምት ውስጥ በማስገባት ግልጽ የሆነ አላማ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.10.2 .መልመጃዎች

በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ሂደት ተማሪዎች እንዲለማመዱ እና ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ መምህራን የተለያዩ የሰዋስው መልመጃዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋል፡፡ ተማሪዎች የቀረበላቸውን አዲስ የቋንቋ መዋቅር በተግባቦታዊ ልምምድ ሂደት አማካኝነት ማገናዘብ እና ማስረጽ እንዲሁም ከክፍል ውጭ ባለው አውድ መገልገል አለባቸው፡፡ ይህንን ለማድረግ ደግሞ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ለማስተማር ዝግጅት ሲያደርጉ ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ እና አሳታፊ የሆኑ መልመጃዎችን ማዘጋጀት ይኖርባቸዋ(Grant 1987፣15)፡፡ከዚህም በተጨማሪ በክፍል ውስጥ የሚገኙት ተማሪዎች የተለያየ የመማር ስልት ያላቸው በመሆኑ የሚዘጋጁት መልመጃዎች የተማሪዎችን ዳራዊ ሁኔታ ያገናዘቡ እና በገሃዱ አለም ተማሪዎች የሚገለገሉበትን የቋንቋ አጠቃቀም አካተው የያዙ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.10.3. መርጃ ( ደጋፊ) መሳሪያዎች

መርጃ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት አይረሴ ለማድረግ እና ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በቀላሉ እንዲገነዘቡ እና እዲያሰርጹ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ይህንንም ለማድረግ መምህራን በክፍል ውስጥ መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ስዕላዊ መግለጫዎችን፣ ሠንጠረዦችን፣ የፊልም ቅንጫቢን፣ አጫጭር ምንባቦችንወዘተ. በመጠቀም ትምህርቱ ተጨባጭ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ስለዚህ የቋንቋ መምህራን በሰዋስው ትምህርት ዝግጅት ወቅት መርጃ መሳሪያዎች ላይ ትኩረት በመስጠት መጠቀም ይኖርባቸዋል (Cunningsworth1984፣ 50)፡፡

## 2.11. የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ

የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብን በተመለከተ መምህራን በቂ ዝግጅት በማድረግ የሰዋስው ትምህርትን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ይህም የተግባቦታዊ ሰዋስው ትምህርትም በመማሪያ ክፍል ውስጥ በሚከተሉት ቅደም ተከተሎች ይከናወናል(መሰሉ፣ 1994)፡፡

1.**ማቅረቢያ፡-**ይህ በመማሪያ ክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ሂደት የመጀመሪያ ትግበራውይም መግቢያ ነው፡፡በዚህ ደረጃ አዲሱ ሰዋስዋዊ ቅርጽ የሚይዘው ፍች እና አጠቃቀም ለተማሪዎቹ በአውድ አማካኝነት ግልጽ የሚደረግበት ነው፡፡ በማቅረቢያ ላይ ተማሪዎቹ አስቀድመው የተማሩትን እና አዲስ የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት እንዲያያይዙ (እንዲያዛምዱ) ይደረጋል፡፡በዚህ ሁኔታ ተማሪዎቹ ለትምህርቱ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው ያደርጋል፡፡አዲሱ ትምህርት የሚቀርብበት አውድ በተለያዩ መንገዶች ሊቀርብ ይችላል፡፡ እነዚህንም እንደሚከተለው ማቅረብ ይቻላል፡፡

**ሀ.በምልልስ፡-**ይህ በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ተግባቦት ነው፡፡ይህም ሰዋስዋዊ ቅርጾችን ለማስተዋወቅ የሚቀርበው አውድ በሁለት ሰዎች መካከል ሊካሄድ የሚችል ንግግር ሲሆን አዲሱን የቋንቋ ቅርጽ፣ፍች እና አጠቃቀም በግልጽ በማሳየቱ እና ባለማሳየቱ ላይ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡በሁለቱ ሰዎች መካከል ለማድረግ የተመረጠው ንግግርም በተማሪዎቹ የክፍል ደረጃ እና ባህል አንጻር ተገቢነት ያለው መሆን አለበት፡፡

**ለ.ገጠመኞችን በመጠቀም፡-**ሰዋስዋዊ የትምህርት ይዘትን ለተማሪዎቹ ለማቅረብ የተለያዩ ገጠመኞችን በክፍል ውስጥ መጠቀም ይቻላል፡፡የሚቀርቡት ገጠመኞች እውነተኛ ወይም ፈጠራ

ሊሆኑ ይችላሉ፡፡እነዚህ በጥቅም ላይ የሚውሉት ገጠመኞች ከተማሪዎቹ ገጠመኝ ጋር የተያያዙ ቢሆኑ የተማሪዎቹን ስሜት በመቀስቀስ እና በማነሳሳት የሰዋስው ትምህርቱ ግልጽ እና ቀላል ሊሆንላቸው ይችላል፡፡

**ሐ.ማብራሪያ በመስጠት፡-**የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን ወደ መማሪያ ክፍል በማምጣት በቂ ማብራሪያ እየሰጡ የሰዋስው ትምህርቱንበአውድ ማስተማር ነው፡፡ለዚህም የተለያዩ ስዕሎችን፣ ቻርቶችን፣ወዘተ.በመማሪያ ክፍል ውስጥ በመጠቀም ማስተማር ይቻላል፡፡ለምሳሌ፡-ምዕላዶችን ለማስተማር ቻርት(ሠንጠረዥ) በመጠቀምማብራሪያ እየሰጡ ማስተማር ይቻላል፡፡

**መ. መሸጋገሪያ መጠቀም፡-**ይህ በተማሪዎቹ የቀደመ እውቀት ላይ ተመስርቶ ከዚያም አዲሱ የሰዋስው ትምህርት ይዘት በአውድ የሚቀርብበት መንገድ ነው፡፡ይህም አውድ በመምህራን አማካኝነት ይዘጋጃል፡፡በዚህ አካሄድ የዕለቱ የሰዋስው ትምህርት የሚጀምረው የባለፈውን በማስታወስ መልክ ነው፡፡ለምሳሌ፡-ተማሪዎቹ ቀደም ሲል ስለምዕላድ ምንነትተምረው ከሆነ ከዚያ በመነሳት ወደ የምዕላድ አይነቶች መሸጋገር ይችላሉ፡፡ከዚያ የሰዋስዋዊ ቅርጹን፣ፍች እና አጠቃቀሙን ግልጽአድርጎ በማሳየት ወደሚቀጥለው እንዲሸጋገሩ ማድረግ ነው፡፡

2. **ማውጣጣት፡-**ይህ ተማሪዎቹ በአውድ የቀረበውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ ተጠቅመው እንዲናገሩ የሚደረግበት ሂደት ነው፡፡ይህም ተማሪዎች ሀሳባቸውን አፍልቀው እንዲናገሩ የሚረዷቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ ይካሄዳል፡፡መምህራን ተማሪዎቹ አዲሱን ቅርጽ ተጠቅመውየማፍለቅ ችሎታቸው ላይ ተመስርተው ወደየትኛው ደረጃ መሸጋገር እንዳለባቸው ይወስናሉ፡፡ ይኸውምእንደሚከተለው ይተገበራል (ይከናወናል)፡፡

- ተማሪዎቹ አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተጠቅመው በራሳቸው ማፍለቅ ካልቻሉመምህራን ወደ ማብራራቱ ይሄዳሉ፡፡
- የተወሰኑ ስህተቶችንእየፈጸሙ ማፍለቅ ከቻሉ ስህተቶችን ማረም እንዲቻል ወደ አፍጽሞ ማፍለቅ ይሸጋገራሉ፡፡
- ተማሪዎቹ ይዘቱን የሚያውቁት ሆኖ መጠነኛ ልምምድ የሚያስፈልጋቸው ከሆነ ወደ ፍልቀራስ ይሸጋገራሉ፡፡

**3.ገለጻ፡-**ይህ መምህራን አዲሱን የቋንቋ ይዘት እንዴት በጥቅም ላይ እንደዋለ የሚያስረዱበት ሂደት ነው፡፡ይህም ተማሪዎቹ አዲሱ የሰዋስው ቅርጽ የሚዋቀርበትን ሁኔታ እንዲገነዘቡ

ያደርጋቸዋል፡፡በዚህ ደረጃ ላይ ተማሪዎቹ የሚማሩት ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋ ከሆነ በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ ቋንቋ ማብራሪያ መስጠት ይቻላል፡፡

**4.አፍጽሞ ማፍለቅ፡-**ይህ ተማሪዎቹ አዲስ በቀረበው የሰዋስው ማስተማሪያ ይዘት ላይ የተገደበ ልምምድ የሚያደርጉበት ደረጃ ነው፡፡ልምምዱ የቀረቡትን ምሳሌዎች ደጋግሞ በመተግበር ይከናወናል፡፡በዚህ ደረጃ ከአጠቃቀም እና ከፍች ይልቅ ከስህተት የጸዳ ትክክለኛነት ላይ ትኩረት ያደርጋሉ፡፡በመሆኑም መምህራን ተማሪዎቹ አዲሱን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በትክክል ማዋቀር መቻላቸውን ይከታተላሉ፡፡ተማሪዎችም አዲሱን የትምህርት ይዘት በትክክል በማፍለቅ ያዋቅራሉ፡፡

**5.ፍልቀራስ፡-**ይህ የሰዋስው ትምህርት ሂደት የመጨረሻው ደረጃ ነው፡፡የሰዋስው ትምህርቱ ወደፍልቀራስ የሚሸጋገረው መምህራን ተማሪዎቹ አዲስ የቀረበውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ በትክክል ማዋቀራቸውን ሲያረጋግጡ ብቻ ነው፡፡ይህ ተማሪዎቹ የተማሩትን ሰዋስዋዊ ቅርጽ ተጠቅመው የራሳቸውን ዓረፍተነገር የሚመሰርቱበት እና ሀሳባቸውን መግለጽ የሚችሉበት ደረጃ ነው፡፡ ተማሪዎቹ ትክክለኛ ዓረፍተነገር ማፍለቅ ከቻሉ አላማው ከግብ ደርሷል ማለት ይቻላል፡፡ካልሆነ ግን መምህራን ወደኂላ ተመልሰው የተለያዩ መልመጃዎችን እና ተግባራትን በመስጠት እንዲለማመዱ ማድረግ አለባቸው፡፡ ተማሪዎቹም የሚሰጣቸውን ተግባራት በሚገባ በማከናወን ትክክለኛ ዓረፍ ተነገሮችን ማፍለቅ ይኖርባቸዋል፡፡ መምህራን ተማሪዎቹ የራሳቸውን ዓረፍተነገር ሲመሰርቱ የሰዋስዋዊ ቅርጹን፣አወቃቀሩን፣አጠቃቀሙን እና ፍችውን መረዳት አለመረዳታቸውን ማረጋገጥ ይኖርባቸዋል፡፡

## 2.12. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማለማመጃ ስልቶች

ተግባቦታዊ የቋንቋ ትምህርት አላማ ተማሪዎች የሚማሩትን ቋንቋ ተጠቅመው ጥሩ የሆነ መስተጋብር በመፍጠር ተግባቦት እንዲያከናውኑ ማስቻል ነው፡፡ይህንንም በተሳካ መንገድ እንዲያከናውኑ ለማድረግ የሚያስችሉ የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ማለማመጃ ስልቶች (ብልሃቶች) አሉ፡፡እነዚህም ስልቶች ከሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት፣ ከመልመጃዎች እና ከተማሪዎች የትምህርት ደረጃ አንጻር የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ (Ur ፣ 1988)፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

**ሀ/ ምልልስን በመጠቀም ማቅረብ፦**ምልልስ የሰዋስው ትምህርትን በክፍል ውስጥ ለማለማመድ ከምንጠቀምባቸው ስልቶች አንዱ ነው፡፡ምልልስ በመማሪያ ክፍል ውስጥ ያሉት ተማሪዎች አንዱ ጠያቂ አንዱ መላሽ እንዲሆን በማድረግ ጥንድ ጥንድ ሆነው የሚለማመዱበት ስልት ነው፡፡በዚህ ስልት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርብላቸውን የሰዋስው ህግጋት ወዲያውኑ ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱ ይረዳቸዋል፡፡በአብዛኛው ይህንን ስልት መጠቀም ያለብን ተማሪዎች ያላቸውን ችሎታ እንዲገልጹ በሚያደርግ ምሳሌ ቢሆን ተመራጭ ይሆናል በማለት Harmer (1987፣ 19) ያብራራሉ፡፡

**ለ/ ሚና ጨዋታን መጠቀም፡-**ሚና ጨዋታ ተማሪዎች የሌላውን ሰው ሚና በመውሰድ ተግባቦታዊ ልምምድ የሚያደርጉበት ስልት ነው፡፡ይህንን ስልት ተጠቅሞ የሰዋስው ህግጋት ላይ ተማሪዎች እንዲለማመዱ ማድረግ የተማሪዎችን ፍላጎት በማነሳሳት (በማነቃቃት) ተግባቦታዊ ተግባራትን እንዲያከናውኑ ያደርጋል፡፡ከዚህም ባሻገር የሚቀርብላቸውን የሰዋስው መዋቅር እንዲያስረዱ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ስለዚህ መምህራን የሰዋስው መዋቅርን የያዙ አውዶችን በመምረጥ ተማሪዎች ሌላውን ወክለው እንዲጫወቱ በማድረግ ማለማመድ እንደሚቻል Grant (1987፣42)ይገልጻሉ፡፡

**ሐ/ ማሳየትን በመጠቀም ማለማመድ፡-**በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ለማለማመድ የምንጠቀምበት ስልት ማሳየት ነው፡፡ይህንን ስልት በመጠቀም መምህራን በመማሪያ ክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ያሉ የተለያዩ ቁሳቁሶችን ወደ ክፍል በማምጣት ማለማመድ ይቻላል፡፡መምህራን በክፍል ውስጥ የሰዋስው መዋቅርን በማሳየት ለማስተማር ወይም ለማለማመድ የእጅ ጣቶችን በማሳየት ነጠላ እና ብዙ ቁጥር አመልካቾችን ይጠቁማሉ፡፡ የጊዜ አመልካቾችን በመጠቀም ደግሞ ስለ የዋህ ኃላፊ ጊዜ፣ የአሁን ጊዜ እና የትንቢት ጊዜ የሚሉትን ያለማምዳሉ በማለት Harmer (1987፣25-26) ያብራራሉ፡፡

**መ/ ችግር ፈቺ ስልትን በመጠቀም ማለማመድ፡-**ይህ ስልት በክፍል ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውለው የታላሚው ቋንቋ ተማሪዎች መካከለኛ ደረጃ እና ከዚያ በላይ ሲሆኑ ነው፡፡ ምክንያቱም በዚህ ደረጃ ያሉ ተማሪዎች ስለታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት ትንታኔ የመስጠት እና የመናገር አቅም ስለሚኖራቸው ነው፡፡ስለሆነም ሰዋስዋዊ ህግጋትን በገለጻ መልክ ለተማሪዎች ከማስተማር ይልቅ የሰዋሰው ችግር ያለባቸውን ጥያቄዎች (መልመጃዎች) በመስጠት የሰዋስው ስህተቱን እንዲለዩ እና ስህተቱንም እንዲያቃኑ በማድረግ ማለማመድ ይቻላል(Harmer 1987፣37)፡፡

***ሠ/ ልምምድን መጠቀም፡-***የልምምድ ስልትን በመጠቀም የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ማለማመድ ተማሪዎች በሚቀርበው የሰዋስው ይዘት ላይ የተሰጣቸውን ተግባራት ወዲያው እንዲያከናውኑ ያደርጋቸዋል፡፡ከዚህም ባሻገር ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ቅርጽ እንዲለማመዱ እድል ይሰጣል(Grant 1987፣35)፡፡

በሌላ በኩል Harmer (1987፣41)መምህራን ይህንን ስልት ተጠቅመው በሚያለማምዱበት ጊዜ ተማሪዎችን በጥንድ ከማሰራት ይልቅ የክፍሉን ተማሪዎች በሙሉ በማሳተፍ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ወዲያውኑ ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ማለማመድ ይበልጡን ተመራጭ እንደሆነ ይገልጻሉ፡፡

## 2.13. የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ደረጃዎች

የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ሊከተሏቸው የሚገቡ ደረጃዎች አሉ፡፡መምህራን እነዚህን የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብ ደረጃዎች በሚገባ ተገንዝበው አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን በመገልገል የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ለተማሪዎቻቸው ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡የቋንቋ ሊቃውንት የሆኑት Celce-Murcia & Sharon (1988፣27)፣Ur (1988፣7)የሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥ በሚሰጥበትና በልምምድ ወቅት በደረጃዎች መክፈል እንደሚቻል ገልጸዋል፡፡ እነዚህም፡-የአቅርቦት ደረጃ፣የልምምድ ደረጃ፣ የአፍልቆትና የምጋቤ ምላሽ ደረጃዎች ናቸው በማለት በአራት (4) ይከፍሏቸዋል፡፡

### 2.13.1 የሰዋስው ትምህርት የአቅርቦት ደረጃ

ይህ የሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ የመጀመሪያ ደረጃ ነው፡፡ይህም አዲስ የሰዋስው መዋቅር የሚቀርብበት ደረጃ በመሆኑ መምህራን ለተማሪዎቹ የሚቀርበውን አዲሱ የሰዋስው የትምህርት ይዘት ማስተዋወቂያ ነው፡፡የዚህ ደረጃ ዋና አላማ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር አጠቃቀም፣ትርጉም እና ቅርጽ ተረድተው የቃላትን ንበት፣ዜማ፣ጥብቀት እና አጻጻፍ ለይተው እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው፡፡በመሆኑም ተማሪዎች የሚቀርብላቸውን አዲስ የሰዋስው ትምህርት ይዘት ምንነት እና አጠቃቀም ለመረዳት ትኩረት ሰጥተው በሚገባ ሊከታተሉ ይገባል፡፡መምህራንም ለተማሪዎች የሚያቀርቡትን አዲሱን የትምህርት ይዘት ተገቢ፣ግልጽ፣አይረሴ እና አፍላቂ በሆነ መልኩ ገለጻውን ትርጉም አዘል በሆነ መንገድ በአውድ ሊያቀርቡላቸው ይገባል(Harmer1991፣17፤Ur 1988)፡፡

በአጠቃላይ ይህ ደረጃ አዲሱ የታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ለተማሪዎች የሚቀርብበት በመሆኑ መምህራን የታላሚውን ቋንቋ አዲስ የሰዋስው መዋቅር ምንነት፣በዚያ ዙሪያ መነሳት የሚገባቸውን አዳዲስ መረጃዎችን ለተማሪዎች ያቀርባሉ፡፡ ተማሪዎቹም ይህንን ለመረዳት በትኩረት ያዳምጣሉ፤ለማስታወስም ይሞክራሉ፤ሰዋስዋዊ መዋቅሩ ላይ በማተኮር ለመረዳት ጥረት ያደርጋሉ፡፡መምህራን ደግሞ የተለያዩ የሰዋስው ትምህርት ማስተማሪያ ስልቶችን በመጠቀም ማለማመድ ይኖርባቸዋል፡፡የማቅረቢያ ስልቶቹ ደግሞ የሚመረጡት ከሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት መዋቅራዊ ባህርይ እና ክብደት እንዲሁም ከአቀራረቡ አመችነት አንጻር ሊሆን እንደሚችልCelce-Murcia (1991) ያስረዳሉ፡፡

## 2.13.2 . የልምምድ ደረጃ

ይህ ሁለተኛው የሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ ደረጃ ሲሆን ተማሪዎች የተወሰኑ ተግባራትን በማከናወን እውቀታቸውን የሚያዳብሩበት ወይም የሚያበለጽጉበት ነው፡፡በዚህ ደረጃ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ሲለማመዱ መምህሩ (መምህርቷ) በጥንቃቄ ይከታተላል (ትከታተላለች)፡፡በዚህ ጊዜ ተማሪዎቹ በመምህሩ (በመምህርቷ) ቁጥጥር ስር ይሆናሉ፡፡ይህም ማለት መምህሩ (መምህርቷ) ውስን መልመጃዎችን ወይም ተግባራትን በማቅረብ ተማሪዎች የሚፈጽሙትን ሰዋስዋዊ ስህተት እየተከታተለ(ች) እርማት ይሰጣል (ትሰጣለች)፡፡በዚህ ምክንያት ተማሪዎች የቋንቋውን ትክክለኛ ቅርጽ፣ አጠቃቀም እና ትርጉም በይበልጥ እያዳበሩ የሚሄዱ በመሆናቸው የሚፈጽሙትም ስህተት አነስተኛ ይሆናል፡፡ይሁንና በልምምድ ደረጃ ተማሪዎቹ የሚያከናውኑት ተግባራት ውሱን (የተገደቡ) ናቸው (Ur ፣1988፤ Cunningsworth 1984፣34)፡፡

እንደ Harmer (1987፣41) አገላለጽአብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ላይ እንዲለማመዱ የምንጠቀመው ስልት ልምምድ ነው፡፡ይህንን ስልት የምንጠቀመው ደግሞ በክፍል ውስጥ ያሉትን ተማሪዎች በሙሉ በጋራ የሚያሳትፍ በመሆኑ እንዲሁም የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር ተጠቅመው ወዲያውኑ ልምምድ እንዲያደርጉ ስለሚያግዝ ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን የተለያዩ የጥያቄ እና መልስ ልምምዶችን በመጠቀም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ላይ እንዲለማመዱ እና ተግባራቱን እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡ ተማሪዎቹም ልምምድ በሚያከናውኑበት ጊዜ ለሚፈጽሙት የሰዋስው ስህተት መምህራን በትኩረት በመከታተል ጣልቃ ገብተው እርማት ሊሰጧቸው እንደሚገባ ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም መምህራን ለልምምድ የሚያቀርቧቸው መርጃ መሳሪያዎች ተገቢና ተማሪዎችን ሊያግዙ እና ሊያበረታቱ የሚችሉ መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርባቸዋል፡፡ ከዚህም አልፎ በልምምድ ወቅት መምህራን የተማሪዎችን ስህተት በጥንቃቄ እየተከታተሉ እርማት ወይም ምጋቤ ምላሽ የሚሰጡ ቢሆንም ቀስ በቅስ ግን ተማሪዎቹ የቋንቋውን መዋቅራዊ ቅርጽ እየተለማመዱ ሲሄዱ ግድብነቱ እየቀነሰ መሄድ ይኖርበታል፡፡ ምክንያቱም ተማሪዎቹ ወደ መጨረሻ አካባቢ ተነሳሽነት ኖሯቸው በራሳቸው በመተማመን ያለፍርሃት በነጻነት ቋንቋውን ለአፍልቆት መጠቀም እንዲችሉ ያግዛቸዋል(Ur 1988፣7፤ Harmer 1987፣ 41)፡፡

## 2.13.3. የአፍልቆት ደረጃ

ይህ ሶስተኛው የሰዋስው ማቅረቢያ ደረጃ ሲሆን ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ትርጉማዊ በሆነ መንገድ ለተግባቦት እና መልእክት ለማስተላለፍ የሚጠቀሙበት ነው፡፡የዚህ ልምምድ ዋነኛ ባህርይ ተግባቦት ነው፡፡ይህንን ደረጃ Cunningsworth(1984፣34)“ነጻ የማፍለቅ ደረጃ” ይሉታል፡፡እኚህ ምሁር እንደገለጹት“የአፍልቆት ደረጃ ተማሪዎቹ የሚያከናውኑት ተግባራት እንደልምምድ ደረጃ በተገደበ ሁኔታ ሳይሆን በተጨባጭ አውድ ውስጥ ገብተው ተግባቦት (መስተጋብር)የሚፈጥሩበት እና በተለያዩ መልመጃዎች ልምምድ የሚያደርጉበት ነው፡፡በዚህ ደረጃ የመምህራን ትኩረት የሚሆነው ቅርጽ ወይም ትክክለኛነት ላይ ሳይሆን በቋንቋው የመጠቀም ችሎታቸው(ተግባቦት) ላይ ነው፡፡በዚህ ደረጃ ያለው የመምህራን ጣልቃ ገብነትም አነስተኛ በመሆኑ ተማሪዎች ያለአንዳች ፍራቻ እና መሸማቀቅ ሀሳባቸውን በነጻነት ለመግለጽ ይሞክራሉ፡፡”ይላሉ፡፡በሌላ አገላለጽ በዚህ ደረጃ ተማሪዎቹ በክፍል ውጭ ባለው አውድ የታላሚውን የቋንቋ መዋቅር እንዲገለገሉበት (እንዲጠቀሙበት) የሚያስችላቸውን ብቃት እንዲያጎለብቱ የሚደረግበት ደረጃ ነው፡፡

በሌላ በኩል በዚህ ደረጃ መምህራን መጀመሪያ ለተማሪዎቹ የታላሚውን የቋንቋ መዋቅር በክፍል ውስጥ ያቀርባሉ፡፡ከዚያም ተማሪዎቹ የተሰጣቸውን ወይም የቀረበላቸውን የቋንቋ መዋቅር ከተረዱ በኋላ የቀረበላቸውን ምሳሌ መሰረት በማድረግ የተሰጣቸውን ተግባራት ያከናውናሉ፡፡የመምህራን ሚና (ተግባር) የሚሆነው ተማሪዎች በቡድን ወይም በጥንድ ሆነው የተሰጣቸውን ተግባራት እንዲያከናውኑ ሁኔታዎችን ማመቻቸት፣እንዲሁም ተማሪዎች ሙሉ አቅማቸውን ተጠቅመው በቋንቋው ተግባቦት እንዲያከናውኑ ማድረግ ነው፡፡ለልምምዱም የተለያዩ ተግባራትን መጠቀም ይቻላል፡፡ከነዚህም ውስጥ ስዕልን መግለጽ፣የተዘበራረቁ

ዓረፍተነገሮችን በቅደም ተከተል እንዲያስቀምጡ ማድረግ፣ችግርፈቺ ተግባራትን፣ተመሳሳይ እና ተቃራኒ ፍችን የማዛመድ ስልት፣በሠንጠረዥ የቀረቡ ቃላትን የመግለጽ ስልት፣ወዘተ. በመጠቀም ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር በሚገባ እንዲለማመዱ ማድረግ አስፈላጊ ነው (Ur ፣1988 ፤ Celce-Murcia ፣1991)።

## 2.13.4. የምጋቤምላሽ (የግብረመልስ) ደረጃ

ምጋቤ ምላሽ (Feed back) በመማር ማስተማሩ የመጨረሻ ተደርጎ ቢወሰድም በሁሉም የልምምድ ደረጃ ሂደት መሰጠት እንዳለበት Celce-Murcia (1991፣229)ያብራራሉ። እንደየልምምዱ ደረጃ የመምህራን ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ስልትም እንደየሁኔታው መለዋወጥ ይኖርበታል።ማለትም በየልምምዱ የመምህራን ምጋቤ ምላሽ መሰጠት አስፈላጊ ነው።በልምምድ ደረጃ የሚሰጡት ምጋቤ ምላሾች አብዛኞቹ ወዲያውኑ ስህተት እንደተሰራ መሆን አለባቸው።

እንደ Ellis (2006፣102) ገለጻ "መምህራን የታላሚው ቋንቋ መዋቅር ካቀረቡ በኋላ ተማሪዎች ሲለማመዱ ስህተት ቢሰሩ ወዲያውኑ በማስቆም እርማት መስጠት አለባቸው። ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ መዋቅር ላይ ያላቸውን የእውቀት አድማስ እንዲያሰፉ እና ተነሳሽነትን በመፍጠር በራስ የመተማመን ስሜታቸውን እንዲያጎለብቱ ያግዛቸዋል።በሌላ በኩል በአፍልቆት ደረጃ (በተግባቦታዊ ልምምድ ደረጃ) ግን ተግባቦቱ መቋረጥ ስለሌለበት መምህራን ተማሪዎች የሚፈጽሙትን ስህተት ማስታወሻ በመያዝ ከልምምዱ በኋላ ምጋቤ ምላሽ መሰጠት ይኖርበታል።" በማለት ያብራራሉ።

ሌላው የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ በመምህራን ወይም በተማሪዎች መከናወን እንደሚችል ምሁራን ይገልጻሉ።Celce-Murcia (1991) እንደገለጹት"ጀማሪ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ ዝቅተኛ በመሆኑ በመምህራን እርማት ቢሰጥ የተሻለ ነው።ነገር ግን መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሱ ተማሪዎች ስህተትን የማገናዘብ አቅም ስለሚኖራቸው እርስ በርሳቸው መተራረም ይችላሉ።›› በማለት ይናገራሉ።

ከዚህ በላይ የተገለጸው ሀሳብ የሚያስረዳው የመማር ማስተማሩን ሂደት ውጤታማ ለማድረግ እና የተማሪዎችን ተነሳሽነት ለመጨመር ተማሪዎች ለሚፈጽሙት ስህተት ምጋቤ ምላሽ መሰጠት እንዳለበት ያስረዳል።በተጨማሪም ምጋቤ ምላሽ በመምህራን ብቻ የሚከናወን ሳይሆን ተማሪዎችም እርስ በእርሳቸው መተራረም እንደሚችሉ ነው።በሌላ በኩል በተማሪዎች

የሚሰጠው እርማት የተማሪዎችን የክፍል እና የትምህርት ደረጃ ያገናዘበ መሆን እንዳለበት ነው፡፡

በአጠቃላይ ምጋቤ ምላሽ በቋንቋ መማር ማስተማር ሂደት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው፡፡ ይህም ተማሪዎች ስለሚማሩት ሰዋስዋዊ ትምህርት እንዲያስቡ ያነቃቃቸዋል፤ ስህተታቸውን አውቀው እንዲያርሙ ይረዳቸዋል፤ችሎታቸውንም ሊፈትሹ ይችላሉ፡፡ ማለትም የተሰጣቸውን ትግበራ ምን ያህል እንዳወቁ እና ስህተታቸው የቱ ጋር እንደሆነ ወዲያው ይረዳሉ፡፡

## 2.14. የቋንቋ መምህራን ሊኖራቸው የሚገቡ ሰዋስዋዊ እውቀቶች

በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት የመማር ማስተማር ሂደት ውጤታማ እና የተሳካ እንዲሆን መምህራን በሰዋስው ትምህርት እውቀት ብቁ እና በሳል ሊሆኑ ይገባል፡፡ የመምህራን በሰዋስው ትምህርት እውቀት ብቁ መሆን ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ መዋቅር በአግባቡ ተረድተው እንዲጠቀሙበት ወይም እንዲገለገሉበት ያግዛቸዋል፡፡ ምንም እንኳ በቋንቋ ትምህርት ክፍል ውስጥ ብዙ መናገር የሚጠበቅባቸው ተማሪዎች ቢሆኑም መምህራን ለተማሪዎቹ መመሪያ ሲሰጡ እና ገለጻ ሲያደርጉ በቋንቋ አጠቃቀማቸው ጥሩ ሞዴል መሆን እንዳለባቸው Odlin (1994) ይገልጻሉ፡፡

አንድ የቋንቋ መምህር ሰዋስውን በጥሩ ሁኔታ ማስተማር እንዲችል የስነልሳን ንድፈሀሳቦችን፣ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር፣ የሰዋስው ትምህርት ማቅረቢያ ዘዴዎችን እና ስልቶችን በሚገባ ማወቅ እንዳለበት ( Harmer ፣1987) ፤Mitchell ፣1994 ፤ Rieger፣ 2009 እና Jean & Simard፣2011 )ያስረዳሉ፡፡

በሞዴልነት የሚታዩ የቋንቋ መምህራን ሊኖራቸው ይገባል የሚባሉት ሰዋስዋዊ እውቀቶች እንደሚከተለው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 2.14.1. ሰዋስውና ተግባቦት የማይነጣጠሉ መሆናቸውን ማወቅ

መምህራን ሰዋስው እና ተግባቦታዊ ስርዓት የተቆራኙ ወይም የተያያዙ መሆናቸውን ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ምንም እንኳን በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ተግባቦታዊ ብቃት ማለትም የአፍላቂ እና የተቀባይ ክሂሎች (የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብና የመጻፍ) መዳበር ዋናው የትምህርቱ አላማ ተደርጎ የሚታይ ቢሆንም የሰዋስው ችሎታ ሳይዳብር የቋንቋ ክሂሎች ሊዳብሩ

አይችሉም፡፡በመሆኑም በቋንቋ ትምህርት ውስጥ ሰዋስዋዊ ስርዓት እና ተግባቦት ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው መሆኑን መምህራን እውቀቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡

### 2.14.2. የሰዋስውና የተግባቦት እውቀት መኖር

የቋንቋ መምህራን በቂ የሰዋስው እና ተግባቦታዊ እውቀት እንዲኖራቸው የሚያስፈልግበት ዋነኛ ምክንያት የተማሪዎችን የአፍልቆት ችሎታ ለመገምገም ይረዳቸዋል፡፡ በተለይም ተማሪዎቹ የጽህፈት እና የንግግር ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ተገቢውን እገዛ ለማድረግ ያስችላል፡፡መምህራን በሰዋስው ትምህርት እውቀት በሳል ከሆኑ ተማሪዎቹ በቋንቋ ትምህርት ሂደት ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች ለመለየት፣ ሊፈጸሙ የሚችሉትን ስህተቶች ቀድሞ በማወቅ እንዳይፈጠሩ ለመከላከልና ለሚፈጽሟቸው ስህተቶችም ትክክለኛውን ሰዋስዋዊ ቅርጽ እና ተግባቦትን እንዲጠቀሙ ለማድረግ ያስችላቸዋል፡፡ በተጨማሪም መምህራን ተገቢ የትምህርት አቀራረብ ስልቶችን በመጠቀም ተማሪዎቹ ሰዋስዋዊ እውቀታቸውን ለማበልጸግ እንዲችሉ ተገቢውን እገዛ ለማድረግ ስለሚያስችላቸው ነው፡፡

### 2.14.3. የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ ስርዓት ማወቅ

መምህራን በታላሚው ቋንቋ በሳል የሰዋስው እውቀት እንዲኖራቸው የሚፈለግበት ዋናው ምክንያት ለተማሪዎች የሚቀርቡትን የማፍለቅ ክሂሎችን ከተቀባይ ክሂሎች ጋር ለማጣጣም የሚያስችላቸው በመሆኑ ነው፡፡አዳምጦ መረዳት እና አንብቦ መረዳት ከመናገር እና ከመጻፍ ይልቅ ረቂቅ የሆኑና ለመከታተልም እጅግ አስቸጋሪ የሆኑ ክሂሎች ናቸው፡፡ ተማሪዎች በማዳመጥም ሆነ በንባብ ልምምድ ጊዜ የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ወይም የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመለየት እና ለችግሮቹም መፍትሄ ለመስጠት መምህራን የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ስርዓት በሚገባ ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡

### 2.14.4. ሰዋስውን በውጤት ተኮር ዘዴ የማቅረብ እውቀት መኖር

የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርቱን በውጤትተኮር የማስተማር ዘዴ የማቅረብ እውቀቱ ሊኖራቸው ይገባል፡፡ይህም ማለት ሰዋስዋዊ ይዘቱን በቀጥታ ማብራሪያ በመስጠት ማስተማር አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለጀማሪ ተማሪዎች ዋና ዋና ችግሮች በሆኑት ሰዋስዋዊ ስያሜዎች እና ህግጋት ላይ በቂ ማብራሪያ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ስለሆነም የቋንቋ መምህራን በሳል የሰዋስው እውቀት ካላቸው እና የተማሪው እውቀት ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ የሚገኝ ከሆነ በሂደት እየዳበረ

እና እየበለጸገ ይሄዳል፡፡መምህራን የሰዋስው እውቀት ከሌላቸው ግን ለተማሪዎቹ የሚቀርበውን የሰዋስው ትምህርት ትንታኔዎችን እና ብያኔዎችን በተፈለገው መጠን ለማብራራት እና በቀላሉ ለማስተማር ይቸገራሉ፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን በሳል የሆነ የሰዋስው እውቀት እና የትምህርት ይዘቱን በቀጥተኛ መንገድ ለማቅረብ የሚያስችል በቂ እውቀት ኖሯቸው ተማሪዎች በጥሩ መንገድ የሰዋስው ትምህርቱን በቀላሉ እንዲያስተምሩ ያስችላቸዋል፡፡

## 2.14.5. ንጽጽራዊ የሰዋስው እውቀት መኖር

መምህራን ንጽጽራዊ የሰዋስው እውቀት ካላቸው በተማሪዎቹ የአፍ መፍቻ እና በታላሚው ቋንቋ መካከል የሚኖረውን ሰዋስዋዊ መዋቅር ልዩነትና አንድነት ለማወቅ ያስችላቸዋል፡፡ ንጽጽራዊ የሰዋስው እውቀት መምህራን በቋንቋ ትምህርት ሂደት ተማሪዎቹን ሊያጋጥሟቸው የሚችሉትን ችግሮች ለመለየት እና ለችግሮቹም መፍትሄ ለመስጠት እንዲሁም ለንግግርና ለጽህፈት ልምምድ ምጋቤ ምላሽ ለመስጠት የጎላ ሚና አለው፡፡

## 2.15. ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ቀደምት የሀገር ውስጥ ጥናቶች ክለሳ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ሰዋስውን በሚመለከት ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ያላቸውን ቀደምት ጥናቶች ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡ ከነዚህም ጥናቶች መካከል የአበበ መብራቴ በ 1998 ዓ.ም. ጥናት ያደረገው ነው፡፡የአበበ ጥናት ‹‹በወላይታ ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ግምገማ በሦስት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት፡ የሚል ማስተር ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ነበር፡፡

የአበበ ጥናት ትኩረት በወላይታ ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ከስነትምህርታዊ ሰዋስው አቀራረብ መርሆች አኳያ ምን ያህል ተገቢነት እንዳለው በመገምገም ጠንካራ እና ደካማ ጎኖችን መለየት ላይ ነው፡፡ለዚህም በዞኑ ካሉት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሶስቱን በናሙናነት በመምረጥ በምልከታ እና በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት መረጃ በመሰብሰብ ጥናቱን አጠናቋል፡፡

የአበበ የጥናት ውጤትም በዞኑ ያሉ መምህራን የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ አንድ አይነት በሆነ መልኩ በገለጻ እንዲሁም ምሳሌ በመስጠት እንደሆነና ለትኩረት ልምምድ የሚሰጠው ሰዓትም አነስተኛ እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከተማሪዎች አቅም በላይ እንደሆነ ለማሳየት ሞክሯል፡፡

ይህ ጥናት ከአበበ ጥናት ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም በአላማው፣ በአጠናን ዘዴው፣ በክፍል ደረጃው ልዩነት አለው፡፡የአበበ ጥናት ቃለመጠይቅን በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያነት ያላካተተው መሆኑና ጥናቱ የተካሄደውም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ የተደረገ ሲሆን ይህ ጥናት ግን በ8ኛ ክፍል በኦሮምኛ አፍፌት በሆኑ ተማሪዎች ላይ የተደረገ እና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያውም ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የጽሑፍመጠይቅ በመጠቀም ሥራ ላይ የዋለ ነው፡፡

ከአበበ መብራቴ በመቀጠል ጥናት ያካሄደው ከበደ አየለ በ1999 ዓ.ም. ሲሆን የጥናቱ ርዕስም ‹‹የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት በክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀምና አተገባበር ፍተሻ በኦሮምያ ክልል በአርሲ ዞን በሚገኙ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ 9ኛ ክፍል ናሙናነት ››የሚልለኤም.ኤ..ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት ነው፡፡

የከበደ ጥናት ያተኮረው በአርሲ ዞን በሚገኙ አራት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ የ9ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ብልሃቶችን አጠቃቀምና አተገባበር መፈተሽ ላይ ነበር፡፡በጥናቱም ያገኘው ውጤት ሁሉም መምህራን የሰዋስው ትምህርትን በገለጻና አጫጭር ምሳሌዎችን ብቻ በመስጠት እንደሚያስተምሩና ሌሎች የሰዋስው ትምህርት ማስተማሪያ ብልሃቶችን ማለትም ምልልስ፣ ሚናጨዋታ፣ አውድ፣ የመሳሰሉትን እንደማይጠቀሙ አረጋግጧል፡፡በተጨማሪም መምህራኑ የትኩረት ልምምድ ደረጃን የመጠቀም ልምዳቸው አነስተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

የከበደ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር በአጠናን ዘዴው ተመሳሳይ ቢሆንም በአላማ፣በተጠኚተማሪዎች የትምህርት ደረጃ፣ በጥናቱ ወሰን ይለያል፡፡የከበደ ጥናት የተካሄደው ለሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች የሚቀርብ የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀም እና አተገባበር ላይ የሚያተኩር ሲሆን ይህ ጥናት ግን በሰሜን ሸዋ ዞን አማርኛን እንደሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩለ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች በሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አተገባበር ላይያ ተኩራል፡፡ይህ ጥናት የመምህራንን የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አተገባበር ከመገምገም አልፎ የትምህርት ዝግጅታቸውን፣ለሰዋስው ትምህርት ያላቸውን አመለካከት እና የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ ተሳትፎ የሚዳስስ በመሆኑከ ከበደ ጥናት ይለያል፡፡

ሌላው ከዚህ ጥናት ጋር ተዛማጅነት ያለው የኢያሱ መሰለ 2003 ዓ.ም.“በ1997 ዓ.ም. በተሻሻሉት የ9ኛ እና የ10ኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፍት ውስጥ የቀረቡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣አቀራረብ እና አደረጃጀት ግምገማ “በሚል ርዕስ የተደረገ ጥናት ነው።

የኢያሱ ጥናት ትኩረት ያደረገው በመማሪያ መጽሐፍቱ ውስጥ የተካተቱት የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አመራረጥ፣አቀራረብ እና አደረጃጀት ከሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው መርሆች አንጻር ሲታይ ምን ይመስላል? በሁለቱ መማሪያ መጽሐፍት መካከል ተለጣጣቂነት አለ ወይስ የለም? የሚሉትን ጥያቄዎች በማንሳት እና ያሉትን ችግሮች በመጠቆም ለችግሮቹም የመፍትሄ ሀሳብ በ መጠቆም ጥናቱን አካሂዷል።

የኢያሱ ጥናት አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የሰነድ ፍተሻ ሲሆን ይህ ጥናት ግን ትኩረት ያደረገው በመማሪያ መጽሐፍ ግምገማ ላይ ሳይሆን የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና አተገባበርን የተመለከተና አብይ የመረጃ መሳሪያውም የክፍል ውስጥ ምልከታ በመሆኑ ከኢያሱ መሰለ ጥናት ይለያል።በተጨማሪም ይህጥናት በ 8ኛ ክፍል ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ላይ የተደረገ በመሆኑ በክፍል ደረጃም ፍጹም የተለየ ነው።

ሌላው የቅርብ ጊዜ ጥናት የሆነው በአማረ ተሾመ (2021) የተደረገ ጥናት ነው።የአማረ ጥናት የሚያተኩረው በተተኳሪ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ምን እንደሚመስል አጠቃላይ የሆነ ግምገማ በማካሄድ የሚታዩትን ክፍተቶች በመጠቆም ለታዩት ችግሮች የመፍትሄ ሀሳብ አስቀምጧል።የጥናቱ ግኝትም በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቶቹ በጥቅል ቀደም እና በዝርዝር ቀደም ተዘጋጅተው እንደቀረቡ ለመለየት የተቻለ ሲሆን ሆኖም በዝርዝር ቀደም ከቀረቡ ሰዋስዋዊ ይዘቶች መካከል ስለሰዋስዋዊ ህግጋቱ የመምህራን ዝርዝር ማብራሪያ የሚፈልጉ ሆነው ነገርግን ምንም አይነት ማብራሪያ ሳይቀመጥላቸው ተማሪዎቹ ከተቀመጠላቸው ምሳሌ በመነሳት ብቻ እንዲሰሯቸው መቅረባቸው ተገቢነት የሌለው እንደሆነ ጠቁሟል። በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ ያሉት የሰዋስው ይዘቶቹ ውጤትተኮር አቀራረብ ስልትን የተከተሉ መሆናቸውን አብራርቷል።ከተከታታይነትና ከተለጣጣቂነት አንጻርም ሲታይ የአደረጃጀት ቅደምተከተል ላይ ችግር እንደሚስተዋል አረጋግጧል።

አማረ ጥናቱን ለማካሄድ የተጠቀመበት አብይ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሰነድ ፍተሻ ሲሆን የመረጃ ምንጩም ተተኳሪ መማሪያ መጻሕፍትና መርሃ ትምህርት ናቸው፡፡የአማረ ጥናት ከሰዋስው ትምህርት እሳቤ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ዝምድና ቢኖረውም በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ፣ይዞት ከተነሳው የጥናቱ ዓላማ፣ ከተጠኚ ተማሪዎች የክፍል ደረጃ እንዲሁም ከጥናቱ ዘዴ አንጻር ፍጹም የሆነ ተዛምዶ የላቸውም፡፡

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የቀረቡት ቀደምት ጥናቶች ከሥነትምህርታዊ ሰዋስው አቀራረብ መርሆች አኳያ ዝምድና ቢኖራቸውም ይህ ጥናት ይዞት በተነሳው የጥናቱ አላማ፣በአጠናን ዘዴው፣ በተማሪዎች የክፍል ደረጃ፣ በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹ፣ በጥናቱ ወሰን፣ ወዘተ. ከሌሎቹ ተመሳሳይ ባለመሆኑ ልዩ ያደርገዋል፡፡

# ምዕራፍ ሦስት

# የአጠናን ዘዴ

## 3.1 . የናሙና አመራረጥ (አወሳሰድ) ስልት

አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማካሄድ የትምህርት ቤቶች፣ የመምህራን እና የተማሪዎች ናሙና መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በተለያዩ የናሙና አመራረጥ(አወሳሰድ) ስልቶች አማካኝነት ናሙና በመውሰድ ጥናቷን ተግባራዊ አድርጋለች፡፡

### 3.1.1. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

ይህ ጥናት የተካሄደው (የተከናወነው) በኦሮምያ ክልል በሰሜን ሸዋ ዞን ከሚገኙ ወረዳዎች ውስጥ አንዱ በሆነው በደብረሊባኖስ ወረዳ ከሚገኙ 19 የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ እርከን ትምህርት ቤቶች ውስጥ በድሬ ጅቦ እና በአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ትምህርት ቤቶች በአመቺ ናሙና ስልት የተመረጡ ሲሆን በናሙናነት የተመረጡበት ምክንያትም አጥኚዋ በመምህርነት የምታገለግለው በዚሁ ትምህርት ቤት አቅራቢያ በመሆኑ ካለው የጊዜና የገንዘብ መጠን በተወሰነ መልኩ የተመጣጠነ እና ትክክለኛ (አስፈላጊ) መረጃዎችንም በቅርበት ማግኘት ስለሚቻል ነው፡፡

### 3.1.2. የመምህራን ናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑ መምህራንን ለመምረጥ ናሙና መውሰድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ይህንንም ከሁለቱ ትምህርት ቤቶች ማለትም ከድሬ ጅቦ አንደኛ ደረጃ እና ከአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች8ኛ ክፍል የሚያስተምሩ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን አነስተኛ በመሆናቸው ወይም ሁለት ብቻ ስለሆኑ አጥኚዋ በጠቅላይ ናሙና በመምረጥ ሁለቱንም መምህራን በማሳተፍ በጥናቷ አካታለች ፡፡

### 3.1.3. የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ጥናቱ የሚያተኩረው በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በመሆኑ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን ተማሪዎች በእጣ ናሙና በመምረጥ አጥኚዋ ጥናቷን አካሂዳለች፡፡ይኸውም የጥናቱ ተተኳሪ

ሆነው የተመረጡት የተማሪዎች ብዛት ድሬ ጅቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ሁለት ቡድን (8ሀ እና 8ለ) ያለው ሲሆን ከ‹‹8ሀ›› ክፍል 34፣ ከ‹‹8ለ›› ክፍል 37 በአጠቃላይ 71 ተማሪዎች ያለው ሲሆን፣ የአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤትም ሁለት ቡድን ሲሆኑ ከ‹‹8ሀ›› 28፣ ከ‹‹8ለ›› 24 በአጠቃላይ 52 ተማሪዎችን የያዘ ነው፡፡ እነዚህ ሁለት ትምህርት ቤቶች በጠቅላላው 123 ተማሪዎች ያላቸው ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ከድሬ ጅቦ 42 ተማሪዎችና ከአባገዳ ደግሞ 38 ተማሪዎች በጠቅላላው 80 ተማሪዎች በናሙናነት ተመርጠዋል፡፡

## 3.2. የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

አጥኚዋ ለዚህ ጥናት ክንውን መረጃ ይሰጣሉ ከተባሉት አካላት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመችባቸው መሳሪያዎች ሶስት(3)ናቸው፡፡እነሱም፡-የክፍል ውስጥ ምልከታ፣ቃለመጠይቅና የጽሑፍመጠይቅ ናቸው፡፡

### 3.2.1. ምልከታ

በዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ አጥኚዋ ጥናቷን የተሟላ ለማድረግ በዋናነት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያየ ተጠቀመችው የክፍል ውስጥ ምልከታ ነው፡፡ይህም ለምልከታ ቅጽ የሚሆን የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አቀራረብና አተገባበር በተመለከተ የቋንቋ ምሁራን በምዕራፍ ሁለት ስር ካነሷቸው የሰዋስው ንድፈሀሳብ አንጻርየተዘጋጀ ሲሆን ተግባር ላይ ከመዋሉ በፊት ተገቢነቱን ለማረጋገጥ በአማካሪ ተገምግሞ አስተያየት ተሰጥቶበት ተግባር ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡የተዘጋጀው ቅጽ ሁለት ክፍሎች ያሉት ሲሆን የመጀመሪያው ክፍል የትምህርት ቤቱ ስም፣ምልከታ የተደረገበት ቀን፣ፈረቃ፣ክፍልና ሴክሽን፣ክፍለጊዜ፣የዕለቱ የትምህርት ርዕስ(ይዘት) እና የትምህርቱን ዓላማ የያዘ ቅጽ ነው፡፡

ሁለተኛው ደግሞ የሰዋስው ትምህርት ይዘት አቀራረብና አተገባበርን በሚመለከት ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት የሚያስችሉ ጥያቄዎችን አጠቃሎ የያዘ ነው፡፡ይኸውም የመምህርቷን የትምህርት ዝግጅት፣የአጋዥ(የመርጃ) መሳሪያዎችን የመጠቀም ሁኔታ፣ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን የማቅረቢያ ስልቶችን የመጠቀም እንዲሁም የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ አስር(10)ጥያቄዎችን የያዘ ቅጽ በመያዝ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ለአራት(4) ቀናት በክፍል ውስጥ ምልከታ የተደረገ ሲሆን ከእያንዳንዳቸው በሁለት(2) ዙር መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡ ፡እነዚህ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የሬቲንግ ስኬል ሞዴል ባለአራት እርከን የአጠያየቅ ስልትን

መሰረት ያደረጉ ሲሆን ሁሉም አማራጭ መልሶችን"4-እጅግ በጣም ጥሩ››፣ "3- በጣም ጥሩ"፣ "2- በመጠኑ"፣"1-በጭራሽ"የሚሉትን አማራጮች የያዙ ናቸው፡፡በአጠቃላይ ተጠኚ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር እና በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የነበራቸውን ተሳትፎ ዓላማን ከማሳካት አንጻር የነበረውን ሚና በዚህ ቅጽ ለመዳሰስ ተችሏል፡፡

## 3.2.2. ቃለ መጠይቅ

አጥኚዋ ጥናቷን የተሳካለ ማድረግ በሁለተኛነት ወይም በደጋፊነት የተጠቀመችው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ቃለ መጠይቅ ነው፡፡ይህም ለመምህራን ብቻ የሚቀርብ ሲሆን ሁለት ክፍሎችን የያዘ ነው፡፡የመጀመሪያው ክፍል ስለመምህራኑ አጠቃላይ መረጃ የያዘ ማለትም ስለመምህራኑ የትምህርት ደረጃ፣እድሜ፣ጾታ፣የሥራ ልምድ፣የሰለጠኑበት የሙያ መስክ፣ወዘተ. የሚመለከት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብና አተገባበርን የሚመለከቱ ስምንት(8)ጥያቄዎች የያዘ (ያካተተ)ነው፡፡እነዚህም መምህራኑ የሰዋስው ማስተማሪያ ስልቶችን እና የአቀራረብ ደረጃዎችን የመጠቀም ሁኔታ፣እንዲሁም ሰዋስውን በክፍል ውስጥ እንዴት እንዲያስተምሩና የመርጃ መሳሪያ አጠቃቀማቸውን የሚመለከቱ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በተጨማሪም ተማሪዎቹ የሰዋስው ትምህርትን የመማር ፍላጎታቸው፣የክፍል ውስጥ ተሳትፏቸውንና በሰዋስው ትምህርት ያላቸው እውቀት ምን እንደሚመስል የጥናቱ ተተኳሪ ከሆኑት መምህራን ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል::

እነዚህም ጥያቄዎች በክለሳ ድርሳናት ስር የቋንቋ ምሁራን ያቀረቧቸው የሰዋስው ንድፈ ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ የተዘጋጁ ሲሆን ተግባር ላይ ከመዋላቸው በፊት ተገቢነታቸውን ለማረጋገጥ በአማካሪ ተገምግመው አስተያየት ተሰጥቶባቸው ተግባር ላይ ውለዋል፡፡እነዚህ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ የሬቲንግ ስኬል (Rating Scale)የአጠያየቅ ስልትን ወይም ደረጃ/እርከን መለኪያ ዘዴን መሰረት ያደረጉ እና አማራጭ መልሶችን የያዙ በመሆናቸው የማያሰለቹ ሆነው የቀረቡ ናቸው፡ ፡በዚህ መልክ የተዘጋጁት ጥያቄዎች ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች ማለትም ከድሬ ጅቦ እና ከአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑት የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ቀርበው ምላሽ እንዲሰጡባቸው ተደርጓል፡፡ለመምህራኑ ቃለመጠይቁ ከመቅረቡ በፊት አጥኚዋ የጥናቱን አላማ ገልጻላቸው ፍቃደኝነታቸውን ካረጋገጠች በኋላ ለሚደረግላቸው ቃለመጠይቅ የየራሳቸውን ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ምላሻቸውን በማስታወሻ በመያዝ (በመጻፍ) ተፈላጊውን መረጃ ለማግኘት ችላለች፡፡በአጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ

አቀራረብና አተገባበርን በተመለከተ ተተኳሪ መምህራን ያላቸውን አስተያየት በመቀበል ከእነርሱ የተገኘውን መረጃ በማጠናከሪያነት ጥቅም ላይ እንዲውል ተደርጓል፡፡

### 3.2.3. የጽሑፍ መጠይቅ

አጥኚዋ መረጃዋን ለማጠናከር ስትል በሶስተኛነት የመረጠችው የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ የጽሑፍመጠይቅ ሲሆን ይህም የጥናቱ ተተኳሪ ለሆኑት ተማሪዎች የተዘጋጀ ነው፡፡ የጽሑፍመጠይቁ ዝግ (አማራጭ መልስ የያዙ) እና ክፍት ጥያቄዎችን የያዙ ሲሆን የጥያቄዎቹ ብዛትም11 ዝግ እና አንድ(1) ክፍት በአጠቃላይ 12 ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡ የጽሑፍመጠይቁ ሁለት ክፍሎችን የያዘ ሲሆን በመጀመሪያው ክፍል ስለተማሪዎች አጠቃላይ መረጃ የያዘ ማለትም የአማርኛ ቋንቋን መማር የጀመሩበት የክፍል ደረጃ እና የትኛው ትምህርት ቤት እንደሚማሩ የሚጠቁም ነው፡፡ሁለተኛው ደግሞ የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና አተገባበርን በሚመለከት የቀረቡ ሲሆን እነዚህም ስለመምህራኑ የሰዋስው ትምህርት አሰጣጥ፣በቂ ዝግጅት ማድረግ አለማድረጋቸውን የሚመለከት፣ በትምህርት ቤታቸው ውስጥ የመማሪያ መጽሐፍት አቅረቦት፣ስለመምህራኑ የሰዋስው ህግጋት እውቀት፣የመምህራኑ ምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ እንዲሁም ተማሪዎቹ ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው ፍላጎት ምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ የሚውሉ ጥያቄዎችን የያዘ ነው፡፡

እነዚህ ጥያቄዎች የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና አተገባበርን በተመለከተ በምዕራፍ ሁለት ስር የቋንቋ ምሁራን ያቀረቧቸውን የሰዋስው ንድፈ ሀሳብ (ብያኔዎች) መሰረት አድርገው የተዘጋጁ ሲሆን ጥያቄዎቹም የሬቲንግ ስኬል (Rating Scale) በአብዛኛው የሊከርት ስኬል (Likert Scale) እየተባለ የሚታወቀውን ባለ አምስት (5) ደረጃ/ እርከን ሞዴል ወይም የአጠያየቅ ስልትን በመከተል የተቀረጹ ናቸው፡፡ ምክንያቱም ይህ ሞዴል ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ነው፡፡መመዘኛዎቹም ባለ አምስት ስኬል ያላቸው ሲሆኑ፣ 5 "ሁል ጊዜ"፣4 "በአብዛኛው"፣3"አንዳንድ ጊዜ"2"አልፎ አልፎ"፣1 "በጭራሽ"የሚሉ አማራጭ መልሶችን የያዙ ናቸው፡፡እነዚህ መጠይቆች አጥኚዋ በጥናቷ ዓላማ ይዛ ለተነሳችባቸው ጥያቄዎች መልስ ያስገኛሉ ብላ በማሰብ በራሷ ያዘጋጀቻቸው ናቸው፡፡በጽሑፍ መጠይቁ ላይ የቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛነታቸው እና ተገቢነታቸው በአማካሪ ተገምግመው ከተረጋገጡ በኋላ ለጥናቱ በናሙናነት በተመረጡ ተማሪዎች ተሞልተው እንዲመለሱ ለማድረግ ተችሏል፡፡

## 3.3. የመረጃ አተናተን ዘዴ

የዚህ ጥናት ዋና አላማ በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረሊባኖስ ወረዳ ውስጥ ከሚገኙ ሁለት የተመረጡ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ማለትም የድሬ ጆቦ እና የአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና አተገባበርን በመፈተሽ የሚታየውን ችግር ለይቶ በማውጣት የመፍትሄ ሀሳብ መጠቆም ነው፡፡ይህንን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የመረጃ መሰብሰቢያመሳሪያዎችን ማለትምየክፍል ውስጥ ምልከታ፣የጽሑፍመጠይቅና ቃለመጠይቅን በመጠቀም ከመምህራን እና ከተማሪዎች መረጃ ለመሰብሰብ ተሞክሯል፡፡እነዚህ በተለያዩ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎችም በክለሳ ድርሳናት ስር ካሉት የምሁራን ንድፈሀሳቦች ጋር በማዛመድ ትንተና ተደርጎባቸዋል፡፡እነዚህም በክፍል ውስጥ በተካሄዱት ምልከታዎች፣ በቃለመጠይቅ አማካኝነት ከመምህራን እና በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች የተገኙት መረጃዎች በመቶኛተሰልተውትንታኔተደርጎባቸዋል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የመረጃውጤት ትንተና

### 4.1. የጽሑፍ መጠይቅና የቃለመጠይቅ መላሾች ዳራ

በዚህ ክፍል ስር የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት መምህራን እና ተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታ እንደሚከተለው ተተንትኖ ቀርቧል።

### 4.1.1. የመምህራን ዳራዊ ሁኔታ

በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመምህራን ጾታ፣ እድሜ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሰለጠኑበት የሙያ መስክ፣ የሰለጠኑበት የትምህርት አይነትና የስራ ልምድን በተመለከተ የቀረቡ መረጃዎች ናቸው። ለእነዚህ መረጃዎች መምህራኑ የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው መጀመሪያ በሠንጠረዥ ቀርቦ ትንተና ተደርጎበታል። መምህራኑን ለመለየት የድሬ ጅቦ መምህርት ‹‹አ.ቋ.››፣ የአባገዳ ደግሞ መምህርት ‹‹ኦ.ቋ.›› በማለት በሠንጠረዡ ላይ ለማሳየት ተሞክሯል።

**ሠንጠረዥ 1፦ የመምህራንን ዳራ የሚያሳይ ሠንጠረዥ፡**

<table>
<tr><th>መምህር</th><th>እድሜ</th><th>ጾታ</th><th>የትምህርት ደረጃ</th><th>የሰለጠኑበት የሙያ መስክ</th><th colspan="2">የሰለጠኑበት የትምህርት አይነት</th><th>የስራ ልምድ</th></tr>
<tr><td rowspan="2">አ.ቋ.</td><td rowspan="2">36</td><td rowspan="2">ሴ</td><td rowspan="2">ዲግሪ</td><td rowspan="2">በመምህርነት</td><td>አብይ</td><td>ንዑስ</td><td rowspan="2">9</td></tr>
<tr><td>አማርኛ</td><td>እንግሊዝኛ</td></tr>
<tr><td>ኦ.ቋ.</td><td>42</td><td>ሴ</td><td>ዲግሪ</td><td>በመምህርነት</td><td>አማርኛ</td><td>-</td><td>17</td></tr>
</table>

አ.ቋ.-- አማርኛ ቋንቋ አፍፊት ኦ.ቋ.-- ኦሮምኛ ቋንቋ አፍፊት

ከዚህ በላይ የቀረበው ሠንጠረዥ የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑትን የመምህራን ዳራ የሚያሳይ ነው። ይኸውም ሁለቱም መምህራን ጾታቸው ሴት ሲሆን እድሜያቸው መምህርት ‹‹አ.ቋ.››36 ፣ መምህርት ‹‹ኦ.ቋ.›› ደግሞ 42 ዓመት የሆኑ ናቸው።የትምህርት ደረጃቸውን ስንመለከት

ሁለቱም ዲግሪ ናቸው። በሌላ በኩል የመምህርት ‹‹አ.ቋ.››የአፍ መፍቻ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን የመምህርት‹‹ኦ.ቋ.››ደግሞ ኦሮምኛ ቋንቋ ነው።ሁለቱም መምህራን የሰለጠኑበት የሙያ መስክ በመምህርነት ሲሆን የመምህርት‹‹አ.ቋ.››አብይ የትምህርት አይነት አማርኛ እና ንዑስ የትምህርት አይነት እንግሊዝኛ ሲሆን የመምህርት ‹‹ኦ.ቋ.›› አብይ የትምህርት አይነት ደግሞ አማርኛ ነው።የሁለቱንም የስራ ልምድ ስንመለከት መምህርት ‹‹አ.ቋ.››ዘጠኝ(9) ዓመት እና መምህርት‹‹ኦ.ቋ.››ደግም 17 ዓመት የስራ ልምድ ያላቸው ናቸው።ስለዚህ ሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት መምህራን በቂ የስራ ልምድ አላቸው ማለት ነው።

በአጠቃላይ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን ዳራዊ ሁኔታ ልዩነት ቢታይባቸውም ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው።ማለትም ሁለቱም በመምህርነት ሙያ የሰለጠኑ ሲሆን የትምህርት ደረጃቸውም ሁለቱም ዲግሪ በመሆናቸው ለሚያስተምሩት የክፍል ደረጃም የሚመጥን ነው። በተጨማሪም ሁለቱም መምህራን በቂ የስራ ልምድ ያላቸው በመሆኑ የመማር ማስተማር ሂደቱን የተሳካና ውጤታማ ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው። የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን ስንመለከት መምህርት ‹‹አ.ቋ.››በአማርኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ሲሆን መምህርት‹‹ኦ.ቋ.›› ግን አፋቸውን የፈቱት በኦሮምኛ ቋንቋ ነው።

## 4.1.2. የተማሪዎች ዳራዊ ሁኔታ

የተማሪዎች ዳራ ለዚህ ጥናት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች የሚማሩበት ትምህርት ቤት፣ ጾታ፣ የአፍ መፍቻ ቋንቋ፣ሁለተኛ ቋንቋ እና አማርኛ ቋንቋን መማር የጀመሩበትን የክፍል ደረጃ የሚገልጽ ነው።ስለሆነም የተተኳሪ ተማሪዎችዳራ ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ትንተና ተደርጓል።

**ሠንጠረዥ 2፡-የተማሪዎችን ዳራ የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| የት/ቤቱ ስም | ጾታ | | | | አፍመፍቻ ቋንቋ | | | | ሁለተኛ ቋንቋ | | ትምህርት የጀመሩበት የክፍል ደረጃ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ወ | | ሴ | | ኦሮምኛ | | አማርኛ | | አማርኛ | | |
| | ብዛ | በ % | ብዛ | በ % | ብዛ | በ % | ብዛት | በ | ብዛ | በ | |
| ድሬ ጅበ | 29 | 36.25 | 13 | 16.25 | 36 | 45 | 6 | 7.5 | 36 | 45 | አምስተኛ ክፍል |
| አባገዳ | 23 | 28.75 | 15 | 18.7 | 38 | 47.5 | - | - | 38 | 47. | አምስተኛክፍ |
| ድምር | 52 | 65 | 28 | 35 | 74 | 92.5 | 6 | 7.5 | 74 | 92. | 80 |

የተማሪዎቹን ዳራ ለማወቅ ከዚህ በላይ በሠንጠረዡ ውስጥ ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የጥናቱ ተተኳሪ በሆኑ ሁለት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉ በናሙናነት የተመረጡ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኦሮምኛ እና አማርኛ ሲሆን በአማርኛ ቋንቋ አፍፈት የሆኑት የአማርኛ ቋንቋን በተገቢው ሁኔታ መጠቀም ቢችሉም ሁለቱም የጥናቱ ተተኳሪ ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋን መማር የጀመሩት አምስተኛ ክፍል ነው። ይሁንና በእነዚህ ሁለት ቋንቋዎች አፋቸውን የፈቱት ተማሪዎች ብዛት በቋንቋቸው ተለይተው ሲታዩ በአማርኛ 6 (7.5%) ፣ በኦሮምኛ ደግሞ 74 (92.5%) ተማሪዎች ናቸው። ይህ የሚያስረዳው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ተማሪዎች ማለትም 74 (92.5%) የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኦሮምኛ እና ሁለተኛ ቋንቋቸው ደግሞ አማርኛ መሆኑ ነው።

በሌላ በኩል በጣም ጥቂት የሆኑት ተማሪዎች ማለትም 6 (7.5%) ያህሉ የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ የሆኑ ተማሪዎች ናቸው።ይህ የሚያመለክተው በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ውስጥ ያሉት አብዛኞቹ ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኦሮምኛ ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋቸው ደግሞ አማርኛ መሆኑን ነው።በሌላ በኩል የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ የሆኑት ጥቂት መሆናቸውን እና እነሱም በድሬ ጅቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚገኙ ሲሆን በአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ጭራሽ አለመኖራቸውን ያመለክታል። በመሆኑም የጥናቱ ተተኳሪ የሆኑት ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸውም ሆነ ከትምህርት ቤት ውጭ እርስ በእርስ የሚግባቡበት ቋንቋ ኦሮምኛ በመሆኑ አብዛኛውን ጊዜ አማርኛ ቋንቋን ለመግባቢያነት የመጠቀም አጋጣሚያቸው አነስተኛ መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም ይህንን ጉዳይ በቃለመጠይቅ አማካኝነት ከተጠኚ መምህራን እና በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 4.2. የመረጃ ውጤት ትንተና

አስፈላጊ የሆኑት መረጃዎች በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከተሰበሰቡ በኋላ በሚያነሱት ርዕሰ ጉዳይ አኳያ ተደራጅተው በሠንጠረዥ አማካኝነት በአሃዝ (በቁጥር) እና በመቶኛ ተሰልተው በውጤቶቹ ላይ አይነታዊ የአጠናን ዘዴን በመጠቀም ትንተና ተደርጎባቸዋል። እነዚህ የተደራጁት መረጃዎች የሚያነሱትን ርዕሰ ጉዳይ መሰረት በማድረግ በሠንጠረዥ ከሰፈሩ በኋላ ትንተና እንዲሰጥባቸው ተደርጓል።

## 4.2.1. የመምህራን የትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ

በዚህ ንዑስ ክፍል ለጥናቱ በናሙናነት በተመረጡ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ተተኳሪ የአማርኛ መምህራን የትምህርት ዝግጅትን በተመለከተ በተዘጋጀው የምልከታ ቅጽ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ አማካኝነት ተጠኚ መምህራን በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርትን ሲያቀርቡ (ሲያስተምሩ) ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በተማሪዎች የጽሑፍመጠይቅ እና ለመምህራን በተደረገ ቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎች ውጤትም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሠንጠረዥ 3፡የመምህራንን የትምህርት ዝግጅት በተመለከተ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ. | የምልከታ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1. | መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ መጀመሪያ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳ ላይበመጻፍ የማስተዋወቁ ሁኔታ ምን ይመስላል ? | እጅግ በጣም ጥሩ(4) | 2 |
| | | በጣም ጥሩ (3) | - |
| | | በመጠኑ (2) | - |
| | | በጭራሽ (1) | - |

እንደሚታወቀው የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጀምረው የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅና አላማውን በግልፅ በማብራራት እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ በመሆኑም ከምልከታ በተገኘው መረጃ ሁለቱም ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ መጀመሪያ ርዕሱን በጥቁር ሰሌዳ ላይ በመጻፍ ማስተዋወቃቸው ‹‹እጅግ በጣም ጥሩ›› መሆኑን ያመለክታል፡፡ ይህም ሁለቱም ተጠኚ መምህራን ተማሪዎቻቸው የዕለቱን የሰዋስው ትምህርት ርዕስ በሚገባ አውቀው ለትግበራውም ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያበረታታ መሆኑን ከምልከታው ለማየት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም ይህን እውነታ በጽሑፍ መጠይቅ አማካኝነት ተማሪዎች ይህንን ጥያቄ ተጠይቀው ሁልጊዜ እንደሚያስተዋውቋቸው ምላሽ የሰጡ መሆኑንና መምህራንም በቃለመጠይቅ አማካኝነት የዕለቱን ትምህርት ርዕስ በሚገባ እንደሚያስተዋውቁና ዝግጁ እንዲሆኑ የሚያደርጓቸው መሆኑን ከመምህራኑ በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 4፡መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የዕለቱን የትምህርት ርዕስከ ማስተዋወቅና አላማውን በግልጽ ከማብራራት አንጻር ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| 3. | መምህራችሁ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ የትምህርቱን አላማ በግልጽ ያብራራሉ? | ሁል ጊዜ (5) | 60 | 75 |
| | | በአብዛኛው (4) | 12 | 15 |
| | | አንዳንድጊዜ (3) | 4 | 5 |
| | | አልፎ አልፎ(2) | 4 | 5 |
| | | በጭራሽ (1) | - | - |
| 1. | መምህራችሁ በቂ ዝግጅት በማድረግ ሰዋስውን ለምሳሌ፡-ቃላትን፣ ሀረጋትን፣ የቃል ክፍሎችን፣ ወዘተ. በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከመጻፍ ጋር በማጣመር (በማቀናጀት) ያስተምራሉ? | ሁል ጊዜ (5) | - | - |
| | | በአብዛኛው (4) | - | - |
| | | አንዳንድጊዜ (3) | 4 | 5 |
| | | አልፎ አልፎ(2) | 14 | 17.5 |
| | | በጭራሽ (1) | 62 | 77.5 |
| 6. | መምህራችሁ ሰዋስውን ሲያስተምሩ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ዓረፍተነገሮችን በመጠቀም የተለያዩ ምሳሌዎችን በመስጠት ያስተምራሉ? | ሁል ጊዜ | 6 | 7.5 |
| | | በአብዛኛው | 24 | 30 |
| | | አንዳንድ ጊዜ | 34 | 42.5 |
| | | አልፎ አልፎ | 16 | 20 |
| | | በጭራሽ | - | - |

እንደሚታወቀው የመማር ማስተማሩ ሂደት የሚጀምረው የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅና አላማውን በግልፅ በማብራራት እንደሆነ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡በመሆኑም ከዚህ በላይ የቀረበው ሠንጠረዥ እንደሚያመለክተው ተጠኚ መምህራን በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ የትምህርቱን ዓላማ በግልጽ ማብራራታቸውን ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይኸውም 60

(75)ተማሪዎች‹‹ሁልጊዜ››በግልጽ ማብራራታቸውን መረጃ የሰጡና አብዛኛውን ቁጥር የያዙ ናቸው፡፡ሌሎች 12 (15) ተማሪዎች‹‹በአብዛኛው››፣4 (5)ተማሪዎች ደግሞ ‹‹አንዳንድ ጊዜ›› እና‹‹አልፎ አልፎ››በማለት ምላሽ የሰጡ ሲሆን‹‹በጭራሽ››ብለው የመለሱ ተማሪዎች የሉም፡፡ ይህ ደግሞ መምህራኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ ርዕሱን በማስተዋወቅ እና የትምህርቱን አላማም በግልጽ በማብራራት ማስተማራቸውን የሚያስገነዝብ በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ይሁን እንጂ በምልከታ የተገኘው መረጃ የተጠኚ መምህራኑን ጠንካራ ጎን የሚያሳይ ቢሆንም ከተመረጡት 80 ተማሪዎች 20 (25)ቱ መምህራቸው የዕለቱን የትምህርት ርዕስ በማስተዋወቅ የትምህርቱን ዓላማ በግልጽ ማብራራታቸውን‹‹በአብዛኛው››፤ ‹‹አንዳንድ ጊዜ›› እና ‹‹አልፎ አልፎ›› የሚል ምላሽ የሰጡት (የመረጡት) መምህርቷ በክፍል ውስጥሲያስተምሩ የዕለቱን ትምህርት ርዕስ ቢያስተዋውቁም ዘወትር በግልጽ የማብራራታቸው ሁኔታ ቀጣይነት (ተከታታይነት) የሌለው እንደሆነ ተማሪዎቹ ለረጅም ጊዜ ካስተዋሉትና ከልምዳቸው በመነሳት የሰጡት ምላሽ መሆኑን ከጽሑፍመጠይቅ በተገኘው መረጃ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በሌላ በኩል መምህራን በቂ ዝግጅት በማድረግ እንደ ቃላት፣ሀረጋት፣የቃል ክፍሎች፣ የመሳሰሉትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ (ሲያስተምሩ) ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው ማስተማር አለማስተማራቸውን ከተማሪዎች በተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ የጽሑፍመጠይቁን ከሞሉት 80 ተጠኚ ተማሪዎች መካከል 4(5) ‹‹ አንዳንድ ጊዜ››ያስተምራሉ ሲሉ፣14 (17.5)‹‹አልፎ አልፎ››በቅንጅት እንደሚያስተምሯቸው፣62 (77.5) ያህሉ ተማሪዎች ደግሞ መምህራቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ በጭራሽ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው (አጣምረው) እንደማያስተምሯቸው ገልጸዋል፡፡ ይልቁንም መምህርቷ ይበልጡን ክፍለ ጊዜ በገለጻ ብቻ እንደሚያስተምሯቸው መረጃው ያሳያል፡፡ይሁንና አነስተኛውን ቁጥር የያዙት ማለትም 18(22.5) ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ መምህራቸው በተከታታይነት (ሁልጊዜ) ባይሆንም በተወሰነ መልኩ አልፎ አልፎ በቅንጅት የሚያስተምሯቸው መሆኑን ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም ለመምህርቷ ቃለመጠይቅ የቀረበላቸው ሲሆን ይኸውም‹‹የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ መዋቅር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣መናገር፣ማንበብና መጻፍ) ጋር አቀናጅተው ያቀርባሉ? 1.በቅንጅት አስተምራለሁ፤2. በተናጠል(በገለጻ) ብቻ አስተምራለሁ፤››የሚል የምርጫ ጥያቄ ቀርቦላቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

ከመምህርቷ የተገኘው መረጃም የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ በቂ ዝግጅት አድርገው እንደሚያቀርቡ ሲገልጹ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅተው ወይም በተናጠል ማስተማራቸውን ለተጠየቁት ጥያቄ አብዛኛውን በተናጠል (በገለጻ ብቻ) የሚያስተምሩ ሲሆን አልፎ አልፎ በቅንጅት የሚያስተምሩ መሆኑን መረጃ ሰጥተዋል፡፡ሁልጊዜ የማያስተምሩበትን ምክንያት ሲገልጹ በቂ ሰዓት ስለሌለ እና ተማሪዎቹም በቡድን ወይም በጥንድ ተወያይተው የደረሱበትን ማስታወሻ በመጻፍ እንዲናገሩ እድል ቢሰጣቸውም በተማሪዎቹ ፊት ቆመው በታላሚው ቋንቋ ለመናገር ወይም ለማንበብ ፍቃደኛ ባለመሆናቸው ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡ይህ ደግሞ የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር እንዳይረዱ ስለሚያደርግ ተግባቦት እንዳይዳብር እና የመማር ማስተማሩ ሂደት እንዲደናቀፍ የሚያደርግ መሆኑ ተስተውሏል፡፡

***ሠንጠረዥ 5፡መምህርቷ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ ቃላትን ሀረጋትንና ዓረፍተ ነገሮችን በምሳሌነት የማስተማር ሁኔታን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ***

| ተ.ቁ. | የምልከታ ጥያቄዎች | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 4. | መምህርቷ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ ቃላትን፣ ሀረጋትንና ዓረፍተነገሮችን በምሳሌነት የማስተማሩ ሁኔታ ምን ይመስላል? | እጅግ በጣም ጥሩ(4) | 1 |
| | | በጣም ጥሩ (3) | 1 |
| | | በመጠኑ (2) | - |
| | | በጭራሽ (1) | - |
| 7. | መምህርቷ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ መዋቅር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት (በማጣመር) የማስተማሩ (የማቅረቡ) ሁኔታ ምን ይመስላል? | እጅግ በጣም ጥሩ | - |
| | | በጣም ጥሩ | - |
| | | በመጠኑ | 1 |
| | | በጭራሽ | 1 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት ተጠኚ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ ቃላትን፣ሀረጋትን፣ዓረፍተነገሮችን በምሳሌነት እያቀረቡ የማስተማሩ ሁኔታ 1(አንድ) መምህርት እጅግ በጣም ጥሩ በሆነ መንገድ የተለያዩ ቃላትን፣ሀረጋትን፣ወዘተ.በምሳሌነት በመስጠት የሚያስተምሩ ሲሆን፣

1(አንድ)መምህርት ደግሞ በጣም ጥሩ በሆነ መንገድ ማስተማራቸውን ለማየት ተችሏል፡፡ ሁለቱም ተተኳሪ መምህራን በተወሰነ ነገር ቢለያዩም ምሳሌዎችን በመስጠት ተማሪዎቻቸው ትምህርቱን እንዲረዱ ለማድረግ ትልቅ ጥረት ማድረጋቸውን ከምልከታው ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይህ ደግሞ የመምህራኑን ጠንካራ ጎንየሚያሳይ በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

በሌላ በኩል የቋንቋውን ሰዋስዋዊ መዋቅር ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች (ማዳመጥ፣ መናገር፣ ማንበብ እና መጻፍ)ጋር አቀናጅቶ የማስተማሩ ሁኔታ ሲታይ1(አንድ)መምህርት የሰዋስው ትምህርቱን አዳምጠው እንዲናገሩ፣ የጻፉትን እንዲያነቡ የማድረጉ ሁኔታ ሙሉ በሙሉ ባይከናወንም ‹‹በመጠኑ›› ያከናወኑ ሲሆን፣1(አንድ) መምህርት ደግሞ እራሳቸው በገለጻ ብቻ የሚያብራሩ በመሆኑ አቀናጅቶ የማስተማሩ ሁኔታ በጭራሽ አለመታየቱን ከምልከታው በተገኘው መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡በተጨማሪም ይህ እውነታ ማለትም ሰዋስዋዊ መዋቅሩን ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ የማስተማሩ ሁኔታ ተዘውታሪ አለመሆኑ በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች በተገኘው ምላሽ እና በቃለመጠይቅ አማካኝነት ከተጠኚ የቋንቋ መምህራን በተገኘው መረጃ ተረጋግጧል፡፡ይህ ተግባር በቀጣይነት ባለመከናወኑ ደግሞ ተማሪዎቹ ብቁ እንዳይሆኑና በራሳቸው እንዳይተማመኑ ከማድረጉም ባሻገር ተግባቦትን እንዳያዳብሩ እንቅፋት እንደሚሆንባቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

## 4.2.2. ተማሪዎች ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነት እና ፍላጎትን በተመለከተ

**ሠንጠረዥ 6፡የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተማሪዎች ተነሳሽነትና ፍላጎት እንዲኖራቸው ከማድረግ አንጻር ከምልከታ የተገኘው መረጃ**

| ተ.ቁ. | የምልከታ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 2. | መምህርቷ በክፍል ውስጥ የሚያቀርቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተማሪዎች ተነሳሽነትና ፍላጎት ኖሯቸው እንዲማሩ ያደርጋል? እንዲማሩ ያደርጋል እእደቸ ያደርጋል የማድረጉ ሁኔታ ምን ይመስላል? | እጅግ በጣም ጥሩ | - |
| | | በጣም ጥሩ | 1 |
| | | በመጠኑ | 1 |
| | | በጭራሽ | - |

በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት የሚቀርበው የሰዋስው ትምህርት ይዘት ተማሪዎች ተነሳሽነትና ፍላጎት ኖሯቸው እንዲማሩ ከማድረጉ አንጻር ሲታይ በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች ማለትም በድሬ ጅቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩት የአማርኛ

ቋንቋ መምህርት የሚያቀርቡት ይዘት ተማሪዎቻቸውን የሚያነሳሳና ፍላጎታቸው እንዲጨምር የማድረጉ ሁኔታ‹‹በጣም ጥሩ››መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ምክንያቱም በድሬ ጅቦ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩት ተማሪዎች በአካባቢያቸው የአማርኛ ቋንቋ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ስላለ ለቋንቋው ተጋላጭ በመሆናቸው የሚቀርብላቸው የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ፍላጎት ኖሯቸው እንዲማሩ ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ተስተውሏል፡፡

በአንጻሩ ደግሞ በአባገዳ ትምህርት ቤት የሚያስተምሩ መምህርት ደግሞ የሚያቀርቡት የሰዋስው ትምህርት ይዘት የተማሪዎችን ተነሳሽነትና ፍላጎት እንዲጨምር ከማድረጉ አኳያ ‹‹በመጠኑ›› መሆኑን ያመለክታል፡፡ይኸውም በአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች ለታላሚው ቋንቋ ተጋላጭ ባለመሆናቸው መምህርቷ የሰዋስው ትምህርቱን ሲያቀርቡ የተማሪዎቹ ፍላጎት እንዲጨምር ጥረት ቢያደርጉም ተማሪዎቹ ለሚቀርብላቸው የትምህርት ይዘት ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት በጣም አነስተኛ መሆኑን ከምልከታ በተገኘው መረጃ እና ከመምህራኑ ቃለመጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 7፡ ተማሪዎች ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትን በተመለከተ ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ፡**

| ተ.ቁ. | ለመምህራን የቀረበ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1. | በእርሶ አመለካከት ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት ምን ይመስላል ? | በጣም ከፍተኛ (5) | - |
| | | ከፍተኛ (4) | 1 |
| | | መካከለኛ (3) | 1 |
| | | ዝቅተኛ (2) | - |
| | | በጣም ዝቅተኛ (1) | - |

ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት ምን እንደሚመስል 1 (አንድ) መምህርት ከፍተኛ ተነሳሽነትና ፍላጎት አላቸው ሲሉ፣ 1 (አንድ) መምህርት ደግሞ መካከለኛ ናቸው በማለት መልሰዋል፡፡ ይህም የሰዋስው ትምህርቱን ለመማር ምንም ያህል ጉጉት ቢኖራቸውም የቋንቋው ሰዋስዋዊ መዋቅር ስለሚከብዳቸው እና የአፍመፍቻ ቋንቋቸው በታላሚው ቋንቋ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ስለሚያሳድርባቸው ለመማር ያላቸው ፍላጎትም በዚሁ ምክንያት እንደቀነሰ ከመምህራኑ የተገኘ

መረጃ ያመለክታል፡፡ በተጨማሪም ይህ እውነታ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ ለማየት ተችሏል፡፡

### 4.2.3. መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር በተመለከተ

**ሠንጠረዥ 8፡ተማሪዎችን የማበረታታትና ከተማሪዎች ጋር መልካም መስተጋብር የመፍጠር ሁኔታን በተመለከተ የተማሪዎች ምላሽ፡**

| ተ.ቁ. | ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 8. | መምህራችሁ ተማሪዎችን በማበረታታትና ከተማሪዎች ጋር መልካም መስተጋብር በመፍጠር የመማር ማስረማሩን ሂደት የተሳካ ለማድረግ ጥረት ያደርጋሉ?በትምህርቱ ላይስ ትኩረት እንድታደርጉ ያበረታቷችኋል ? | ሁልጊዜ (5) | 48 | 60 |
| | | በአብዛኛው (4) | 13 | 16.25 |
| | | አንዳንዴ (3) | 11 | 13.75 |
| | | አልፎአልፎ(2) | 8 | 10 |
| | | በጭራሽ (1) | - | - |
| 10. | መምህራችሁ የተለያዩ መልመጃዎችንና ተግባራትን በማቅረብ ቋንቋውን ተጠቅማችሁ እንድትለማመዱና እንድትተገብሩ ይረዷችኋል? | ሁል ጊዜ | - | - |
| | | በአብዛኛው | 19 | 23.75 |
| | | አንዳንድ ጊዜ | 39 | 48.75 |
| | | አልፎ አልፎ | 20 | 25 |
| | | በጭራሽ | 2 | 2.5 |

ከዚህ በላይ ካለው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው ሁለቱም ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በማበረታታት እና ከእነርሱ ጋር ጠንካራና መልካም መስተጋብር በመፍጠር የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካና ውጤታማ ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት እንደሚያደርጉ ተማሪዎቹ ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡ከተጠኚ ተማሪዎች አብዛኞቹ ማለትም 48(60)ተማሪዎች‹‹ሁልጊዜ››፣ 13(16.25)ተማሪዎች ‹‹በአብዛኛው››፣11(13.75) ተማሪዎች ‹‹አንዳንድ ጊዜ››የሚል መልስ ሲሰጡ8(10) ተማሪዎች ደግሞ‹‹አልፎ አልፎ›› እንደሚያበረታቷቸው እና ከመምህራቸው ጋርም የጠነከረ ግንኙነት እንዳላቸው ከጽሑፍ መጠይቁ የተገኘው መረጃ ያመለክታል፡፡በፍጹም አያበረታቱንም የሚል ተማሪ አልነበረም፡፡ በተጨማሪም በትምህርታቸው ላይም ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉ የሚያበረታቷቸው መሆኑን ተጠኚ ተማሪዎች ምላሻቸውን የሰጡ ሲሆን ይህ ደግሞ የተጠኚ መምህራን ጠንካራ ጎን በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው ፡፡

በሌላ በኩል መምህራቸው የተለያዩ መልመጃዎችንና ተግባራትን በማቅረብ ቋንቋውን ተጠቅመው እንዲለማመዱና እንዲተገብሩ የማድረጋቸውን ሁኔታ ሲጠየቁ ተጠኚ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ 19(23.75)ተማሪዎች‹‹በአብዛኛው››፣39(48.75)ተማሪዎች ‹‹አንዳንድ ጊዜ››፣

20(25) ተማሪዎች ደግሞ‹‹አልፎ አልፎ››የተለያዩ ተግባራትንና መልመጃዎችን ቋንቋውን ተጠቅመው እንዲለማመዱና እንዲተገብሩ የሚረዷቸው መሆኑን ሲገልጹ፣2 (2.5) ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ እንዲለማመዱና መልመጃዎችንም እንዲሰሩ የማይረዷቸው መሆኑን ከጽሑፍ መጠይቁ ለማወቅ ተችሏል፡፡በተጨማሪም‹‹ሁልጊዜ›› የሚለውን ምርጫ የመረጠ ተማሪ አልነበረም፡፡ምክንያቱም መምህርቷ በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘቱን አብዛኛውን ጊዜ እራሳቸው በገለጻ መልክ የሚያብራሩ በመሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ ለማየት ተችሏል፡፡ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ ለተተኳሪ መምህራን ቃለመጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ይኸውም‹‹ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ ሰዋስዋዊ ህግጋት ላይ ያላቸው እውቀት ምን ይመስላል？(5-በጣም ከፍተኛ4 -ከፍተኛ 3 -መካከለኛ2- ዝቅተኛ1- በጣም ዝቅተኛ)››የሚል ዝግ (የምርጫጥያቄ) ቀርቦላቸው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ከሁለቱ መምህራን1 (አንድ) መምህርት‹‹መካከለኛ›› ሲሉ፣1 (አንድ) መምህርት ደግሞ የታላሚው ቋንቋ የሰዋስው እውቀት‹‹ዝቅተኛ››እ ንደሆነ ከቃለመጠይቁ የተገኘው መረጃ አመልክቷል፡፡

**መምህርቷ ሰዋስዋዊ ስያሜዎችንና ህግጋትን ከማብራራት አንጻር ከምልከታ የተገኘ መረጃ፡**

| ተ.ቁ. | የምልከታ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 3. | መምህርቷ ሰዋስዋዊ ስያሜዎችንና ረቂቅ ሰዋስዋዊ ህግጋትን ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ ገለጻ (ማብራሪያ) ይሰጣሉ？ | እጅግ በጣም ጥሩ(4) | - |
| | | በጣም ጥሩ (3) | 2 |
| | | በመጠኑ (2) | - |
| | | በጭራሽ (1) | - |
| 6. | መምህርቷ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች መልመጃዎችን እየሰሩ እንዲለማመዱ የማበረታታቱ ሁኔታ ምን ይመስላል？ | እጅግ በጣም ጥሩ | - |
| | | በጣም ጥሩ | - |
| | | በመጠኑ | 2 |
| | | በጭራሽ | - |

የቋንቋ መምህራን ሰዋስዋዊ ስያሜዎችንና ረቂቅ ሰዋስዋዊ ህግጋትን ተማሪዎቹ በቀላሉ ተረድተው የተሰጣቸውን ተግባራት በሚገባ እንዲያከናውኑ ሊያበረታቷቸው ይገባል፡፡ ይሁንና ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው ሁለቱም ተተኳሪ መምህራን በክፍል ውስጥ ሰዋስዋዊ ስያሜዎችንና ረቂቅ ሰዋስዋዊ ህግጋትን ተማሪዎች በቀላሉ ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ የማብራራቱ ሁኔታ በጣም ጥሩ መሆኑን በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ ለማየት ተችሏል፡፡ይህ በክፍል ውስጥ የሚሰጡት ገለጻ (ማብራሪያ) መልካም ሆኖ ሳለ ተማሪዎች ማብራሪያውን ከማዳመጥ ውጭ በቡድን ወይም በጥንድ የሚተገብሩት ነገር አለመኖሩ በምልከታው ታይቷል፡፡የተለያዩ መልመጃዎችንም በመስጠት እዚያው ክፍል ውስጥ

እንዲለማመዱ የማበረታታቱ ሁኔታ እምብዛም አልታየም፡፡ይልቁንም ሙሉውን ክፍለ ጊዜ መምህርቷ ብቻ ገለጻ ሲያደርጉና በማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡትን መልመጃዎችም በራሳቸው ሲሰሩ ተስተውሏል፡፡በተጨማሪም ይህንሀቅ በጽሑፍ መጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች በተገኘ ምላሽ እና በቃለመጠይቅ አማካኝነት ከመምህራኑ በተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ይህ ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን ተለማምደው በራሳቸው መተግበር እንዳይችሉ፣የራስ መተማመን ስሜት እንዳያድርባቸው እንዲሁም ሰዋስዋዊ ስያሜዎችንና ረቂቅ ሰዋስዋዊ ህግጋትን በቀላሉ እንዳይረዱ እንቅፋት ይሆንባቸዋል፡፡

## 4.2.4. የመምህራን የመርጃ መሳሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ

**ሠንጠረዥ 9፡ መምህራን መርጃ መሳሪያዎችን በመጠቀም ማስተማራቸውን በተመለከተ ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ፡**

| ተ.ቁ. | ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 4. | መምህራችሁ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የዕለቱን ትምህርት ተጨባጭና አይረሴ ለማድረግ መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ስእል፣ ምንባብ፣ ሠንጠረዥ፣ የመሳሰሉትን ይጠቀማሉ？ | ሁል ጊዜ (5) | - | - |
| | | በአብዛኛው (4) | 25 | 31.25 |
| | | አንዳንድ ጊዜ (3) | 30 | 37.5 |
| | | አልፎ አልፎ (2) | 23 | 28.75 |
| | | በጭራሽ (1) | 2 | 2.5 |

የዕለቱን የትምህርት ርዕስ ተጨባጭና አይረሴ ለማድረግ እንዲሁም ተማሪዎቹ የተማሩትን በቀላሉ ማስረጽ እንዲችሉ የሚያግዛቸው መሆኑን የቋንቋ ምሁራን ያስረዳሉ፡፡ ይሁንና ከዚህ በላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው ተጠኚ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የዕለቱን ትምህርት ተጨባጭ እና አይረሴ ለማድረግ አጋዥ (መርጃ) መሳሪያዎችን የመጠቀም ሁኔታ በተመለከተ በጽሑፍ መጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ 25 (31.25)ተማሪዎች ‹‹በአብዛኛው ይጠቀማሉ››፤30 (37.5)‹‹አንዳንድ ጊዜ ይጠቀማሉ››፤23 (28.75)ተማሪዎች ‹‹አልፎ አልፎ››የሚጠቀሙ መሆናቸውን ሲገልጹ፣2 (2.5)ተማሪዎች ደግሞ በጭራሽ እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡ይሁንና በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ የመምህራኑ የመርጃ መሳሪያ አጠቃቀምን በተመለከተ በዕለቱ

ይጠቀሙ እንጂ ዘላቂነት(ተከታታይነት) የሌለው መሆኑንና እንዲሁም ከተማሪዎቹ በተገኘውመረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሠንጠረዥ 10፡-መምህርቷ በክፍል ውስጥ መርጃ መሳሪያዎችን**

**መጠቀማቸውን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ. | የምልከታ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 5. | መምህርቷ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ሠንጠረዥ፣ ስእሎች፣ ወዘተ. ወደ ክፍል አምጥቶ የማስተማሩ ሁኔታ ምን ይመስላል? | በጣም ከፍተኛ(5) | - |
| | | ከፍተኛ (4) | - |
| | | መካከለኛ(3) | 2 |
| | | ዝቅተኛ (2) | - |
| | | በጣም ዝቅተኛ (1) | - |

ከምልከታ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው ሁለቱም ተተኳሪ መምህራንመርጃ መሳሪያዎችን የመጠቀማቸው ሁኔታ ‹‹መካከለኛ›› ደረጃ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን ይኸውም 1(አንድ) መምህርት የዕለቱን የሰዋስው ትምህርት ሲያስተምሩ በወረቀት ላይ የቃላት መደብን የሚያሳይ ሠንጠረዥ በማዘጋጀት ትምህርቱን ሲያቀርቡ እንደነበርና 1(አንድ) መምህርትም እንደዚሁ የምዕላድ አይነቶችን(ነጻና ጥገኛ ምዕላዶችን) የሚያሳይ መርጃ መሳሪያን በመጠቀም ተማሪዎችን ለማስረዳት ያደረጉት ጥረት የሚበረታታ ነው፡፡ ምክንያቱም አጋዥ መሳሪያዎችን ወደ ክፍል በማምጣት የዕለቱን ትምህርት ማስተማር ተማሪዎች ያንን የተማሩትን ርዕሰጉዳይ እንዲረዱት፣እንዲያስታውሱት እና በቶሎ ከራሳቸው ጋር እንዲያዋህዱ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና ስላለው ነው፡፡ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር Cunningsworth (1984፣50) መምህራን በክፍል ውስጥ መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ስእላዊ መግለጫዎች፣ ፍለሽ ካርድ፣ ሠንጠረዦች፣ አጫጭር ምንባቦች፣የመሳሰሉትን ሊጠቀሙ ይገባል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ መርጃ መሳሪያዎች በክፍል ውስጥ የሚቀርበውን የትምህርት ይዘት አይረሴ ለማድረግና ተማሪዎች የሚማሩትን ትምህርት በቀላሉ እንዲገነዘቡት እና እንዲያሰርጹት ለማድረግ ትልቅ አስተዋጽኦ ስለሚያበረክት ነው፡፡ ስለዚህ መምህራን በትምህርት ዝግጅት ወቅት መርጃ መሳሪያዎች ላይ ትኩረት በመስጠት መጠቀም እንደሚኖርባቸው ያስረዳሉ፡፡

በተጨማሪም ለመምህራኑ በቀረበው ቃለመጠይቅ የሰዋስው ትምህርትን ለማስተማር የመማሪያ እና የአጋዥ መጽሐፍት አቅርቦት በበቂ ሁኔታ መኖሩን እና ተተኳሪ መምህራን የዕለቱን ትምህርት ሲያቀርቡ መርጃ መሳሪያዎችን መጠቀማቸውን ተጠይቀው ሁለቱም መምህራን

የሰጡት ምላሽ በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት (Curriculum) መለወጥ ጋር በተያያዘ የመማሪያ መጽሐፍ እጥረት እንዳለ እና የአጋዥ መጽሐፍት አቅርቦትም በጣም አናሳ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡ምክንያቱን ሲገልጹ መማሪያ መጽሐፉ አዲስ እንደመሆኑ መጠን ለእያንዳንዱ ተማሪ በነፍስ ወከፍ ያልተዳረሰ ሲሆን የአጋዥ መጽሐፍት አቅርቦትን በተመለከተ የትምህርት ቤቱ ማህበረሰብ ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከት በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በቂ መጽሐፍ በግዢ መልክ እንዲቀርብ አያደርጉም፡፡ይህ ደግሞ በመማር ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እንዲያደርስ አድርጓል በማለት መልስ ሰጥተዋል፡፡ይሁንና ተጠኚ መምህራን መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ሠንጠረዥ፣ ስእላዊ መግለጫ፣ምንባቦችን፣ ወዘተ.በተከታታይነት ባይሆንም በተቻለ መጠን በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች በማዘጋጀት ወደ ክፍል በማምጣት የሚያስተምሩ መሆኑን ከቃለመጠይቁ ለመረዳት ተችሏል፡፡

## 4.2.5.ማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ የሰዋስው ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብን በተመለከተ

**ሠንጠረዥ 11፡-መምህርቷ ወደ ክፍል ይዘው የሚመጡት የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማራኪና ሳቢ በሆነ መልኩ ማቅረባቸውን በተመለከተ ከተማሪዎች**

**የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ፡**

| ተ.ቁ. | ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 7. | መምህራችሁ በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ ይዘው የሚመጡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘት (ርዕስ) ማራኪና አስደሳች በሆነ መልኩ ያቀርቡላችኋል? | ሁል ጊዜ (5) | 10 | 12.5 |
| | | በአብዛኛው(4) | 11 | 13.75 |
| | | አንዳንድ ጊዜ (3) | 28 | 35 |
| | | አልፎ አልፎ (2) | 28 | 35 |
| | | በጭራሽ (1) | 3 | 3.75 |

መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት የቋንቋ ይዘቱን መዋቅርና ስለሚያካትታቸው ይዘቶች ማወቅ ይኖርባቸዋል፡፡ምክንያቱም አንዳንድ የሰዋስው መዋቅሮች ከተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ጋር የሚመሳሰሉና በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉ ሲሆን አንዳንዶቹ ደግሞ ሙሉ በሙሉ የተለያዩና ተማሪዎቹ ቶሎ ሊገነዘቧቸው የማይችሉ ናቸው፡፡ስለዚህ የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርቱን ከማቅረባቸው በፊት በቂ ጊዜ ወስደው

በመዘጋጀትማራኪና አስደሳች የሆነ ርዕስ በክፍል ውስጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል(Ur፣ 1988)። ይሁንና ከሠንጠረዡ መረዳት እንደሚቻለው መምህርቷ ሊያስተምሩ ወደ ክፍል ይዘው የሚመጡትን የሰዋስው ትምህርት ይዘት ማራኪና አስደሳች በሆነ መልኩ የማቅረባቸውን ሁኔታ በጽሑፍ መጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች የተገኘው መረጃ አብዛኞቹ ተማሪዎች ማለትም 28(35) ‹‹አንዳንድ ጊዜ›› እና ‹‹አልፎ አልፎ›› አስደሳችና ማራኪ አድርገው ማቅረባቸውን የገለጹ ሲሆን 11(13.75) ተማሪዎች ‹‹በአብዛኛው››፣10(12.5) ተማሪዎች ‹‹ሁልጊዜ›› ሲሉ፣ 3(3.75) ተማሪዎች ደግሞ‹‹በጭራሽ››ይዘቱማራኪና አስደሳች ሆኖየማይቀርብ መሆኑን ከጽሑፍመጠይቁ መመልከት ተችሏል።በተጨማሪም ለተጠኚ መምህራን የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ተጠቅመው ትምህርቱን ማራኪና ሳቢ አድርገው ማቅረባቸውን በተደረገላቸው ቃለመጠይቅ አማካኝነት የሰጡት ምላሽ ‹‹አብዛኛውን ጊዜ የምጠቀመው ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ (ከንጥል ወደ ጥቅል) እያብራራሁ አስተምራለሁ እንጂ ሌሎች ዘዴዎችን ተጠቅሜ አላውቅም።ምክንያቱም አጠቃላይ የቋንቋውን መዋቅር ገልጬላቸው ሌላውን በራሳቸው እንዲተገብሩት ባደርግ ጊዜ ማጥፋት እንጂ ተማሪዎች ፈቃደኛ አይሆኑም። ››በማለት ምላሻቸውን ሰጥተዋል።

**ሠንጠረዥ 12፡- የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም የሰዋስው ትምህርቱን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብን በተመለከተ ከክፍል ምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ. | የምልከታ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 9. | መምህርቷ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን በመጠቀም ትምህርቱን ማራኪና ሳቢ አድርገው የማቅረባቸው ሁኔታ ምን ይመስላል ? | እጅግ በጣም ጥሩ(4) | - |
| | | በጣም ጥሩ (3) | - |
| | | በመጠኑ (2) | 2 |
| | | በጭራሽ (1) | - |

እንደሚታወቀው የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ማለትም እንደ ሂደት ተኮር፣ ውጤት ተኮር፣ ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር፣ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ፣ የመሳሰሉትን በመጠቀም ይዘቱን ሳቢና ማራኪ አድርጎ ማቅረብ ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርቱን በሚገባ እንዲገነዘቡት እና ተግባቦትን እንዲያዳብሩ ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል። ይሁን እንጂ ከላይ ከቀረበው ሠንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ የተገኘው መረጃ ሁለቱም

ተተኳሪ መምህራንየዕለቱን ትምህርት ‹‹በመጠኑ›› ሳቢና ማራኪ አድርገው ለማቅረብ የተጠቀሙት የቋንቋ ምሁራን ካስቀመጧቸው የሰዋስው ትምህርት ማስተማሪያ ዘዴዎች ውስጥ በአንዱ ማለትም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በገለጻ መልክ ብቻ ሲያስተምሩ ታይተዋል፡፡ ይሁንና በ40 ደቂቃ ውስጥሁሉንም የማስተማሪያ ዘዴዎች በመጠቀም ሊያስተምሩ ይገባል ለማለት ባይቻልም በተቻለ መጠን ተማሪዎችን ማሳተፍ በሚችል መንገድ ተማሪዎቹ በሂደት ተግባቦት ላይ እንዲደርሱ ለማድረግ ተጠኚ መምህራኑ ብዙም ጥረት ሲያደርጉ አልታዩም፡፡ በቃለመጠይቅ አማካኝነት ከመምህራኑ በተገኘ መረጃ መሰረት ሁለቱም መምህራን የሰጡት ምላሽ አብዛኛውን ጊዜ በክፍል ውስጥ የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ዘዴ ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በገለጻ መልክ የሚያስተምሩ እና እነዚህን ዘዴዎች የማይጠቀሙ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ በውይይት መልክ የማያስተምሩበትን ምክንያት ሲገልጹ የጊዜ እጥረት፣የመማሪያ መጽሐፍ በወቅቱ አለመቅረብ፣ ወዘተ. ችግሮች እንዳሉ ከቃለመጠይቁ በተገኘው መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ የሰዋስው ትምህርቱን አስደሳች አድርጎ ለማቅረብ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር መሆኑ ለመመልከት ተችሏል፡፡ በተጨማሪም የታለመው ዓላማ ከግብ እንዳይደርስ ትልቅ እንቅፋት እንደሚሆን በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.2.6. የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን በመጠቀም የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን በተመለከተ

**ሠንጠረዥ13፡- መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ሲያስተምሩ የምጋቤ ምላሽ አሰጣጣቸውን በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ፡**

| ተ.ቁ. | ለተማሪዎች የቀረቡ ጥያቄዎች | አማራጮች | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 5. | በሰዋስው ትምህርት ሂደት እናንተ ለምትፈጽሟቸው ስህተቶች መምህራችሁ ወዲያው ምጋቤ ምላሽ ይሰጧችኋል? | ሁል ጊዜ (5) | - | - |
| | | በአብዛኛው (4) | 9 | 11.25 |
| | | አንዳንድ ጊዜ (3) | 21 | 26.25 |
| | | አልፎ አልፎ (2) | 26 | 32.5 |
| | | በጭራሽ (1) | 24 | 30 |
| 11. | መምህራችሁ በጽሑፍ የሚመለሱ አጫጭር ተግባራትን በክፍል ውስጥ እንድታከናውኑ (እንድትተገብሩ) ያደርጋሉ? እርማትስ ይሰጧችኋል? | ሁል ጊዜ | 2 | 2.5 |
| | | በአብዛኛው | 10 | 12.5 |
| | | አንዳንድ ጊዜ | 25 | 31.25 |
| | | አልፎ አልፎ | 35 | 43.75 |
| | | በጭራሽ | 8 | 10 |

መምህራን በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርትን ሲያስተምሩ ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን በመስጠት እንዲተገብሩ በማድረግና ለሚፈጽሟቸው ስህተቶችም ወዲያው ምጋቤምላሽ መስጠት ተማሪዎች ስህተታቸው የቱ ጋር እንደሆነ ማወቅ እንዲችሉና በራሳቸው እንዲተማመኑ ለማድረግ የሚያስችላቸው መሆኑ ይታመናል፡፡በመሆኑም ተማሪዎቹ ለሚፈጽሙት ሰዋስዋዊ ስህተቶች መምህራቸው ወዲያው ምጋቤ ምላሽ (ግብረመልስ) የሚሰጧቸው መሆኑን ተጠይቀው ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ይኸውም 9(11.25) ተማሪዎች ‹‹በአብዛኛው››ምጋቤ ምላሽ ይሰጡናል ሲሉ፣ 21(26.25) ተማሪዎች ‹‹አንዳንድ ጊዜ››፣26(32.5) ተማሪዎች ‹‹አልፎ አልፎ›› ይሰጡናል ብለው የመለሱ ሲሆን 24(30) ተማሪዎች በጭራሽ ምጋቤ ምላሽ አይሰጡንም ሲሉ ‹‹ሁልጊዜ›› ብለው የመለሱ ተማሪዎች አልነበሩም፡፡

በሌላ በኩል በክፍል ውስጥ በጽሑፍ የሚመለሱ አጫጭር ተግባራትን እንዲተገብሩ ማድረግና እርማት መስጠትን በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ ምላሽ 2(2.5) ተማሪዎች ‹‹ሁልጊዜ››፣ 10(12.5) ተማሪዎች ‹‹በአብዛኛው››፣ 25(31.25) ተማሪዎች ደግሞ ‹‹አንዳንድ ጊዜ›› ይሰጣሉ ብለው የመለሱ ሲሆን ይበልጡን ቁጥር የያዙ መላሾች ማለትም 35(43.75) ተማሪዎች ‹‹አልፎ አልፎ›› ይሰጡናል ሲሉ 8(10) በጭራሽ አይሰጡንም የሚል ምላሽ ሰጥተዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 14፡-የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎችን ተጠቅሞ ማስተማርን በተመለከተ ከመምህራን ቃለመጠይቅ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ. | ለመምህራን የቀረበ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 4. | እርሶ ሰዋስውን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ የሰዋስው አቀራረብ ደረጃዎች ማለትም የአቅርቦት ደረጃ፣ የልምምድ፣ የአፍልቆት እና የግብረመልስ (ምጋቤ ምላሽ) ደረጃ በመጠቀም ተማሪዎችን ያስተምራሉ? | ሁልጊዜ | - |
| | | በመጠኑ | - |
| | | አንዳንድ ጊዜ | 1 |
| | | በጭራሽ | 1 |
| 8. | ሰዋስውን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶችለማረም ማስታወሻ በመያዝ በየደረጃዎቹ ምጋቤ ምላሽ ይሰጣሉ? | ሁልጊዜ | |
| | | በአብዛኛው | - |
| | | አልፎአልፎ | 2 |
| | | በጭራሽ | - |

መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የአቀራረብ ደረጃዎችን ማለትም የአቅርቦት፣ የልምምድ፣የአፍልቆትና የምጋቤ ምላሽ (የግብረ መልስ) ደረጃዎችን በሚገባ ተገንዝበው አቅማቸው በሚፈቅደው መጠን በመጠቀም የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ለተማሪዎች ማቅረብ እንዳለባቸው Celce-Murcia (1991) ይገልጻሉ፡፡ነገር ግን ተተኳሪ መምህራን ሰዋስውን በክፍል ውስጥ ሲያስተምሩ እነዚህን የአቀራረብ ደረጃዎች በመጠቀም ተማሪዎቻቸውን ማስተማራቸውን ሲጠየቁ 1(አንድ) መምህርት ‹‹አንዳንድ ጊዜ እጠቀማለሁ››ሲሉ 1(አንድ) መምህርት ደግሞ ‹‹በጭራሽ በደረጃ ከፋፍዬ አስተምሬ አላውቅም›› በማለት ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሰዋስውን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ተማሪዎች ለሚፈጽሟቸው ስህተቶች ማስታወሻ በመያዝ በየደረጃዎቹ ምጋቤ ምላሽ መስጠታቸውን ሲጠየቁ ሁለቱም መምህራን ‹‹አልፎ አልፎ›› የሚሰጡ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ሁልጊዜ እያንዳንዱ ተማሪ ለሚፈጽመው ስህተት ማስታወሻ በመያዝ ምጋቤምላሽ ለመስጠት የክፍለጊዜ እጥረት መኖር፣ የተማሪ ቁጥር መብዛትን፣ ወዘተ. እንደምክንያት ገልጸዋል፡፡ይሁንና ይህንን እውነታ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ ሁለቱም የተማሪዎችን ስህተት ለማረም ማስታወሻ በመያዝ ግብረ መልስ (ምጋቤ ምላሽ) ሲሰጡ አልታዩም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መምህራኑ የሚሰጡት ምጋቤምላሽ ሁሉንም ተማሪዎች ማዕከል ያደረገ አለመሆኑ በጽሑፍ መጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች በተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ትክክለኛ ሰዋስዋዊ መዋቅር በሚገባ እንዳይረዱ ከማድረጉም በላይ በራሳቸው እንዳይተማመኑ አሉታዊ ተጽዕኖ ይፈጥርባቸዋል፡፡

**ሠንጠረዥ 15፦ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች በየደረጃ ምጋቤ ምላሽ መስጠትን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ፡**

| ተ.ቁ | የምልከታ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 8. | መምህርቷ ሰዋስውን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ተማሪዎች የሚፈጽሟቸውን ሰዋስዋዊ ስህተቶች በየደረጃው ማስታወሻ በመያዝ ምጋቤ ምላሽ የመስጠቱ ሁኔታ ምን ይመስላል? | እጅግ በጣም ጥሩ (4) | - |
| | | በጣም ጥሩ (3) | - |
| | | በመጠኑ (2) | 1 |
| | | በጭራሽ (1) | 1 |

ከዚህ በላይ የቀረበው ሰንጠረዥ የሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራን በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የሰዋስው አቀራረብ ደረጃዎችን (የአቅርቦት፣ የልምምድ፣ የአፍልቆት እና የምጋቤምላሽ ደረጃዎች) ተጠቅመው ሲያስተምሩም ሆነ ማስታወሻ በመያዝ ምጋቤምላሽ (እርማት) ሲሰጡ አለመታየቱ ነው፡፡ከሁለቱመምህራን 1(አንድ) መምህርት ማስታወሻ ሳይዙ ተግባቦቱን (ትግበራውን) በማቋረጥ በተወሰነ መልኩ ምጋቤምላሽ የሰጡ ሲሆን 1(አንድ) ደግሞ የዕለቱን ትምህርት በገለጻ መልክ አስተምረው ከጨረሱ በኋላ ምንም አይነት ምጋቤምላሽ ሳይሰጡ እንዳጠናቀቁ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ ተረጋግጧል፡፡ በተጨማሪም ይህን እውነታ በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት ከተማሪዎች በተገኘ መረጃ እና በቃለመጠይቅ አማካኝነት በሠንጠረዥ አስራ አምስት ስር በተገለጹት ችግሮች ማለትም የክፍለጊዜ እጥረት፣ የተማሪዎች ቁጥር መብዛት፣ ወዘተ. ምክንያትወጥነት ባለው መንገድ ምጋቤምላሽ መስጠት ያልተቻለ መሆኑን ከመምህራን በተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.2.7. የማስተማሪያ ስልቶችን በተመለከተ

**ሠንጠረዥ 16፡ የማስተማሪያ ስልቶችን በመጠቀም ማስተማርን በተመለከተ ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ፡**

| ተ.ቁ. | ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 2. | መምህራችሁ በክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በሚና ጨዋታ፣ በምልልስ፣ ወዘተ.በመጠቀምእንድትለማመዱ ያደርጓችኋል? | ሁልጊዜ (5) | 1 | 1.25 |
| | | በአብዛኛው (4) | 1 | 1.25 |
| | | አንዳንድ ጊዜ (3) | 8 | 10 |
| | | አልፎአልፎ (2) | 9 | 11.25 |
| | | በጭራሽ (1) | 61 | 76.25 |

መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የማስተማሪያ ስልቶችን እንደምልልስ፣ሚናጨዋታ፣ማሳየት፣ወዘተ. በመጠቀም ተማሪዎቻቸው እንዲለማመዱ እና ጥሩ የሆነ መስተጋብርን በመፍጠር ተግባቦት እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸው መሆኑን Ur (1988) ገልጸዋል፡፡ በመሆኑም እነዚህን የማስተማሪያ ስልቶች ተተኳሪ መምህራን የመጠቀማቸውን ሁኔታ ከጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ 1 (1.25) ተማሪ ‹‹ሁልጊዜ››፣ 1 (1.25)

ተማሪደግሞ ‹‹በአብዛኛው›› በማለት የመለሰ ሲሆን ይህም በጣም ዝቅተኛ ቁጥር (አሃዝ) የያዘነው፡፡8 (10) ተማሪዎች ‹‹አንዳንድጊዜ›› እና 9 (11.25) ደግሞ ‹አልፎ አልፎ›› የሚል ምላሽ ሲሰጡ አብላጫውን ቁጥር የያዙ 61 (76.25) ተማሪዎች ‹‹በጭራሽ›› በእነዚህ ስልቶች እንደማይጠቀሙ ገልጸዋል፡፡በተጨማሪም ለተማሪዎቹ ክፍት ወይም ልቅ (ማብራሪያየሚፈልግ ጥያቄ) ቀርቦላቸዋል፡፡ ይህም ጥያቄ ‹‹የሰዋስው ትምህርትን ስትማር/ሪ የሚያጋጥሙህን/ ሽን ተግዳሮቶች (ችግሮች) አብራራ/ሪ፡፡››ለሚለው ጥያቄ የጽሑፍ መጠይቁ ከተሰጣቸው 80 ተማሪዎች መካከል 10(12.5) ‹‹ተውላጠ ስሞችን መለየት ይከብደኛል››፤8(10)‹‹ጾታአለይም››፤ 7(8.75)‹‹ነጠላና ብዙ ቁጥር መለየት ያስቸግረኛል››፤11(13.75)‹‹የቃላት፣የዓረፍተ ነገር አወቃቀር››፤3(3.75)‹‹ፊደሎችን መለየት ያስቸግረኛል››፤1(1.25)‹‹መጻፍ ናማንበብበጣም ይከብደኛል››፤14(17.5)‹‹ የቃላት መደብን መለየት ያስቸግረኛል››፤11(13.75)‹‹ነጻና ጥገኛ ምዕላድን መለየት አልችልም››፤ 9(11.25) ‹‹ጥገኛና ስርወ ቃል መጻፍ አላውቅም››ብለው ሲመልሱ 2(2.5)የእጅ ጽሑፋቸውን ለማንበብ አስቸጋሪ በመሆኑ ያልተነበበ ሲሆን4(5) ተማሪዎች ደግሞ ለዚህ ጥያቄ መልስ አልሰጡም፡፡

### 4.2.8. ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ ማድረግን በተመለከተ

**ሠንጠረዥ 17፡-ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርትን ሲማሩ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ እድል መስጠትን በተመለከተ ከተማሪዎች የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ. | ለተማሪዎች የቀረበ ጥያቄ | አማራጮች | በቁጥር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| 9. | መምህራችሁ ሀሳባችሁን በነጻነት (ሳትፈሩና ሳትጨነቁ) እንድትገልጹ እድል ይሰጧችኋል? | ሁልጊዜ (5) | - | - |
| | | በአብዛኛው (4) | 4 | 5 |
| | | አንዳንድ ጊዜ(3) | 12 | 15 |
| | | አልፎ አልፎ (2) | 20 | 25 |
| | | በጭራሽ (1) | 44 | 55 |

ከዚህ በላይ ከቀረበው ሰንጠረዥ መረዳት የሚቻለው በክፍል ውስጥ በሚደረገው ተግባቦት ላይ ተማሪዎች ሳይፈሩ፣ ሳይሸማቀቁና ሳይጨነቁ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ መምህራቸው እድል የመስጠታቸውን ሁኔታ በተመለከተ ለተማሪዎች በቀረበው የጽሑፍመጠይቅ የተገኘው ምላሽ ‹‹በአብዛኛው›› እድል ይሰጡናል ያሉት 4 (5) ተማሪዎችሲሆኑ 12 (15) ተማሪዎች ‹‹አንዳንድ ጊዜ››፤ 20 (25) ተማሪዎች ደግሞ ‹‹አልፎአልፎ›› ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ እድል እንደሚሰጧቸው ገልጸዋል፡፡ አብዛኞቹ ተማሪዎች ‹‹በጭራሽ›› ሀሳባችንን በነጻነት ለመግለጽ እድል አይሰጡንም ያሉት ደግሞ 44 (55) ተማሪዎች ሲሆኑ እነዚህ ይበልጡን ቁጥር የያዙ ናቸው፡፡ ‹‹ሁልጊዜ እድል ይሰጡናል››ብለው የመለሱ ተማሪዎች የሉም፡፡

**ሠንጠረዥ 18፡- ተማሪዎች ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ሁኔታን በተመለከተ ከምልከታ የተገኘ መረጃ**

| ተ.ቁ. | የምልከታ ጥያቄ | አማራጭ | በቁጥር |
|---|---|---|---|
| 10. | የተማሪዎች በአፍልቆት ደረጃ ሀሳባቸውን በነጻነት የመግለጽና የሰዋስው ህግጋትን የማውጣት አቅም ምን ይመስላል ? | እጅግበጣም ጥሩ | - |
| | | በጣም ጥሩ | - |
| | | በመጠኑ | - |
| | | በጭራሽ | 2 |

ከዚህ በላይ ያለው ሠንጠረዥ የሚያስረዳው ተማሪዎች በአፍልቆት ደረጃ ሀሳባቸውን በነጻነት መግለጽና የሰዋስው ህግጋትን የማውጣት አቅምን በተመለከተ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ የተገኘው መረጃ ሁለቱም ተተኳሪ መምህራን ተማሪዎቻቸው ሳይጨነቁና ሳይሸማቀቁ ሀሳባቸውን በነጻነት እንዲገልጹ እድል ሲሰጡና እንዲናገሩ ሲያበረታቷቸው አልታዩም፡፡ ይሁንእንጂ በአፍልቆት ደረጃ ተማሪዎች ታላሚውን ቋንቋ ትርጉማዊ በሆነ መንገድ ለተግባቦትና ለመልዕክት ማስተላለፊያ የሚጠቀሙበት ደረጃ በመሆኑ የሚያከናውኑትን ተግባር ተጨባጭ በሆነ አውድ ውስጥ በነጻነት ተግባቦት (መስተጋብር) የሚፈጥሩበት ነው፡፡ ስለሆነም በዚህ ደረጃ የመምህሩ/ርቷ ጣልቃገብነት አነስተኛ በመሆኑ ተማሪዎች ያለአንዳች ፍራቻና መሸማቀቅ ሀሳባቸውን በነጻነት ለመግለጽ የሚሞክሩበት በመሆኑ መምህራን የተለያዩ

መልመጃዎችን በማቅረብ የታላሚውን ሰዋስዋዊ መዋቅር በሚገባ እንዲለማመዱና የሰዋስው ህግጋትን የማውጣት አቅማቸው እንዲዳብር ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ Ur (1988) እና Celce-Murcia (1991) ያብራራሉ፡፡ በመሆኑም ተተኳሪ መምህራን ይህንን ተግባር አለመፈጸማቸው በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታና በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት በተገኘው መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡

## 4.3. የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በምዕረፍ አራት ስር የተለያዩ የመረጃ ትንታኔዎች እና መሰረታዊ ጉዳዮች ቀርበዋል፡፡ እነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮችም በቅድሚያ የጥናቱን መሰረታዊ አላማ ማለትም ‹‹የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል ትንታኔ በማስቀደም በቀጣይነትም የጥናቱ ንዑሳን አላማዎች በዝርዝር የተተነተኑበት ነበር፡፡

ጥናቱ በዋነኝነት ትኩረት ያደረገው የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነበር፡፡ይኸውም የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የትምህርት ዝግጅታቸው፣ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸውን መስተጋብር፣ የመርጃ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣ የማለማመጃ ስልቶች አጠቃቀም፣ ወዘተ. በመፈተሽ ያላቸውን ጠንካራና ደካማ ጎኖችን ለማየት ተችሏል፡፡ ከዚህ በመነሳት የጥናቱን ግኝት ማብራሪያም እንደሚከተለው ለመግለጽ ተሞክሯል፡፡

የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበርን በተመለከተ በዚህ ጥናትና በሌሎችም መሰል ጥናቶች እንዲሁም የምሁራን ገለጻ (Harmer 1987፣Stern 1992፣ Bygate,et,al. 1994፣ መሰሉ 1994፣…) ስለሰዋስው ትምህርት አቀራረብ እንዳረጋገጡት የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አቀራረብ በተማሪዎች ላይ ችግር የማይፈጥር፣ ውጤታማ፣ ተወዳጅ እና ስሜትን የሚስብ እንዲሁም የሰዋስው ትምህርቱን ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በቅንጅት በመስጠት ስርዓቱንም በማሳወቅ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የዳበረ እውቀት እንዲኖራቸው ከማድረጉም ባሻገር በቋንቋ ትምህርቱ የተማሪዎች እውቀት እያደገና እየበለጸገ ሲሄድ በቋንቋዎች መካከል ያለውን ልዩነት እየተገነዘቡ እንዲሄዱ ከፍተኛ እገዛ ያደርግላቸዋል ማለት ይቻላል፡፡

ይሁን እንጂ በዚህ ጥናት ውስጥ በትንተናው እንደታየው የቋንቋ መምህራኑ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት፡ ለምሳሌ፡- የክፍለጊዜ ማነስ፣ በቂ ግንዛቤ አለመኖር፣ የመማሪያ መጽሐፍ እጥረት፣

ወዘተ. አማካኝነት የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ አለመሆኑ፣ ማራኪና ስሜትን የሚስብ አለመሆኑ እና የተማሪዎችን ፍላጎት የማያሟላ እንዲሁም ከቋንቋ ክሂሎች ጋር ተቀናጅቶ የማይቀርብ መሆኑ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል። ይህ ደግሞ የሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ የዳበረ (የላቀ) እውቀት እንዳይኖራቸው የሚያደርግ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ምንም አይነት እገዛ የማያደርግላቸው መሆኑን ከጥናቱ የተገኘው ውጤት አመልክቷል።

በሌላ በኩል Odlin (1994) ስለሰዋስው ትምህርት አቀራረብ እንዳብራሩት ጥሩ የሰዋሰው ትምህርት የማይረሳ መሆን እንዳለበት፣ለተማሪው የሚቀርበው አዲስ ጽንሰሀሳብን የያዘ የሰዋስው ትምህርት በበቂ ማብራሪያ የተደገፈና በተማሪው አእምሮ በመስረጽ አይረሴ እንዲሆን ማድረግ መቻሉ፣ ተማሪዎቹ በትምህርት ሂደት ጥሩ ተሳታፊ እንዲሆኑ እና አዲስ የሚቀርብላቸውን የሰዋስው መዋቅር በቀላሉ እንዲያስታውሱት ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት መሆኑን ከገለጻው ለማረጋገጥ ተችሏል።

በአጠቃላይ የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር እንደትምህርቱ ውስብስብነት እና እንደተማሪው ዳራ (ማንነት) ታይቶ በተግባር ላይ የሚውል እንጂ ዝም ብሎ ከተለያዩ የአቀራረብ ስልቶች አንዱን መርጦ በዘፈቀደ መጠቀም እንዳልሆነ ከገለጻው ለመረዳት ተችሏል። ከምሁራኑ ማብራሪያ መረዳት እንደሚቻለው ዘመናዊው የሰዋስው የማስተማር ስልት በተውጣጣ አቀራረብ ወይም በቅንጅታዊ አቀራረብ ማስተማር የተሻለና ተማሪዎችን ውጤታማ የሚያደርግ መሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል። ከዚህ አንጻር የዚህ ጥናት ውጤት ከላይ ለአብነት የተጠቆሙት ምሁራን የገለጹትን ሀሳብ የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል።

በሌላ በኩል የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካና ውጤታማ እንዲሆን በሰዋስው ትምህርት ይዘት ላይ በቂ ዝግጅት ማድረግ ይገባቸዋል። ማለትም የቋንቋ ይዘቱን መዋቅርና ስለሚያካትታቸው ይዘቶች ማወቅ ይኖርባቸዋል።ምክንያቱም አንዳንድ የሰዋስው መዋቅሮች ከተማሪዎች የአፍመፍቻ ቋንቋ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸውና በቀላሉ ሊረዷቸው የሚችሉ ሲሆን አንዳንዶቹ ግን ሙሉ ለሙሉ የተለያዩ እና ተማሪዎቹ ወዲያው ሊገነዘቧቸው የማይችሉ ናቸው። ስለሆነም መምህራን የሰዋስው ትምህርትን ክፍል ውስጥ ከማቅረባቸው በፊት በቂ ጊዜ ወስደው ሊዘጋጁበት እንደሚገባ Ur (1988፣5) አብራርተዋል።

ሌላው የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ማስተማር ይኖርባቸዋል። ይህንን ሀሳብ ለማጠናከር Thornbury (1997) ተማሪዎች የሰዋስው ትምህርት ይዘቶችን ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከመጻፍ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ማቅረብ አስፈላጊ መሆኑን ይገልጻሉ።

የምሁሩ ገለጻ የሚያስረዳው መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲተገብሩ ከአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ በማቅረብ የተማሪዎችን የተግባቦት ችሎታ ለማዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ  የሚያበረክት ነው። ተማሪዎች በትግበራ ወቅት ትምህርቱን ከራሳቸው የህይወት ገጠመኝ በመነሳት ህጉን በራሳቸው ጥረት እንዲያውቁት ይደረጋል። ይህ ሲባል ተማሪዎች የተለያዩ ተግባራትን እያከናወኑ የታላሚውን ቋንቋ መዋቅራዊ ፍችና አውዳዊ አጠቃቀም ተገንዝበው በቋንቋው መጠቀም እንደሚችሉ ከማብራሪያው ለመረዳት ተችሏል። ይሁን እንጂ የጥናቱ ግኝት እንደሚያመለክተው ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ከቋንቋ ክሂሎች ጋር በማቀናጀት ተማሪዎች እያዳመጡ እንዲናገሩ፣ እያነበቡ እንዲጽፉ ከማድረግ ይልቅ በተናጠል በገለጻ ብቻ የሚያስተምሩ መሆኑን በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ፣ ከመምህራን ቃለመጠይቅና ከተማሪዎች የጽሑፍመጠይቅ በተገኘ መረጃ ለማረጋገጥ ተችሏል።በመሆኑም የዚህ ጥናት ግኝት ከላይ የቋንቋ ምሁራን ከሰጡት ማብራሪያ ጋር የማይዛመድ ሆኖ ተገኝቷል።

ሌላው በአገር ውስጥ ከተካሄዱት ጥናቶች ውስጥ አንዱ የከበደ አየለበ 1999ዓ.ም. የተጠናው ጥናት ሲሆን ዋና ትኩረቱም የሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አጠቃቀምና አተገባበር መፈተሸ ነበር።ይኸውም የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ የማስተማሪያ ብልሃቶችን እንደምልልስ፣ሚናጨዋታ፣አውድ፣የመሳሰሉትን በመጠቀም ትምህርቱን ማራኪና አስደሳች አድርገው በማቅረብ ተማሪዎቹ በታላሚው ቋንቋ የዳበረ እውቀት እንዲኖራቸውና የቋንቋውን ሰዋስዋዊ መዋቅር ተገንዝበው (ተረድተው)ጥሩ ተግባቦትን እንዲያከናውኑ ማድረግ እንዳለባቸው ጠቁሟል።ይሁን እንጂ በጥናቱ ያገኘው ውጤት ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርቱን በገለጻና አጫጭር ምሳሌዎችን በመስጠት ብቻ እንደሚያስተምሩና ከላይ የተዘረዘሩትን የማስተማሪያ ብልሃቶችን እንደማይጠቀሙ አረጋግጧል፡ ፡በተጨማሪም የትኩረት ልምምድ ደረጃን የመጠቀም ልምዳቸው አነስተኛ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል።የከበደ ጥናት የተጠቆሙት ችግሮች የታዩበት በመሆኑ ከዚህ የጥናት ውጤት ጋርየተዛመደ ሆኖ ተገኝቷል።

በአጠቃላይ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ በቂ ዝግጅት ማድረግ፣ ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ እና አሳታፊ የሆኑ መልመጃዎችን አዘጋጅቶ ማቅረብ፣ የዕለቱን ትምህርት አይረሴና ተጨባጭ ለማድረግ መርጃ (ደጋፊ) መሳሪያዎች እንደ ስዕላዊ መግለጫዎችን፣ ቻርቶችን፣ ወዘተ. መጠቀም ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ ውጤታማ እንዲሆኑና ለታቀደው ዓላማ መሳካትም ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ከቋንቋ ምሁራን ገለጻ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይሁንና የዚህ ጥናት ውጤት ከላይ የቋንቋ ምሁራን ከገለጹት ሀሳብ ጋር የማይዛመድ እና ምሁራኑ የሰጡትን ማብራሪያ የማያጠናክር ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ በቂ ዝግጅት የላቸውም፤ ተማሪዎችን የሚያሳትፉ መልመጃዎችን ሲያቀርቡ አልታዩም፤ የዕለቱን ትምህርት አይረሴና ተጨባጭ ለማድረግ መርጃ መሳሪያዎችን የመጠቀም ሁኔታቸው የተቆራረጠ እና ዘላቂነት የሌለው ማለትም ዘወትር የማይጠቀሙ መሆኑን እና የምጋቤምላሽ አሰጣጣቸውም ቢሆን ሁሉንም ተማሪዎች ያማከለ ሳይሆን ፊት ለፊት ለሚቀመጡ እና እጅ ለሚያወጡ ብቻ የሚሰጥ መሆኑን በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በመሆኑም ተተኳሪ የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ በትምህርቱ ላይ በቂ ጊዜ ወስደው ዝግጅት ቢያደርጉ፣ መርጃ መሳሪያ የዕለቱ ትምህርት የጀርባ አጥንት በመሆኑ አዘውትረው ቢጠቀሙ፣ የሰዋስው የማስተማሪያ ስልቶችን እንደምልልስ፣ ሚናጨዋታ፣ ወዘተ. ያሉትንበአግባቡ በመጠቀም ተማሪዎችን ቢያለማምዱ እንዲሁም ለተማሪዎች የሚሰጡት ምጋቤምላሽ ሁሉንም የክፍሉን ተማሪዎች ያማከለ ቢሆን፣ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር በሚገባ ተገንዝበው ጥሩ ተግባቦትን እንዲያከናውኑ ይረዳቸዋል፤ ለሰዋስው ትምህርቱ ተነሳሽ እንዲሆኑና የመማር ፍላጎታቸው እንዲጨምር ከማድረጉም በተጨማሪ በራስ የመተማመን ስሜት እንዲያድርባቸው ትልቅ አስተዋጽኦ የሚያበረክት በመሆኑ መምህራኑ ይህንን ከግምት ውስጥ በማስገባት ሊያስቡበት ይገባል፡፡

# ምዕራፍ አምስት

# ማጠቃለያ እና የመፍትሄ ሀሳቦች

## 5.1. ማጠቃለያ

አጥኚዋ ይህንን ጥናት ለማካሄድ የተነሳችበት አብይ ጉዳይ በሰሜን ሸዋ ዞን በሚገኙ ሁለት የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የ8ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አቀራረብና አተገባበርን መፈተሽ ነው። በዚህም መሰረት በምልከታ፣ በቃለመጠይቅ እና በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት የመምህራንን የትምህርት ዝግጅት፣ ተማሪዎች ለሰዋስው ትምህርት ያላቸው ተነሳሽነትና ፍላጎት፣ የሰዋስው ትምህርት አቀራረብ ደረጃዎች በመጠቀም እንዴት እንደሚያቀርቡ መፈተሽ፣ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው መስተጋብር እንዲሁም የመምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥ ምን እንደሚመስል መረጃ በመሰብሰብ ለመፈተሽ ተሞክሯል። እነዚህ የተሰበሰቡት መረጃዎች በመተንተን የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል።

1. የሰዋስው ትምህርት ይዘት ሊዳብር የሚችለው ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከመጻፍ ጋር ተቀናጅቶ ሲቀርብ ነው። ይሁን እንጂ በእነዚህ ተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ጋር አቀናጅቶ ከማቅረብ ይልቅ ይበልጡን ሰዓት ለገለጻ የሚጠቀሙ መሆኑን የጥናቱ ግኝት ያመለክታል።
2. የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ለማስተማር በቂ ዝግጅት በማድረግ እንዲሁም ተገቢነት ያለውን ይዘት ተማሪዎችን ማዕከል ያደረጉ መልመጃዎችንና ተተግባሪነት ያለውን ዓላማ በማዘጋጀት ተማሪዎች በታላሚው ቋንቋ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጭ ጥሩ ተግባቦት እንዲያከናውኑ የሚረዳቸውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት በክፍል ውስጥ ማቅረብ ይኖርባቸዋል። ነገር ግን የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሚዘጋጁበት የሰዋስው ትምህርት ይዘት ከተማሪዎች እድሜ፣ ከመጡበት ማህበረሰብ፣ ከህይወት ገጠመኞቻቸው ጋር የማይጣጣም እና የተማሪዎቹን ፍላጎት የማያነሳሳ እንዲሁም ተግባቦትን ለማዳበር የማያስችል መሆኑን ከምልከታ እና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ የተገኘው መረጃ በመምህራኑ የትምህርት አሰጣጥ ላይ ችግር እንዳለ ይጠቁማል። መምህራኑ የሚያቀርቧቸው መልመጃዎችና ምሳሌዎችም በገለጻመልክ ቋንቋውን ከማሳወቅ ውጭ

ተማሪዎች ተግባቦትን እንዲያዳብሩ የማያበረታቱ እና አሳታፊነት የጎደላቸው መሆናቸውን ከጥናቱ የተገኘው ውጤት ያመለክታል፡፡

3. በመማር ማስተማር ሂደት ለሰዋስው ትምህርት ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም የትምህርት አይነት ውጤታማነት (ስኬታማነት) የተማሪዎቹ ፍላጎት፣ ተነሳሽነትና ተሳትፎ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ይታመናል፡፡ይሁን እንጂ የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሚያስተምሯቸው የ 8ኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ቋንቋ ሰዋስውን ለመማር ያላቸው ፍላጎትና ተሳትፎ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ፣ ከመምህራን በቃለመጠይቅ የተገኙ መረጃዎችና ከተማሪዎች በጽሑፍመጠይቅ አማካኝነት የተገኙ መረጃዎች የሚጠቁሙ ሲሆን ይህ ደግሞ በሰዋስው ትምህርቱ አተገባበር ላይ ትልቅ ጫና የሚፈጥር መሆኑ በጥናቱ ውጤት ተረጋግጧል፡፡
4. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስው ተጠቅመው ልምምድ እንዲያደርጉ እንደ ምልልስ፣ ማሳየትን፣ ሚና ጨዋታን፣ በአውድ ማስተማርን፣ ወዘተ. የመማር ማስተማር ስልቶችን በመጠቀም ተግባቦትን እንዲያዳብሩ የማድረጉ ሁኔታ ዝቅተኛ እንደሆነ በክፍል ውስጥ በተደረገ ምልከታ፣ ከመምህራን ቃለመጠይቅና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በተገኙ መረጃዎች ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ደግሞ በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የተማሪዎችን ተነሳሽነት እንደሚቀንስ እና ተግባቦት ላይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚያሳድር እንደሆነ የጥናቱ ግኝት ያሳያል፡፡ ከመምህራን በቃለመጠይቅ አማካኝነት በተገኘው መረጃ መሰረት መምህራኑ የሰጡት ምላሽ የክፍለ ጊዜ እጥረት፣ በመማሪያ መጽሐፉ ውስጥ የቀረቡት መልመጃዎች አመቺ አለመሆናቸው እንዲሁም በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት የተማሪ መጽሐፍ በመቀየሩ የተማሪ መጽሐፍ እጥረት መኖር፣ የተማሪዎች ለልምምዱ ፈቃደኛ አለመሆን፣ ወዘተ. ተግዳሮት መሆናቸውን እንደ ምክንያት ገልጸዋል፡፡
5. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ተጠቅመው ተግባቦት እንዲያከናውኑ እንዲሁም መልካም የሆነ መስተጋብር እንዲፈጥሩ የሰዋስው ትምህርቱን ግልጽ፣ አሳታፊና አፍላቂ በሆነ መንገድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ በተወሰነ መልኩ ይዘቱ ግልጽነት ቢኖረውም ተማሪዎችን ግን የማያሳትፍና ለአፍልቆት የማይጋብዝ መሆኑን በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዚህ ምክንያት ተማሪዎች

ክፍል ውስጥ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ መዋቅር ተጠቅመው እርስ በእርስ ተግባቦት የሚያከናውኑበት አጋጣሚ በጣም ዝቅተኛ መሆኑን የጥናቱ ውጤት አመልክቷል፡፡

6. በክፍል ውስጥ የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሳካና ውጤታማ እንዲሆን ለማድረግ የመምህራንና የተማሪዎች መልካም የሆነ መስተጋብር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ይታመናል፡፡ በመሆኑም ተተኳሪ መምህራን ከተማሪዎቻቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት መልካም መሆኑን እና ተማሪዎቻቸውንም በተቻለ መጠን ለማበረታታት የሚያደርጉት ጥረት ከፍተኛ መሆኑን በክፍል ውስጥ ምልከታ፣ በጽሑፍ መጠይቅ ከተማሪዎች የተገኙ መረጃዎች እንዲሁም በቃለመጠይቅ አማካኝነት ከመምህራኑ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ይህ ደግሞ የመምህራኑ ጠንካራ ጎን በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡

7. የቋንቋ መምህራን የሰዋስውን መዋቅራዊ ቅርጽ፣ ፍችና አጠቃቀም በሚያስተምሩበት ጊዜ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ ያሉ አውዶችን፤ የተማሪዎችን የህይወት ገጠመኝ በመጠቀም ማስተማር ተማሪዎች ለሰዋስው ትምህርቱ የሚኖራቸው ፍላጎትና ተነሳሽነት እንደሚጨምር በምዕራፍ ሁለት ስር የምሁራኑ ገለጻ ያስረዳል፡፡ በተጨማሪም አጋዥ መሳሪያዎችን እንደ ስእል፣ ሠንጠረዥ፣ ምንባብ፣ የመሳሰሉትን በመጠቀም ማስተማር ትምህርቱን አይረሴ ለማድረግና ተማሪዎች በቶሎ እንዲረዱት እንዲሁም ከራሳቸው ህይወት ጋር እንዲያዋህዱ ለማድረግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ይኖረዋል፡፡ ይሁንና ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በአውድ የመጠቀም እና ተማሪዎች ከህይወት ገጠመኛቸው ጋር እንዲያዋህዱ አድርገው የማስተማሩ ሁኔታ አለመታየቱን የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡ እንዲሁም እነዚህ ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ አጋዥ መሳርያዎችን አልፎ አልፎ የሚጠቀሙ መሆናቸውን ቢገልጹም በምልከታና ከተማሪዎች የጽሑፍ መጠይቅ በተገኙ መረጃዎች መምህራኑ የአጋዥ መሳሪያዎችን የመጠቀም ሁኔታቸው ተከታታይነት የሌለውና በጣም ዝቅተኛ መሆኑን ለመመልከት ተችሏል፡፡

8. በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት መምህራን ለተማሪዎች በየደረጃው ምጋቤምላሽ መስጠት የተማሪዎች የመማር ፍላጎት እንዲጨምር ያደርጋል፤ በራሳቸውም የመተማመን ስሜት እንዲያጎለብቱ ይረዳቸዋል፡፡ በመሆኑም የተተኳሪ መምህራን የምጋቤ ምላሽ አሰጣጥን ለማየት እንደተሞከረው በልምምድ ደረጃ ወዲያውኑ እርማት የሚሰጡ ሲሆን በአፍልቆት ደረጃምየተማሪዎች ተግባቦት ሳይቋረጥ ማስታወሻ በመያዝ መጨረሻ ላይ ምጋቤ ምላሽ

መስጠት ሲገባቸው ተተኳሪ መምህራኑ ግን የተማሪዎችን ተግባቦት በማቋረጥ ምጋቤ ምላሽ ሲሰጡ ተስተውሏል፡፡ የሚሰጡት ምጋቤ ምላሽም (እርማት) ሁሉንም ተማሪዎች ባሳተፈ መልኩ ሳይሆን ፊት ለፊት ለተቀመጡና እጅ ላወጡ ተማሪዎች ብቻ የሚሰጥ እንደነበር በክፍል ውስጥ በተደረገው ምልከታና ከተማሪዎች የጽሁፍ መጠይቅ በተገኘው መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ ለመምህራኑ በተደረገ ቃለመጠይቅም ተተኳሪ መምህራኑ ማስታወሻ በመያዝ ምጋቤ ምላሽ የመስጠቱ ሁኔታ ያልተለመደ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህ ምክንያት ሲሰጡ ደግሞ ለክፍለ ጊዜው የተሰጠው ሰዓት በቂ ባለመሆኑ ለእያንዳንዱ ተማሪ ማስታወሻ ይዞ ምጋቤ ምላሽ መስጠት አዳጋች እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የሚሰጥ ምጋቤምላሽ ደግሞ የተማሪዎችን ተነሳሽነት የሚቀንስ፣ የማያበረታታ፣ ተግባቦትን የሚያደናቅፍ እና አሳታፊነት የጎደለው እንደሆነ የጥናቱ ግኝት አመልክቷል፡፡

## 5.2. የመፍትሄ ሀሳቦች

ከላይ በማጠቃለያው ለመግለጽ እንደተሞከረው በ8ኛ ክፍል ውስጥ የሚታየውን የሰዋስው ትምህርት ይዘት የክፍል ውስጥ አቀራረብ እና አተገባበር ከሥነትምህርታዊ ሰዋስው ንድፈሀሳብ አንጻር ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በሚያቀርቡበት ወቅት የሚጠቀሙት የማስተማሪያ ስልቶች በተማሪዎች የተግባቦት ብቃት ላይ ያላቸው አወንታዊ ገጽታና አሉታዊ ተጽእኖዎች ለይቶ ማወቅ ሲሆን ለታዩት ችግሮች ደግሞ የመፍትሄ ሀሳቦችን ማቅረብ ነው፡፡ ይህንንም ከላይ በማጠቃለያው ክፍል የታዩትን ተግዳሮቶች አስወግዶ (ቀርፎ) የመማር ማስተማሩን ሂደት የተሻለና ውጤታማ ያደርጋሉ ተብለው የታመነባቸው የመፍትሄ ሀሳቦች ከዚህ ቀጥሎ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

1. የመምህራኑን የትምህርት ዝግጅት በተመለከተ በተተኳሪ ትምህርት ቤቶች የሚያስተምሩ የቋንቋ መምህራን ትምህርቱን ከማቅረባቸው በፊት በቂ ዝግጅት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ ይህም ከተማሪዎች እድሜ፣ የክፍል ደረጃ፣ ከመጡበት ማህበረሰብ ጋር የሚጣጣም ይዘት ላይ በቂ ዝግጅት አድርገው ቢያስተምሩ መልካም ነው፡፡ በተጨማሪም የዕለቱ ዓላማም አንድ ሆኖ እሱም ሊተገበርና ከግብ መድረስ የሚችል ቢሆን እንዲሁም የሚያቀርቧቸው የተለያዩ ምሳሌዎችና መልመጃዎች ሁሉንም ተማሪዎች የሚያሳትፉ ቢሆኑ ይመረጣል፡፡

2. በጥናቱ ተተኳሪ የሆኑ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ ተማሪዎቹ የታላሚውን ቋንቋ ቅርጽ፣ ፍችና አጠቃቀም በቀላሉ እንዲረዱ በክፍል ውስጥና ከክፍል ውጭ የተማሪዎችን የህይወት ገጠመኝ በአውድ በመጠቀም ቢያስተምሩ፣ እንዲሁም ትምህርቱን ተጨባጭ እና አይረሴ ለማድረግ የተለያዩ መርጃ መሳሪያዎችን እንደ ሠንጠረዥ፣ ስእል፣ አጋዥ መጽሐፍት፣ ወዘተ. በመጠቀም ቢያስተምሩ የተሻለ ውጤት ለማምጣት ያስችላል፡፡
3. መምህራኑ የሰዋስው ትምህርት ይዘትን ሲያቀርቡ የማለማመጃ ስልቶችን እንደ ምልልስ፣ ሚና ጨዋታ፣ የተለያዩ ነገሮችን በማሳየት፣ ወዘተ. በክፍል ውስጥ በመጠቀም ማስተማር የተማሪዎች ተግባቦት እንዲዳብር ይረዳል፡፡ ስለዚህ ተተኳሪ መምህራን እነዚህን የሰዋስው ማለማመጃ ስልቶችን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ በማድረግ የተማሪዎችን የተለያዩ ገጠመኞች በመጠቀም ተማሪዎቹ ቃለምልልስ እንዲያደርጉ፣ የሌላን ሰው ሚና በመውሰድ ጭውውት በማድረግ እንዲለማመዱ፣ የተለያዩ አውዶችን በመፍጠር የክፍል ውስጥ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ማስተማር አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፡፡
4. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርቱን ሲተብሩ ተማሪዎች የታላሚውን ቋንቋ ሰዋስዋዊ መዋቅር ተጠቅመው ተግባቦት እንዲያከናውኑ ትምህርቱን ግልጽ፣ አሳታፊና አፍላቂ በሆነ መንገድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡
5. በመማር ማስተማር ሂደት ወቅት መምህራን ለተማሪዎቻቸው ምጋቤምላሽ መስጠት የተማሪዎቹ የመማር ፍላጎት እንዲጨምር ያደርጋል፤ በራስ የመተማመን ስሜት እንዲያጎለብቱ ይረዳቸዋል፡፡ ስለዚህ የቋንቋ መምህራን ተማሪዎች ለሚፈጽሙት ሰዋስዋዊ ስህተት ማስታወሻ በመያዝ መጨረሻ ላይ ምጋቤምላሽ ቢሰጡ መልካም ነው፡፡
6. የጥናቱ ተተኳሪ መምህራን የሰዋስው ትምህርት ይዘትን በክፍል ውስጥ ሲያቀርቡ ሰዋስውን በተናጠል ከማስተማር ይልቅ ከሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ከማዳመጥ፣ ከመናገር፣ ከማንበብና ከመጻፍ ጋር አቀናጅተው በማስተማር የተማሪዎች ተግባቦት እንዲዳብር ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ቢያደርጉ የተሻለ ውጤት ላይ ለመድረስ ያስችላል፡፡

**ዋቢመጻሕፍት**


መሰሉ መንግስቱ፡፡(1994፡፡‹‹የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ስነዘዴ፡፡››ዲላ፣ዲላ መምህራን ትምህርትና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የርቀት ትምህርት ክፍል (ያልታተመ)፡፡

………… (2000)፡፡*የአማርኛ ሰዋስው*፡አዲስ አበባ፣እሌኒ ማ.ኃ.የተ.የግ.ማህበር፡፡

………… (2010)፡፡*አጭርና ቀላልየአማርኛ ሰዋስው*፡አዲስ አበባ፣አልፋ ማተሚያ ቤት፡፡

አልፋ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ፡፡ (2006)፡፡ *ክሂሎችን የማስተማር ስነ ዘዴ፡፡* አዲስ አበባ ፡ አልፋ ዩኒቨርሲቲ የርቀት ትምህርት ክፍል፡፡

አማረ ተሾመ ሙላቱ፡፡(2021)፡፡የሰዋስው ትምህርት ይዘቶች አቀራረብና አደረጃጀት ፍተሻ ፤በ 2004 ዓ.ም.ተሻሽሎ በታተመው የ 11ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ መነሻነት የተደረገ ጥናት፤ጎንደር ዩኒቨርሲቲ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ አማርኛ ትምህርት ክፍል (ያልታተመ)፡፡

አበበ መብራቴ፡፡(1998)፡፡‹‹በወላይታ ዞን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች 9ኛ ክፍል ውስጥ የሰዋስው ትምህርት አተገባበር ግምገማ በሦስት ትምህርት ቤቶች ናሙናነት ›› ለማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ ፣ አዲስ አበባ ፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ያልታተመ) ፡፡

ኢያሱ መሰለ፡፡(2003)፡፡‹‹በ1997 ዓ.ም. በተሻሻሉት የ 9ኛ እና የ 10ኛ ክፍል የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጻህፍት የሥነ ትምህርታዊ ሰዋስው ይዘቶች አመራረጥ፣ አቀራረብና አደረጃጀት ግምገማ››ለማስተር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ ፣ አዲስ አበባ፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ያልታተመ) ፡፡

ከበደ አየለ፡፡(1999)፡፡‹‹የሰዋስው ትምህርትን በክፍል ውስጥ የማስተማሪያ ብልሃቶች አጠቃቀምና አተገባበር ፍተሻ፡- በኦሮምያ ክልል በአርሲ ዞን በሚገኙ አራት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በ 9ኛ ክፍል ናሙናነት›› ለአም.ኤ.ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡አዲስ አበባ፡የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ትምህርት ክፍል (ያልታተመ)፡፡

ጌታሁን አማረ፡፡(1997)፡፡*ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ፡፡* አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

………(2011)። *ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ* (የተሻሻለ ሁለተኛ እትም)። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ቢ.ኢ.ማተሚያ ቤት።

……(2013)።*የአማርኛ ሰዋስው፡ህትመት ጃጃው አታሚዎችና ዴቨሎፐርስ ኃ.የተ.የግ.ማ.*።

Adugna Guade.(2008 ).''High School English Language Teachers Beliefs About Grammar Teaching and Their Actual Classroom Practice. Four High School In Amhara Regionin Focus'' Addis Abeba University. Department of Foreign Language and Literature Graduate Program (Unpublished).

Batstone,R.(1994).*Grammar*.Oxford;Oxford University Press.

Best,J.& Kahn,J.(1993).Research in Education ($7^{th}$ eds). New Delhi: Prentice Hall of India.

Bygate.M.etal.(eds.)(1994).*Grammar and the Language Teacher*. New York: Prentice Hall. Pp.215–223.http://www.kieliverkosto.fi/article/ opettajan-pedagoginen-sisaltotieto-kielitiedon-opetuksen-nakokulmasta/.com,"

Carter, R.(1990). *Knowledge about Language and Curriculum*, Hadder stoughter: London Sydney Auckland.

Celce-Murcia,M.(1991).*Teaching English as a Second or Foreign Language*($2^{nd}$ed). Losangeles; Heinle and Heinle Publishers.

Celce-Murcia,M.and Sharon,H.(1988).*Techniques and Resources in Teaching Grammar.* Oxford :Oxford University Press .

Chalker,S.(1994).*Pedagogical GrammarPrinciples and Problems*. In M. Bygate, etal. (eds).*Grammar and The Language Teacher*. New York: Prentice Hall. Pp.31- 44.

Cook,V.(2001).*Second Language Learning and Language Teaching*($3^{rd}$ eds). New York: Oxford University Press.

Corder,S.(1975).''The Edinburgh Course in Linguistics.'' In Bygate, M. etal.(eds). *Grammar and The Language Teacher*. New York: Prentice Hall.

Crystal,D.(1987).‘’The Cambridge Encyclopedia of Language.’’In Bygate,M.etal. (eds).*Grammar and The Language Teacher*. NewYork: Prentice Hall.

Cunningsworth,A.(1984).*Evaluating and Selecting EFL Teaching Materials*. Oxford:Heinemann.

Ellis, R.(1997).*Research and Language Teaching*. Oxford : OUP.

``````` (2000).’’The Place of Grammar Instruction in The Second Language/ Foreign Language Curriculum.’’ In Brown, K, et al. (eds). *Language and Linguistics*. Encyclopedia, Oxford: Elsevier Ltd. Vol.9. Pp,28-54.

```````(2006).‘’Current Issues in The Teaching of Grammar: As SLA Perspective.’’*TESOLQuarterly*. Auckland,New Zealand; University of Auckland. Vol.40.No.1,Pp.83-107.

Grant, N.(1987). *Making the Most of Your Text Book*. London; Longman.

Greembaum.S.(1988).*Good English and the Grammar*. London: Longman.

Harmer,J.(1987).*Teaching and Learning Grammar*.Longman; Longman Group Ltd.

……… (1991).*The Practice of English Language Teaching.* London;Longman Ltd.

Jean,G.& Simard, D.(2011).*Grammar Teaching and Learning in L2: Necessary, But Boring? Foreign Language Annals*, Pp. 467–494.

Kachru,Y.(2010).*Pedagogical Grammars for Second Language Learning. In M. Berns (eds). Concise Encyclopedia of Applied Linguistics*. Amsterdam: Elsevier, Pp.172–178

Krashen,S.D.(1995).*Principles and Practice in a Second Language Acquisition*. London ; Prentice Hall Macmillan.

LarsenFreeman,D.(1991).‘’Teaching Grammar.’’InCelce-Murcia,M.(eds). *Teaching English as a Second or Foreign Language*. Botston: Heinmann Publishers. Pp.246=295.

Littlewood,W.(1984). *Foreign and Second Language Learning*. Cambridge;CPU.

……….(2012).*Communication-oriented Language Teaching*:*Where Are We Now? Where Do We Go From Here? Language Teaching*.Pp.349–362.

Mirsolow.(2004).‹‹On The Effectiveness of Options in Grammar Teaching.›› Retrieved From ;http:// w.w.w.the freeLiberary.On Jan. 28/2023.

Michal,B.(2007).‘’PedagogicalGrammar.’’Retrieved From;http;//knoll.google.com.on Nov.16/2022.

Mitchell, R.(1994). *Grammar and Teaching*. In M. Bygate et al.(eds).*Grammar and The Language Teacher*. New York: Prentice Hall, Pp.215–223.

Newby, D.(2000).*Notions and Functions. In:Byram,M.(ed.),Routledge Encyclopedia of Language Teaching and Learning.* London: Routledge, 449-451.

Nordquist,J.(2006).‘’PedagogicalGrammar.’’RetrievedFrom; http;//inwikipidia,org/wiki.on Nov.7/2022.

Nunan, D.(1991).*Language Teaching Methodology A Textook for Teachers*. London: Prentice Hall International LTD.

Odlin,T.(ed.)(1994).*PerspectivesonPedagogical Grammar*.Cambridge: Cambridge University Press.

Palmer, F.(1984).*Grammar.(2nd eds.)*.Harmsworth:Penguins Books.

Rättyä,K.(2014).*Opettajan Pedagoginen Sisältötieto Kielitiedon Opetuksen Näkökulmasta.Kieli,Koulutus Ja Yhteiskunta.Retrieved From Mitchell, R. 1994. Grammar and Teaching. In M.*

Richards, J.C.& Schimdit, R.(2002).*Longman Dictionary of Language Teaching and Applied Linguistics.* London :Longman.Ltd.

Richards,J.C.&Rodgers,T.(1995).Approaches and Methods in Language Teaching. Cambridge:Cambridge University Press.

Rieger,B.(2009).*Hungarian University Students Beliefs about Language Learning; a Questionnaire Study*. Pp.97-113.

Stern, H.H.(1991).*Fundamental Concepts of Language Teaching*. Oxford: OUP,

Taylor J.(2008).*Some Pedagogical Implications of Cognitive Linguistics. In. S. De Knop & T.De Rycker (eds.).Cognitive Approaches to Pedagogical Grammar.A Volume in Honour of René Dirven. Berlin: Mouton de Gruyter*, Pp.38–65.

Thornbury,S.(1999).*How to Teach Grammar*. London; Longman.

Ur,P.(1988).*Grammar Practice Activities:A Practical Guide For Teacher*. Cambridge:Cambridge University Press.

Westney,P.(1994).*Four Rules and Pedagogical Grammar.In T.Odlin (ed.), Perspectives on* Pedagogical Grammar. Cambridge: Cambridge University Press, Pp. 72–96.

Widodo,H.(2006).‹‹Approaches and Procedures for Teaching Grammar.››Retrieved From; http:// www.education Waikato ,ac.nz/files/.on Feb.20/2023.

Wilkins,D.(1976).Linguistics in Language Teaching, New York:Edward Anrold Publishers Ltd.

# አባሪዎች

## ማረጋገጫ

“የአማርኛ ሰዋስው ትምህርት የክፍል ውስጥ አተገባበር ፍተሻ (በሰሜን ሸዋ ዞን በደብረ ሊባኖስ ወረዳ በድሬ ጅቦ እና በአባገዳ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች፣በ8ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የቀረበ ጥናት)” በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት የአማርኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሁፍ ትምህርት ክፍል ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረብኩት ይህ ጥናት በማንኛውም አካል ያልተሰራና ወጥ የራሴ ሥራ መሆኑን፣ የተጠቀምኩባቸው ድርሳናትን በትክክል ዋቢ መሆናቸውን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

**በጽጌ ግርማ**

________________

መስከረም 2016